ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስ እና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በኢሉ አባቦር ዞን በዶረኒ ወረዳ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረግ ሥርዓት ትንተና

በ

ሉባባ አህመድ እንድሪስ

ለኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

2012 ዓ.ም

ጅማ

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ


## የሶሻል ሳይንስ እና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር


# በኢሉ አባቦር ዞን በዶረኒ ወረዳ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረግ ሥርዓት ትንተና


በ

ሉባባ አህመድ

አማካሪ፡- ጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር)


ለኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


2012 ዓ.ም

ጅማ

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስ እና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ (አማርኛ) ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

## በኢሉ አባቦር ዞን በዶረኒ ወረዳ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረግ ሥርዓት ትንተና

በ

ሉባባ አህመድ እንድሪስ

**የፈተና ቦርድ አባላት**

| | ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| 1. አማካሪ | ________________________ | __________ | _________ |
| 2. የውስጥ ፈታኝ | ________________________ | __________ | _________ |
| 3. የውጭ ፈታኝ | ________________________ | __________ | _________ |

# ማረጋገጫ

ለዚህ ጥናት የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች በሙሉ በአግባቡ ተጠቅሜያለሁ። ይህ ጥናት በተከናወነበት አካባቢ ከዚህ በፊት ያልተሠራ እና የመጀመሪያ ጥናት መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም፡- ሊባባ አህመድ

ፊርማ ____________

ቀን _____________

# ምስጋና

በመጀመሪያ ለዚህ ላበቃኝ አላህ "አልሃምድሊላ" በማለት ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በመቀጠል ጥናቱ ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው አቅጣጫ በመስጠትና በማረም ይህን ቅርጽ ይዞ እስኪወጣ ድረስ እገዛ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር) ከማንም በላይ አመሰግናሁ። በዚህ ጥናት ውስጥ በልዩ ልዩ መልኩ የበኩላቸውን ድጋፍ እና ትብብር ያደረጉልኝ ሰዎች ለሥራዬ መሳካት የነበራቸው ተሳትፎ የጎላ ነበር።

በፎክሎርና በስነጽሁፍ የትምህርት ዘርፎች የጠለቀ እውቀት እንዲኖረኝ ላስተማሩኝ የኮርስ መምህራን በሙሉ ምሥጋናዬ የጎላ ነው። ለለማ ንጋቱ (ዶ/ር) እድሜና ጤና ይስጥልኝ። በሌላ መልኩ አይዞሽ ትደርሻለሽ እያሉ በሀሳብ ሲያበረታቱኝ ለበነበሩ ጓደኞቼ በሙሉ የከበረ ምስጋናዬ ይድረሳቸው። በተለይም በየደረጃው ስህተቶቼን በማረምና አስተያየት በመስጠት ለተባበሩኝ ጓደኞቼ ፋሲካ ወ/ሚካኤልና አስፋው አባተ ምሥጋናዬ የላቀ ነው።

እንዲሁም በመስክ ቆይታዬ መረጃ በማቀበል በከፍተኛ ቅንነት ትብብር ላደረጉልኝ የዶረኒ ወረዳ ማህበረሰብ እና በየቀበሌዎቹ አብረውኝ በመዘዋወር እገዛ ላደረጉኝ አቶ አረጋ ሁንዴና አቶ ሞገስ ከበደ ከልብ አመሰግናችኋለሁ፡፡
እድሜዬን ሙሉ እገዛ ላደረጋችሁልኝ ቤተሰቦቼ ልዩውን ምስጋና ውሰዱ፤ ከሁሉም በላይ ግን የትምህርት ፍላጎቴ ተሳክቶ ለዚህ እንድበቃ በየትኛውም ጊዜ እና ሁኔታ ከጎኔ ላልተለየሽ ውዷ እህቴ መሬም አህመድ ከልብ የመነጨ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ። ወንድሜ የሱፍ አህመድና እህቴ መዲና መሐመድ በዚህ ስራ ላይ የምትችሉትን ብቻ ሳይሆን የማትችሉትንም አድርጋችኋልና ምስጋናዬ ከልብ ነው።

በመጨረሻ ያለብህን የስራ ጫና፣ ድካም እንዲሁም የጊዜ እጥረት ተቋቁመህ ይህ ጥናት ስኬታማ እንዲሆን በገንዘብም ሆነ በስነልቦና ድጋፍ ላደረክልኝ ዉዱ ባለቤቴ ለክንዴ አንለይ (ዶ/ር) ስፍር ቁጥር የሌለው ምስጋና ለአንተ ይሁን። ድካምህ ለፍሬ በቅቷልና ደስ ይበልህ!

**ሙዳዬ ቃላት**

ሉቢ ፡ ለስጦታ የሚላኩ እቃዎች

ሙካ ኡርጌሳ ፡ ጥሩ ጠረን ያለው የመፋቂያ እንጨት

ሚልኪ ፡ ገድ

ማደሮ ፡ ማዕድ ማቅረቢያ

ረገዳ ፡ ጭፈራ፣ሽብሸባ

ሲርባ ዱርባ ፡ የልጃገረዶች ጭፈራ

ሻርፌ ፡ ቆለምሽሽ

ቡሉኮ ፡ ከጥጥ የሚሰራ ባህላዊ የእናቶች ልብስ

ቡቲ ፡ ጠለፋ

ቡና ቀላ ፡ ከድፍን ቡና የሚዘጋጅ ባህላዊ ምግብ

ነቀታ ፡ በተጋቢዎች ቤተሰብ ስምምነት የሚከወን የጋብቻ አይነት

ነቂ ፡ በወንድ ቤተሰብና በሙሽራው አማካኝነት ከሙሽራዋና ከሙሽራዋ ቤተሰብ ፍቃድ

አረብሶ ፡ የመበሻሸቂያ ስድብ

አሴና ፡ ከቤተሰብ ፍቃድ ውጪ በሁለቱ ተጋቢዎች ስምምነት የሚከናወን የጋብቻ አይነት

ኢጨቻ ፡ ችካል

ውጪ የሚደረግ ጋብቻ አይንት

ዋርሳ ፡ የባል ወንድም

ደለጋ ፡ የእናቶች ጭፈራ

ድንግል ፡ ሴት ያላወቀ ወንድ፣ወንድ ያላወቀች ሴት ፣የግብረ ስጋ ግንኙነት ያልፈጸሙ

ጉሜ ፡ ጥምዝ የእጅ አንባር

# ማውጫ

ምስጋና ........ I
ሙዳዬ ቃላት ........ II
ማውጫ ........ III
አጠቃሎ ........ IV
1. መግቢያ ........ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 2
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3
1.3. የጥናቱ አላማ ........ 5
1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ........ 5
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 6
1.6. የጥናቱ ወሰን ........ 6
1.7. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች ........ 7
1.8. የመስክ ተሞክሮ ........ 8
2. ክለሳ ድርሳናት ........ 12
2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ........ 12
2.1.1. የባህል ጽንሰ ሀሳብ ........ 12
2.1.2. የፎክሎር ጥናት ቅኝት ........ 14
2.1.3. ልማድ ........ 15
2.1.4. ጋብቻ በሰውልጅ ህይወት ........ 16
2.1.5. የድንግልና ምንነት ........ 18
2.1.6. ድንግልና ከጋብቻ አንጻር ........ 18
2.1.7. ድንግልናን እስከ ጋብቻ ቀን ጠብቆ ማቆየት ያለው ጠቀሜታ ........ 20
2.1.8. የድንግልና ሀይማኖታዊ አስተሳሰቦች ........ 22
2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 22
2.3. የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ ........ 30
2.3.1. የዶረኒ ወረዳ መገኛ ........ 30
2.3.2. በዶረኒ ወረዳ የሚኖረው የኦሮሞ ማህበረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ ........ 31

2.3.3. የዶረኒ ወረዳ ስያሜ ........................................................................32
2.3.4. ጥንታዊ የዶረኒ አስተዳደር ሥርዓት ..................................................32
2.3.5. የዶረኒ ወረዳ እና የገዳ ሥርዓት ውድቀት ..........................................33
2.3.6. የዶረኒ ወረዳ የኦሮሞ ማህበረሰብ የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት ........................33
3. የጥናቱ ዘዴና አካሄድ ................................................................................ 35
3.1.የጥናቱ ዘዴ ............................................................................................ 35
3.2. የንሞና አመራረጥ ስልት ..................................................................... 35
3.2.1. የቦታ ንሞና አመራረጥ.......................................................................... 35
3.2.2. የመረጃ አቀባዮች ንሞና አመራረጥ .................................................... 36
3.3.የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ................................................................. 37
3.3.1. ቃለ መጠይቅ .................................................................................... 38
3.3.2. ቡድን ተኮር ውይይት ........................................................................ 39
3.3.3. ሰነድ ፍተሻ ....................................................................................... 39
3.4.የመረጃ አደረጃጀትና መተንተኛ ዘዴ ...................................................... 40
3.4.1. የመረጃ አደረጃጀት ............................................................................ 40
3.4.2. የመረጃ ትንተና .................................................................................. 40
4. የመረጃ ትንተና ........................................................................................ 42
4.1.በኢሉ አባቦር ዞን በዶረኒ ወረዳ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት ትንተና.................................................................... 42
4.1.1. ቅድመ ጋብቻ ..................................................................................... 44
4.1.1.1. የትዳር አጋር መረጣ ........................................................................ 44
4.1.1.2. ሚልኪ (Milkii) ማየት ........................................................................ 48
4.1.1.3. ሉቢ (Lubii) ማድረስ ......................................................................... 49
4.1.1.4. የቀለበት ሥርዓት ............................................................................. 51
4.1.1.5. ሚዜ መረጣ .................................................................................... 53
4.1.1.6. የሙሽሮች አመጋገብ ......................................................................... 54
4.1.1.7. ሲርባ ዱርባ (sirba durbaa) ............................................................... 54
4.1.2. ጊዜ ሰርግ ........................................................................................... 55
4.1.2.1. ረኮ ቀሉ (Rakoo Qaluu) .................................................................. 61

4.1.2.2. አርጋ ሚዜ (Argaa Minzee) ........................................... 65
4.1.3. ድህረ ሰርግ ................................................................. 67
4.2.“ሲርባ ዱርባ” እና ድንግልና ........................................................ 67
4.3. ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት ማህበራዊ
ተግባራት ........................................................................ 73
4.3.1. ጠንካራ ማህበራዊ ግንኙነትን ከመፍጠር አኳያ ያለው ፋይዳ ..................... 73
4.3.2. ከስነልቦና አኳያ ያለው ፋይዳ ..................................................... 74
4.3.3. ጤናማ ማህበረሰብ ከመፍጠር አኳያ ያለው ፋይዳ ................................. 78
4.3.4. ከኢኮኖሚ አኳያ ያለው ፋይዳ .......................................................79
4.4. በሥርዓቱ ላይ እየታዩ ያሉ ለውጦችና የማህበረሰቡ አስተያየት ........................80
4.4.1. የብዙሃን መገናኛ እና የማህበራዊ ድህረ ገጾች መስፋፋት ......................82
4.4.2. ሀይማኖትዊ ተጽዕኖ.......................................................... 83
4.4.3. የዘመናዊ አስተሳሰብ ........................................................ 84
4.4.4. ዘመናዊ አስተዳደር .......................................................... 85
5. ማጠቃለያ እና አስተያየት ........................................................ 87
5.1. ማጠቃለያ ........................................................................ 87
5.2. አስተያየት ...................................................................... 89
ዋቢዎች ................................................................................ 91
አባሪዎች...................................................................................96

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ዋና ትኩረቱን ያደረገው በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልል "በኢሉ አባቦር ዞን ዱረኒ ወረዳ በኦሮሞ ማህበረሰብ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረግ ሥርዓት ትንተና" በሚል ርዕስ የተካሄደ ነው። ጥናቱ በማህበረሰቡ ከሚከወኑ የሰርግ ሥርዓቶች መካከል በነቀታ (Naqataa) የጋብቻ አይነት ድንግልናቸውን ጠብቀው ለጋብቻ ለበቁ ሴቶች ስለሚደረገው ሥርዓት፣ ለማህበረሰቡ የሚሰጠዉን ማህበራዊና ስነልቦናዊ ፋይዳ እንዲሁም ሥርዓቱ አሁን ስላለበት ሁኔታ ለማሳየትና ሰንዶ ለማኖር አልሞ የተነሳ ነው።

አጥኚዋ የጥናቱን አላማዎች ከግብ ለማድረስ ገላጭ የምርምር ዜዴን ተጠቅማለች። በጥናቱ በወረዳው ካሉ አስራ ሁለት ቀበሌዎች መካከል በአላማ ተኮር የንሞና ዘዴ በተመረጡ አራት ቀበሌዎች ላይ መረጃዎች ተሰብስበዋል። መረጃ አቀባዮቹ ታላሚ የንሞና ዘዴና በጓድ ጥቆማ የተመረጡ ሲሆን የአካባቢውን ባህል ጠንቅቀው የሚያውቁ የባህሉ ባለቤቶችና በሥርዓቱ ጋብቻቸውን የመሰረቱ ናቸው። ቃለ መጠየቅ፣ ቡድን ተኮር ውይይት እንዲሁም ሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ ዜዴዎችን በመጠቀም የጥናቱ መረጃዎች ተሰብስበዋል። መረጃዎቹም እንዳስፈላጊነታቸውና እንደ መረጃ ሰጪዎች ፍቃደኝነት በቪድዮ፣ በፎቶ ግራፍ፣ በመቅረጸ ድምጽና በማስታዎሻ ደብተር ተሰንደዋል። የተሰበሰቡ መረጃዎችም በኮድ በመከፋፈል ተደራጅተው በአይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ተተንትነው ቀርበዋል።

የጥናቱ ወጤት እንደሚያመለክተው በኢሉ አባቦር ዞን ዱረኒ ወረዳ የኦሮሞ ማህበረሰብ የተለያዩ የጋብቻ አይነቶች ያሉት ሲሆን ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት በነቀታ (Naqata) የጋብቻ አይነት ይከወናል። በሥርዓቱ ከትዳር መረጣ ተጋቢዎች ጋብቻ እስከሚመሰርቱበት ቀን ድረስ በተለያዩ ሂደቶች ውስጥ ይታለፋል። ማህበረሰቡም ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሙሽራዋን ክብርና ጨዋነት ለማሳየት ሲሉ የተለያዩ ክወኔዎችና ተግባራት እንደነበራቸው የጥናቱ ወጤት ያሳያል።

በወረዳው የሚኖረው የኦሮሞ ማህበረሰብ ልጃገረዶች የከንፈር ወዳጅ እንዲኖራቸው እንዲሁም በአብዛኛው በሌሊት ጊዜ በሚከወን ባህላዊ ጭፈራ ላይ መሳተፍ ይፈቀድላቸዋል። በመሆኑም ወጣቶቹ በባህላዊ ጭፈራው በሌሊት ሜዳ ላይ ከከንፈር

ወዳጆቻቸው ጋር አብሮ የመጨፈር፣ የመሳሳም እና የመተቃቀፍ መብት አላቸው። በተቃራኒው ከዚህ ጋር ተያየዞ የሚያጋጥሙ ፈተናዎችን ተቋቁመው ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር መብቃት እንደሚጠበቅባቸው በጥናቱ ተረጋግጧል።

ድንግልናን ጠብቆ ለትዳር መብቃትን አስመልክቶ የሚደረገው ሥርዓት ለማህበረሰቡ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ አስመልክቶ በነቀታ የጋብቻ አይነት በተጋቢዎች ቤተሰብ ደረጃ በከፍተኛ መጠናናት የሚመሰርት በመሆኑ ትስስሩ ከተጋቢዎች አልፎ ጠንካራ ማህበራዊ ግንኙነትን ይፈጥራል። ከስነልቦና አኳያም ለተጋቢዎቹም ሆነ ለተጋቢዎቹ ቤተሰቦች መረጋጋትን፣ ክብርን፣ ደስታን እንዲሁም ፍቺን ከመቀነስ አንጻር ጠቀሚታው የጎላ ሲሆን በግብረ ስጋ ግንኙነት አማካኝነት ከሚተላለፉ በሽታዎችና ከስነ ተዋልዶ ጤና አንጻርም ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል። ነገር ግን ባህላዊ ሥርዓቱ በተለያዩ ምክንያቶች ማለትም በቴክኖሎጂ መስፋፋት፣ በሀይማኖታዊ ተጽኖ፣ በዘመናዊነት አስተሳሰብ መስፋፋት እና በዘመናዊ አስተዳደር ህጎች ሳቢያ በአሁን ወቅት ሙሉ በሙሉ እንደጠፋ ማረጋገጥ ተችሏል።

ከላይ የቀረቡትን የጥናቱን ግኝቶች መሰረት በማድረግ ድንግልናቸው ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት ለተጋቢዎች ሆነ ለተጋቢዎች ቤተሰብ በሚያስገኘው ስነልቦናዊ ፋይዳ የትዳር ፍቺን ከመቀነስ አኳያ አስተዋጾ የጎላ በመሆኑ ጠቃሚ ባህሉ የሚያገግመበት ሁኔታ ቢፈለግ መልካም ይሆናል፤ እንዲሁም ባህላዊ ሥርዓቱ ከመጥፋቱም ባሻገር ስለባህሉ ጠንቅቀው የሚያውቁ የባህሉ ባለቤቶች በእድሜ መግፋት ምክንያት ከማለፋቸው በፊት መረጃው ተሰንዶ ለተተኪው ትውልድ የሚተላለፍበት መንገድ ቢፈልግ ፤ በተጨማሪም በወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ተቀርጸው የተቀመጡትን ባህላዊ እሴቶች በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ወደ ህዝብ የሚደርሱበት ሁኔታዎች ቢመቻች ጠቃሚ ይሆናል። በመጨረሻም በወረዳው እየከሰሙ ያሉ ፎክሎራዊ እሴቶች ሙሉ በሙሉ ከመጥፋታቸው በፊት ተቀርጸው የሚቀመጡበት ሁኔታ ቢፈጠር እና ሌሎች ተመራማሪዎች ይህንን ጥናት መነሻ በማድረግ በወረዳው የሚታወቁ የጋብቻ አይነቶችን በንጽጽር እንዲሁም እያንዳንዱ ባህላዊ ሥርዓቶችን ከፎክሎራዊ ጽንሰ ሃሳብ አንጻር ቢያጠኑ መልካም ነው በማለት አጥኚዋ አስተያየቷን አስቀምጣለች።

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ሀገረሰባዊ ልማድ (folk custom) አንዱ የፎክሎር ዘውግ ሲሆን አንድ ማህበረሰብ በተደጋጋሚ የሚከዉነዉን ድርጊትና ቅደም ተከተላዊ ሥርዓት መሰረት በማድረግ የሚቀርብ የጥበቦች ጥቅል መጠሪያ ነው (Dorsan፣ 1972) ። ሰለሞን (2007) "ማህበረሰቡ መልካም ህይወት ለመኖር ጠቃሚ ናቸው በሚል በዕለት ዕለት ህይወቱ የሚከውናቸውና፣ እንዲህ ቢሆን በህይወቴ ላይ ችግር ይገጥመኛል የሚፈራቸው፤ ይህን ባደርግ በህይወቴ ውስጥ የተሻለ ነገር ይገጥመኛል ብሎ የሚከውናቸው፤ ይህ ነገር ስለሚያስፈልገኝ እንዲህ ባደርግ ፍላጎቴ ማሟላት እችላለሁ ወዘተ. በሚል በውስጥ መንፈሳዊ እምነት የሚከውናቸው በርካታ ልማዶች አሉ" በማለት በሃገረሰባዊ ዕምነት ምንነት በገለፀበት ክፍል አብራርቷል። ታዲያ ይህ የፎክሎር ቅንጣት የሆነው ልማድ በሁሉም ማህበረሰብ ዘንድ ቢኖርም እንደየአካባቢውና እንደየባህሉ አይነት አከናወኑም የተለያየ ነው። የዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ትኩረት የሆነው ኦሮሞ ሰፊ ህዝብ ነው። ከዚህ ማህበረሰብ መካከል የኢሉ አባቦር ኦሮሞ ተጠቃሽ ነው። በኢሉ አባቦር ዞን፣ በዶረኒ ወረዳ የሚኖረዉ የኦሮሞ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ ባህሉን የሚያንጸባርቅባቸው የተለያዩ ልማዶች አሉት። ከነዚህ ልማዶች መካከል በሰርግ ወቅት ይደረጉ  የነበሩ ነገር ግን እየቀሩ የመጡ ሥርዓቶች ወይም ሃገረ ሰባዊ ሁነቶች ተጠቃሾች ናቸው። በአካባቢው ከሚጠቀሱት የሰርግ ሥርዓቶች በአሴና (Aseenna) ላገቡ፣ በነቂ (Naqii) ላገቡ፣ በቡቲ (Butii) ላገቡ እንዲሁም በነቀታ (Naqata) የጋብቻ ሥርዓት ድንግልናቸውን ጠብቀው ለጋብቻ ለበቁ ሴቶች የሚደረጉ ሥርዓቶች ጥቂቶቹ ናቸው። እነዚህ ሥርዓቶች በተለያዩ ተጽዕኖዎች ሳቢያ አንዳንዶቹ እየከሰሙ አብዛኞቹ ደግሞ ሙሉ በሙሉ እየጠፉ ይገኛሉ።

ጥናቱ በአምስት ምዕራፎች የተደራጀ ነው። በመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ ጥናቱ የሚያስገኘው ጠቀሜታና የጥናቱ ወሰን በቅደም ተከተል ቀርበዋል። በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትና ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት እንዲሁም ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ ዳራ በአጭሩ የተዳሰሰበት ክፍል ነው። በሦስተኛው ምዕራፍ የጥናቱ ዘዴ፣ የንሞና አመራረጥ ስልት፣ ለጥናቱ ጥቅም ላይ የዋሉ መረጃዎች እንዴትና በምን ዘዴ እንደተሰበሰቡ እና

እንደተመረጡ እንዲሁም የጥናቱ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ተዳሷል። አራተኛው ምዕራፍ ከመስክ የተገኙ መረጃዎች የተተነተኑበት ሲሆን የመጨረሻውና አምስተኛው ምዕራፍ የጥናቱ ማጠቃለያና አስተያየት የቀረበበት ነው። በመጨረሻም ዋቢ መጻሕፍት እና ሌሎች አባሪዎች ከማጠቃለያው በኋላ ቀርበዋል።

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ባህል ሰፊና ውስብስብ የሆነ፣ የሰው ልጅ ከሚኖርበት ማህበረሰብ የሚያገኘው /የሚማረው/ እውቀት ነው። በመሆኑም ባህል እምነት፣ ስነጥበብ፣ ስነምግባር፣ ህግና ደንቦች እንዲሁም ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ፣ የሚወረስ፣ ኑሮውን ለመምራት የሚገለገልባቸውን ቋንቋዎች፣ ወኪሎች፣ የሥነምግባር እሴቶችን የሚያጠቃልል ነው። ስለሆነም ባህል ከህብረተሰቡ ጋር ብቻ ተቆራኝቶ የሚገኝ እንጅ ከህብረተሰቡ ውጭ ለብቻው የራሱን ህልውና ጠብቆ መኖር የሚችል አይደለም (Tylor፣1871) ።

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በኢሉ አባቦር ዞን ዶረኒ ወረዳ በኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለሚበቁ ሴቶች ይደረግ የነበረውን ሥርአት፣ ለውጡ ምን እንደሚመስል ማሳየት እና ሰንዶ ማኖር ነው። የኦሮሞ ብሄረሰብ በርካታ ባህላዊ እሴቶች ያሉት ሲሆን ከእነዚህ መካከል አንዱ የሠርግ ሥርዓት ነው። ይህ ሥርዓት እንደየአካባቢው /መልከዓ ምድራዊ ልዩነትና አሠፋፈር/ እንደ የጋብቻ አይነቱ የአከባበር ሁኔታው ይለያያል። በመሆኑም ብሄረሰቡ የሰርግ ሥርዓቱን እንደ ልዩነቱ የሚከውናቸው ሥርአቶች ይለያያሉ።

ማህበረሰቡ በነቀታ (Naqata) የጋብቻ አይነት ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች በሚደረግ ባህላዊ ሥርዓት ላይ የሙሽራን ክብርና ጨዋነት ለማሳየት የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ ክዋኔዎች አሏቸው። በሌላ መልኩ ደግሞ በሰርግ ወቅት ሙሽራዋ ድንግልናዋን ጠብቃ ለጋብቻ መብቃቷን ወይም ድንግልናዋን ጠብቃ ለትዳር አለመብቃቷን ለማሳየት በወንዱ ሙሽራ ቤተሰቦች እና በሴቷ ሙሽራ ቤተሰቦች የሚከናወኑ ተግባራትም አሉ። እነዚህ ሁሉ ማህበራዊና ባህላዊ ፋይዳወች የያዙ ክዋኔዎች ደግሞ መጠናት አለባቸው።

ከዚህ ቀደም በኢሉ አባቦር ዞን በዶረኒ ወረዳ ድንግልናቸውን ጠብቃው ለጋብቻ ለበቁ ሴቶች የሚከወን ሥርዓትን በተመለከተ በመጀመሪያ ድግሪ፤ በሁለተኛ ድግሪም ሆነ በሌሎች የተጠኑ ጥናቶችን አላገኘሁም። ነገር ግን በአካባቢ ባይሆንም በኢትዮጵያ ደረጃ

የተጠና አንድ የምርምር ስራ ተገኝቷል። ይህም መለስ እና ሌሎች "The Value of Virginity Related with sexual Behaviour and Associated Factors Among youth in Mekelle city, Northern Ethiopia" በሚል ርዕስ በመቐለ ከተማ ድንግልና በወጣቶች ዘንድ ስላለው ዋጋና ከሥነጾታዊ ባህርያት ጋር ባለው ግንኙነት ላይ ያተኮረ ጥናት አካሂደዋል (Yohannes, Tegabu, G/Slassie, & Gidey, 2016)። በተጨማሪም ደስታ (2006)፣ አዜብ (2006) እና ስንቅነሽ (2007) በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጹሁፍ ትምህርት ክፍል ባቀረቡት ጥናት ርዕሰ ጉዳያቸው ከእኔ ጥናት ጋር ባይመሳሰልም በትንታኔ ወቅት የኔን ርዕሰ ጉዳይ ዳሰዋል። ነገር ግን የነዚህ ጥናት አላማ ከዚህ ጥናት አላማ ጋር የማይመሳሰል በመሆኑ ርዕሰ ጉዳዩን ከማንሳት በዘለለ በሰፊው አልተዳሰሰም። እናም ከዚህ በመነሳት በኢሉ አባቦር ዞን በዶረኒ ወረዳ በኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ በነቀታ (Naqata) የጋብቻ አይነት ድንግልናቸውን ጠብቀው ለጋብቻ ለበቁ ሴቶች የሚደረገውን ባህላዊ የጋብቻ ሥርዓት፣ የሥርዓቱ ፋይዳ እና ለውጡ ምን እንደሚመስል ተዳስሶ ቀርቧል።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

ይህን ጥናት ለማድረግ አነሳሽ ምክንያቶች ሁለት ናቸው። አንደኛው የግል ሲሆን ሁለተኛው አካዳሚያዊ ምክንያት ነው።

አጥኝዋ ጥናቱ የሚካሄድበት ቦታ ተወልዳ ያደገች በመሆኗ ለድንግልና ይሰጥ የነበረውን ትልቅ ክብር ከልጅነቷ ጀምሮ በሠርግ ሥርዓቶች ላይ በሚከወኑ ክዋኔዎች እና በሚደረጉ ተግባሮች እያየች አድጋለች። ነገር ግን ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በተለያዩ አጋጣሚዎች ባደረገቻቸው ጭውውቶች ድንግልናን ጠብቆ ለትዳር መብቃት አሁን ላይ ዋጋ እንደሌለው መቆጠሩን፣ ሆኖም ግን በትዳር ላይ አዎንታዊ ተጽኖ እንደነበረው በመስማቷ ጉዳዩ ከጋብቻና ከሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች (ማህበራዊና ስነልቦናዊ) ጋር ያለውን ቁርኝት አንስታ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በማጥናት ለማሳየት ያላት ፍላጎት አነሳሽ ምክንያት ሆናት።

ቆየት ባሉት ጊዜ የዶረኒ ወረዳ በኦሮሞ ማህበረሰብ የሰርግ ሥርዓቶች ላይ ይከወኑ የነበሩ የተለያዩ ሥርዓተ ከበራዎች አሁን አሁን በተለያዩ ምክንያቶች እየከሰሙ፤ እንዲሁም ሙሉ በሙሉ እየጠፉ ይገኛሉ። አጥኚዋ ይህንን እንድትገነዘብ ያደረጋት በ 2010 ዓ.ም. በክረምት ወቅት ዘመዶቿን ለመጠየቅ ወደ ወረዳው በሄደችበት ወቅት የአንደኛ አመት ትምህርቷን አጠናቃ ስለነበር ለጥናት የሚሆናትን ርዕስ ለመወሰን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ጎራ በማለት

የተጠኑና ያልተጠኑ ፎክሎራዊ እሴቶችን ስትፈትሽ ለባህል ፌስቲቫል የተዘጋጀ መጽሄት እና የሠርግ ቪድዮ አግኝታለች። ሆኖም ግን ቪዲዮውም ሆነ መጽሄቱ  ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች ይደረግ የነበረው ሥርዓት ርዕሱን ከማንሳት ያለፈ ክወናው ሙሉ በሙሉ አልተዳሰሰም። በመሆኑም ለዚህ ሥርዓት ፎክሎራዊ ጥናት መደረግ አለበት የሚል እምነት ስላደረባት አነሳሽ ምክንያት ሆናት።

እንደሚታወቀው ዓለም በለውጥ ሂደት ውስጥ ነው። ከዚሁ በተጓዳኝ መልኩ ፎክሎር ራሱን የቻለ አካዳሚያዊ የትምህርት መስክ የሆነው ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ ሲሆን በሃገር ደረጃ ደግሞ ገና ዳዴ በማለት ላይ መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑ በሀገራችን የሚገኙ የብሄር ብሄረሰቦች ፎክሎራዊ እሴቶች በአብዛኛው አልተጠኑም። እነዚህ ፎክሎራዊ እሴቶች የተለያዩ ማህበረሰቦች ማህበራዊ ፍልስፍናቸውን የሚገልጹ ሥርዓቶች ሳይጠኑና ሳይቀረሱ በተለያዩ ምክንያቶች (በቴክኖሎጂ መስፋፋት፣ በምዕራባውያን የባህል ወረራ...) እየደበዘዙና እየጠፉ ቢሄዱ አብሮ የሚደበዝዘውና የሚጠፋው የማህበረሰቡ ታሪክ፣ ፍልስፍና አመለካከት በአጠቃላይ የማህበረሰቡ ማንነት ጭምር ነው። ከነዚህ በመጥፋት ላይ ካሉ ባህሎች ውስጥ በዶረኒ ወረዳ በነቀታ (Naqata) የጋብቻ ሥርዓት ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች  የሚደረገው ሥርዓት መሆኑን አጥኚዋ በመረዳቷ ለተተኪው ትውልድ መረጃውን ቀርሶ ማስቀመጥ ካላት ፍላጎት የመነጨ ሥርዓቱን ለመመርመር አነሳሽ ምክንያት ሆናት።

ሌላውኛው ምክንያት አጥኒዋ ያነሳችው ርዕስ በዶረኒ ወረዳ ብቻ ሳይሆን በሌሎች የኢትዮጵያ አካባቢዎች ከሚገኙ ባህሎች አንጻር ትኩረት ያልተሰጠው ጉዳይ መሆኑ ነው። በአካባቢው ይከውን የነበረው ሥርዓትም በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ (በቪዲዮ፣ በፎቶ፣ በድምጽ...) ተሰንዶ የማይገኝ በመሆኑ፣ የታሪክ ምንጭ የሆኑ የእድሜ ባለጸጎች እድሜያቸው እየገፋ፣ እየሞቱ በአዲስ ትውልድ በመተካቱ የነበረውን ሥርዓት ለማጥናት ትክክለኛውን መረጃ ማግኘት ከባድ የሚሆንበት አጋጣሚ ወደ ፊት ሊፈጠር ይችላል። በመሆኑም ከዚህ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶችን ለሚያጠኑ ባለሞያዎች  የመረጃ ምንጭ እንዲሆንና ባህላዊ እሴቱን ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ ከሚል አካዳሚያዊ ምክንያት ጥናቱን ለማካሄድ ይበልጥ አነሳሽ ምክንያት ሆናት።

## 1.3. የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በኢሉ አባቦር ዞን በዶረኒ ወረዳ በኦሮሞ ማህበረሰብ በነቀታ (Naqata) የጋብቻ አይነት ድንግልናቸው ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ባህላዊ ሥርዓትን መተንተን ሲሆን የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች አሉት።

### 1.3.1. ዝርዝር ዓላማዎች

- ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገውን ባህላዊ ሥርዓት ይመረምራል፤ እንዲሁም ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ላልጠበቁ ሴቶችም ያለውን ያከባበር ልዩነት ይዳስሳል።
- ማህበረሰቡ ለልጃገረዶች ከሚሰጠው ነጻነት አንጻር ልጃገረዶች ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለመብቃት የሚገጥማቸውን ፈተና ይፈትሻል።
- ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ባህዊ ሥርዓት ለማህበረሰቡ ያለውን ፋይዳ ይዳስሳል።
- በሥርዓቱ የሚታየውን የለውጥ ሁኔታ ከማህበሰቡ አተያይ አንጻር ማቅረብ እና ለለውጡ በምክንያትት የሚነሱትን ጉዳዮች ይመረምራል።
- የባህላዊ ሥርዓቱን በጽሁፍ ሰንዶ ያስቀምጣል።

## 1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

የጥናቱ ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል።

- በነቀታ (Naqata) የጋብቻ አይነት ድንግልናቸውን ጠብቀው ለጋብቻ ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት ምን ይመስላል? ድንግልናቸውን ጠብቀው ለጋብቻ ላልበቁትስ?
- ማህበረሰቡ ለልጃገረዶች ከሚሰጠው ነጻነት አንጻር ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለመብቃት የሚገጥማቸው ፈተና ምንድን ነው?
- ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርአት ፋይዳው ምንድ ነው?
- ሥርዓቱ ላይ በጊዜ ሂደት የመጣው ለውጥ ምንድን ነው? ለለውጡ በምክንያትነት የሚነሱ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? የሚሉት ናቸው።

## 1.5.የጥናቱ ጠቀሜታ

በኢሉ አባቦር ዞን በዶረኒ ወረዳ በኦሮሞ ማህበረሰብ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት ላይ ጥናት መደረጉ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታመናል።

❖ ይህንን ሥርዓት ትኩረት ለማይሰጡ የማህበረሰቡ አባላት ፋይዳውን ተገንዝበው ሥርዓተ ክወናውን በውል እንዲያጤኑት መነሳሳትን ሊፈጥር ይችላል፡፡

❖ ወደ ፊት በወረዳው የሚገኙ ሌሎች የጋብቻ አይነቶችን በንጽጽር ለማጥናት ለሚፈልግ በመረጃ ምንጭነት ሊያገለግል ይችላል።

❖ በአንድ ወቅት ይከወን የነበረ ባህል በአንዳች ምክንያት በተወሰነ መልኩ ወይም ሙሉ በሙሉ ሊቀየር ወይም ሊጠፋ ይችላል። በመሆኑም በዶረኒ ወረዳ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓተ ክወና፤ በተለያዩ ምክንያቶች ጨርሶወኑ የመጥፋት አደጋ ገጥሞታል። ስለዚህ ይህ ጥናት መደረጉ የማህበረሰቡ ወግና ልማድ፣ ቱባ ባህሉና ቅርሱን ጠንቅቀው የሚያውቁ የባህሉ ባለቤቶች በእድሜ መግፋት ምክንያት ከማለፋቸው በፊት መረጃዉን በመሰነድ ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላልፍ ያስችላል።

❖ ማንኛውም አካል በጥናቱ አካባይ ዉስጥ ከሚገኘዉ ከአከባቢው ህብረተሰብ ጋር ወይይት ማድረግ ቢፈልግ በተወሰነ መልኩ የህብረተሰቡን ማንነት እና ስነልቦናዊ አመለካከት ተረድቶ፤ የመፍትሔ ሀሳቦቹን እንደመመሪያዉ በማስቀደም መመሪያዎቹን ጥናቱ ከሚጠቁመው የማህበረሰቡ እምነት እና አመለካከት አንፃር እንዲያደራጁ የተወሰነ መረጃ ይሰጣል።

❖ ከባህሉ ውጭ የሆነ ወይም የአካባቢውን ባህል ለማያውቅ ሰው ይህንን ጥናት እድል ገጥሞት ቢያነበው ጥናቱ በሀገር ደረጃ የባህል ልውውጥ እንዲኖር የማድረግ እድል ይፈጥራል።

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ለአንድ ጥናት ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ወጪ እና ጊዜን ከግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነው። ይህ ክፍል የጥናቱን ስፋት ምን ምን ጉዳዮችን እንደሚዳስስ የሚገልጽ ክፍል ነው።

በኢሉአባቦር ዞን በዶረኒ ወረዳ በኦሮሞ ማህበረሰብ የተለያዩ የጋብቻ አይነቶች አሉ። ለምሳሌ አሴና (Aseenna)፣ ነቂ (Naqii)፣ ቡቲ (Butii)፣ ነቀታ (Naqata) ወዘተ. የሚጠቀሱ ናቸው። እያንዳንዱ የጋብቻ አይነት የተለየ የአከናዋን ሥርዓት አለው። በዚህ ጥናት ትኩረት የሚደረገው በነቀታ (Naqata) የጋብቻ አይነት በሚከናወነው ድንግልናቸውን ጠብቀው ለጋብቻ ለበቁ ሴቶች የሚደረገውን ሥርዓት፣ አሁን ያለበት ሁኔታ እና ለማህበረሰቡ የነበረውን ፋይዳ ማሳየት ነው።

በሌላ በኩል በወረዳው ከሚገኙ አስራ ሁለት ቀበሌዎች መካከል ጥናቱ ያተኮረው በአራት ቀበሌዎች (ኤሌሞ፣ ፋኒ፣ ወይራና ቦሬጫ) ላይ ብቻ ነው። ምክንያቱም አጥኝዋ በአራቱ ቀበሌዎች ባህሉ በሰፊው ይከወን እንደነበር ስለምታውቅ እና በተጨማሪም በነዚህ ቀበሌዎች መረጃ ሊሰጧት የሚችሉ ሰዎችን እንደምታገኝ እርግጠኛ ስለሆነች ነው። ድንግልናን ጠብቆ ለትዳር መብቃት በሁሉንም የአካባቢው ማህበረሰብ ክብር የሚሰጠው እና የተለያየ የአከባበር ሁኔታም አለው። ይሁን እንጂ ይህ ጥናት በወረዳው የሚኖሩ የሌሎችን ብሄረሰቦች አከባበር ሥርዓትም ሆነ አመለካከት እንዲሁም በቦታ ወይም በአካባቢ ልዩነት በኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ የሚታየውን ወይም ሊመጡ የሚችሉትን የክወና ልዩነት አያንጸባርቅም።

## 1.7. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች

አጥኝዋ በመስክ ቆይታዋ ያጋጠሟት ችግሮች ቀላል የሚባሉ አይደሉም። ከነዚህ መካከል በመጀመሪያ ደረጃ የሚጠቀሰው ጥናቱ ከድንግልና ጉዳይ ጋር የተያያዘና ወሲብ ነክም ጭምር በመሆኑ፤ በመረጃዎች አሰባሰብ ወቅት በተለይ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ተኮር ውይይት ላይ መረጃ  አቀባዮች መረጃ ከመስጠት መቆጠብ (ማፈር) ነበረ። ቢሆንም የጥናቱ ዓላማ የግለሰቦችን ታሪክ ለመጻፍ ሳይሆን የነበረውን ሥርዓተ ከበራ እንዴት እንደ ነበር፣ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ፋይዳ እና አሁን ያለበትን ሁኔታ ለማጥናት ብቻ ትኩረት የሚያደርግ መሆኑን አጥኚዋ በመግለጽ እንዲሁም  አጥኚዋ  ሴት በመሆኗ በተለይ ሴቶችን በቅርበት (እንደእናት) በማናገር  በቂ መረጃ ልትሰበስብ ችላለች። ከዚህ አንጻር የምርምሩ ዓላማ ከግብ እንዳይደርስ እንቅፋት የሚሆኑ የጎሉ ችግሮች አልተፈጠሩም።

በሁለተኛ ደረጃ የሚነሳው አጥኝዋን ያጋጠማት ችግር ለጥናቱ የተመረጠው ወረዳ አጥኝዋ አሁን ከምትኖርበት አካባቢ በጣም ሩቅ ከመሆኑም በላይ የመንገዱ ሁኔታ ተቆራራጭ እና መደበኛ ትራንስፖርት የማይገኝበት በመሆኑ ተመላልሶ መረጃ ለመሰባሰብ በጣም አስቸጋሪ ነበር። ይሁን እንጂ ወደ ቦታው ለመሄድ ብዙ ቀናትን በመመደብና መደበኛ ያልሆኑ ትራንስፖርቶችን በመጠቀም መረጃውን መሰብሰብ ተችሏል። በተጨማሪም ከወረዳው ከተመረጡት አራት ቀበሌዎች ሶስቱ (ፋኒ፣ ወይራና ቦጮ) ከዋናው መንገድ በጣም የራቁና ወደ ቀበሌዎቹ የሚወስዱ መንገዶች መኪና የማይገባባቸው መሆናቸው ነው። እነዚህ መንገዶች  ረጅም የእግር ጉዞ ልምድ የሚጠይቁና ተስፋ የሚያስቆርጡ ነበሩ። ይህንም የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሰራተኞች ባደረጉላት ትብብር በሞተር ወደቀበሌዎቹ በመጓዝ መረጃዎችን መሰብሰብ ችላለች።

በሶስተኛ ደረጃ አጥኝዋን ያጋጠማት ችግር አንዳንድ መረጃ አቀባዮች መረጃውን ለመስጠት ፈቃደኛ ሆነው የራሳቸውን የህይወት ተሞክሮ በሚገባ ሊነግሯት ፈቃደኛ ከሆኑ በኋላ ድምጻቸው በቴፕ መቀዳትን ፍቃደኛ ይሆኑና በቪዲዮ ካሜራ እንዳይቀረጽ መከልከላቸውና ፎቶ ግራፍ አንነሳም ማለታቸው ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ መረጃውን ለመስጠት ፍቃደኛ ቢሆኑም ማንኛውንም  ድምጽ፣ ፎቶ እንዲሁም ቪድዮ ለመቀረጽ ፍቃደኛ አለመሆናቸው ነው። ይህን ችግር ለመፈታት መረጃው ሲሰበሰብ በድምጽ ለመቀረስ ፍቃደኛ የሆኑትን በድምጽ ምንም ፍቃደኛ ያልሆኑትን መረጃቸው እስከጠቀመ ድረስ በማለት  በማስታወሻ ደብተር በመጻፍ መረጃውን መውሰድ ተችሏል።

## 1.8. የመስክ ተሞክሮ

አጥኝዋ ለጥናት የመረጠችው አካባባቢ ተወልዳ ያደገችበት በመሆኑ ወደ መስክ ከመውጣቷ በፊት ምን ማድረግና የት የት መሄድ እንዳለባት በሀሳብ አካባቢውን ቃኝታለች። አካባቢውን ስትቃኝ በልጅነቷ በአካባቢው ስትጫወትባቸው የነበሩ የመጫዎቻ ስፍራዎች፣ የተማረችባቸው ትምህርት ቤቶች፣ ከወንዝ ውሃ የቀዳችባቸው ምንጮች ሁሉንም በሀሳብ ስትዳስስ ተረት እና እንቆቅልሽ እየነገሩ ያሳደጓት ሰዎችም አብረው ይታዎሷት ነበር። በዚህ ጊዜ ይህንን የመረጠችውን ርዕሰ ጉዳይ ጠንቅቀው ያውቃሉ ብላ ያሰበቻቸውን ሰዎች ሀሳቧን ገታ ታደርግና ታስባለች። በዚህ ጊዜ አጥኚዋ ትልመ ጥናቷን ባለማቅረቧ በአካል

አልተንቀሳቀሰችም ነበር። ነገር ግን “ድንግልናን” በተመለከተ የተጻፉ ማንኛውንም ጥናታዊ ጽሁፎች፣ መጽሀፍት እንዲሁም ቪድዮች በማየት ቅድመ ዝግጅት ታደርግ ነበር።

መጋቢት መጀመሪያዎቹ አካባቢ ትልመ ጥናቷን አቅርባ የተሰጧትን ማስተካከያዎች በማረም ለዩኒቨርሲቲው እንዳስገባች ወደ ኢሉ አባቦር ዞን ዶረኒ ወረዳ በመጓዝ መረጃ ለማሰባሰብ በ14/07/2011 ዓ.ም ቅድመ ሁኔታዎችን ያጠናቀቀች ቢሆንም በዕለቱ ቤተሰባዊ ችግር ስለገጠማት ጉዞዋን ሰርዛለች። ይሁን እንጂ አጥኚዋ በወቅቱ የሰባት ወር ነፍሰ ጡር ስለነበረች በዚህ ምክንያት ተዳክማ ወደ ኋላ መቅረት እንደሌለባት እራሷን በማሳመኗ ምንም አይነት ድካም አይሰማትም ነበር። ነገር ግን ይህንን ብትቋቋምም የገጠማትን ሌላ ችግር በፍጥነት መፈታት ባለመቻሏ እቅዷን ከግብ ማድረስ አልቻለችም። በመሆኑም አጥኝዋ በቆራጥነት መንፈስ ሴትነት፣ ማርገዝ እና መውለድ ጸጋ እንጂ መሰናክል ሊሆን አይገባም በሚል ለቃለ መጠይቅና ለቡድን ተኮር ውይይት መነሻ የሚሆኑ ጥያቄዎችን በማሰናዳትና ቪዲዮ ካሜር፣ የፎቶ ካሜራና ማስታወሻ ደብተር አዘጋጅታ ሰኔ 30፣ 2011 ዓ.ም በወለደች በአስራ አምስተኛ ቀን ስምንት ስዓት ላይ ዶረኒ ወረዳ ደረሰች። ጊዜው ክረምት ከመሆኑም በላይ ወደ ወረዳው የሚወስደው መንገዱ ኮረኮንች በመሆኑና መደበኛ ትራንስፖርት የማይገኝለት መሆኑ አጥኚዋ ከነበረችበት ሁኔታ ጋር ተደምሮ ጉዞውን ፈታኝ አድርጎት ነበር። ይሁን እንጂ አጥኚዋ ካነገበችው አላማ አንጻር ድካሟን ድካም በማድረግ ለሁለት ሰዓታት በቤተሰቦቿ ቤት እረፍት ካደረገች በኋላ አስራ አንድ ስዓት ላይ ወደ ዶረኒ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ስታመራ ስዓቱ የሰራተኞች የስራ ስዓት መውጫ በመሆኑ ሰራቶኞቹ በአብዛናው ከስራ እየወጡ በር ላይ አገኘቻቸው። ሰራቶኞቹን በአብዛኛው የምታውቃቸው በመሆናቸው የናፍቆት ሰላምታ ተለዋወጡ። ከዚያም የባህልና ቱሪዝም ሰራተኛ ለሆኑት አቶ ሞገስ ከበደ ርዕሰ ጉዳዩን ቀድማ በስልክ ነግራቸው ነበር። በአካል ሲገናኙ ደግሞ ከመስሪያ ቤታቸው እስከ ቤተሰቦቿ ቤት ድረስ በእግር እየተጓዙ ሳለ አላማውንና አጠቃላይ ለመስራት ያሰበቻቸውን ጉዳዮች አብራርታ አስረዳቻቸው። እሳቸውም በስራ ምክንያት በወረዳው ውስጥ በሚገኙት ቀበሌዎች ባደረጉት እንቅስቃሴ በተለያዩ ሰርጎች ላይ በመገኘት ባደረጉት ምልከታ ድንግልናን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች ይደረግ የነበረው ሥርዓት በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ እንደቀረ ነገሯት። ነገር ግን በሥርዓቱ ጋብቻቸውን የፈጸሙ በርካታ የባህሉ ባለቤት የሆኑ የሀገር ሽማግሌዎችን ማግኘት እንደምትችል በርግጠኝነት ገለጹላት። አያይዘውም ወደ ምትፈልጋቸው ቀበሌዎች

አብረዋት በመጓዝ ሊረዷት እንደሚችሉና ለጥናቷ ይጠቅማት ዘንድ ያሉትን ቪዲዮችና መጽሄት እንደሚሰጧትም ተነጋግረው ተለያዩ።

ቃል በገቡት መሰረት በማግስቱ ጠዋት ስራ እንደገቡ ቪዲዮዎችና መጽሄት መውሰድ እንደምትችል ስልክ በመደወል ነገሯት። አጥኚዋም ጊዜዋን ላለማባከን ስትልና መስራቤታቸውም ከቤተሰቦቿ ቤት ቅርብ በመሆኑ ስልክ በደወሉላት አስር ደቂቃ ልዩነት መስሪያ ቤት በመሄድ ያዘጋጁላትን ቪዲዩና መጽሄት ወሰደች። በዕለቱ መጽሄቱን ስታነብ በመዋሏ ተጨማሪ መረጃ ለማደራጀት እንድትችል አስችሏታል። አጥኚዋ በቀጣዩ ቀን ከአቶ ሞገስ ከበደ ጋር በመሆን ወደ አቶ ታደስ ሁንዴ ቤት አቀናች። ሁለት ሆነው አቶ ታደሰ ሁንዴ ቤት እንደ ደረሱ አቶ ሞገስ "ቤቶች እንደምን ሰነበታችሁ?" ሲሉ አቶ ታደሰ ሁንዴ ትንሽ አይናቸውን ስለጋረዳቸው ብዙም ከቤት ወተው ወዲያ ወዲህ ለማለት የሚያስችላቸው ሁኔታ ላይ አይደሉም። ነገር ግን ከአቶ ሞገስ ጋር ከዚህ በፊት ባህል ነክ ስራዎችን አብረው ሰርተው ስለነበር ገና የአቶ ሞገስን ድምጽ እንደሰሙ ስላወቋቸው ከመቀመጫቸው በመነሳት፤ ጋቢያቸውን እያጣጣሉ ፈገግ በማለት "እንደምነህ ልጄ ምን እግር ጣለህ?" በማለት በደስታ ለሁለቱም ሰላምታ አቀረቡላቸው። "ቁጭ በሉ" በማለት የመቀመጫዎቹን አቅጣጫ በእጃቸው አመለከቷቸው። አጥኚዋም ከተቀመጠች በኋላ ማን እንደሆነች፣ ለምን እነደመጣች፣ የስራዋን አላማ አስረዳቻቸው እሳቸውም "ባህል ለማጥናት" የሚለውን በመስማታቸው በእጅጉ ተደሰቱ። በዚህ መሀል ባለቤታቸው ወ/ሮ አባይነሽ መርጋ ከወደ ጓደ መጡና ትህትና የተሞላው ሰላምታቸውን አቀረቡ። አጥኚዋም ከመቀማጫዋ በመነሳት ወ/ሮ አባይነሽ መርጋ ጋር ሰላምታ ከተለዋወጠች በኋላ ፍቃደኝነታቸውን በመጠየቅ እሳቸውንም እንደምትፈልጋቸው በመንገር አብረው እንዲቀመጡ ሆነ። ከዚያም አቶ ታደሰ ሁንዴ ከባለቤታቸው ወ/ሮ አባይነሽ መርጋ ጋር በመሆን ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች ይደረግ የነበረውን ሥርዓት ከራሳቸው የህይወት ተሞክሮ ጋር በማዋዛት አንዳንዴ አሁን ያለውን ሁኔታ ያስቡና በስጨት በማለት "እናንተ የዚህ ትውልድ ሆናችሁ ስለባህል በማንሳታችሁ ፈጣሪ ይስጣችሁ" እያሉ ይመርቃሉ ። አንዳንዴ ደግሞ የነበረውን ሁኔታ በሚያስገርም የአገላለጽ ስልት በግልጽ ሲተርኩ አጥኚዋንም ሆነ አብረዋር የነበሩትን በማዝናናት ነበር። አቶ ታደሰ ሁንዴ ትልቅ የታሪክ መጽሀፍ ናቸው። ታሪክ ከማወቃቸውም በላይ በአገላለጽ ክህሎትም ጭምር የታደሉ ናቸው። አጥኚዋ ከሳቸው ጋር በነበራት ቆይታ ደስታም ሀዘንም ይሰማት ነበር። ደስታዋ እንዲህ አይነት የእድሜ ባለጸጋን አግኝታ የምትፈልገው መረጃ በሚገባ በማስራጃ

እያጣቀሱ ስለተረኩላት እድለኝነት ተሰምቷት ሲሆን ሀዘኗ ደግሞ እኝህ ታሪክ አዋቂ ሰው የያዙትን መረጃ ለትውልድ የሚያስተላልፉበት መንገድ ተበጅቶላቸው ይሆን? በሚል ስጋት ነው። በአጠቃላይ አጥኚዋ ከአቶ ታደሰና ከባለቤታቸው ወ/ሮ አባይነሽ መርጋ ቤት ቡና ተፈልቶላት፣ በቅቤ  የተቀባ ቂጣ ተመግባ በነበረት ቆይታ በእጅጉ ተደስታ በተጨማሪም በዚህ ሥርዓት ጋብቻቸውን የፈጸሙ ሌሎች መረጃ አቀባዮችን ጠቁመዋት በምስጋና ተሰነባበቱ። ታድያ በእለቱ ከእሳቸው ጋር በነበራት ቆይታ 7፡30 የተጀመረው ቃለ መጠይቅ ሳይታወቅ መሽቶ ነበርና11፡30 ስዓት ተጠናቆ ለአዳር ወደ ቤተሰቦቿ ቤት ተመለሰች።

በመሆኑም አቶ ታደሰ ሁንዴ በጠቆሟት መሰረት ኤሌሞ ቀበሌ ያሉትን መረጃዎች ሰብስባለች። ነገር ግን አብዛኞቹ መረጃ አቀባች በሰርጋቸው ወቅት የነበረውን ሁኔታ ከተረኩላት በኋላ ስለወረዳው አካባቢያዊ ዳራም ሆነ የተያዩ መረጃዎችን ለማግኘት የተሻለ እወቀት ያላቸው አቶ ታደሰ እንደሆኑ ጠቁመዋታል። አጥኚዋ በየቀበሌዎቹ ተዘዋዉራ መረጃ ስትሰበስብ በርካታ ታሪክ አዋቂዎች የእድሜ ባለጸጎች ገጥመዋታል። ሁሉም መረጃ አቀባዮች መረጃ ያቀበሏት በደስታና በመልካም መስተንግዶ ነበር። በተጨማሪም በሁሉም ቀበሌዎች የተመረጡ መረጃ አቀባዮችም ሆኑ በጥቆማ የተገኙ መረጃ አቀባዮች በሰርጋቸው ወቅት የነበረውን  ሁኔታና የትዳር ተሞክሯቸውን መረጃ ከሰጡ በኋላ ሌሎችን መረጃ አቀባዮችን በመጠቆም ከፍተኛ ትብብር አድርገዋል። አጥኚዋም መረጃዎቿ በትክክል መጠናቀራቸውን ካረጋገጠች በኋላ ነሐሴ 15፣ 2011 ዓ.ም ወደ ጅማ ተመልሳላች፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# 2. ክለሳ ድርሳናት

ይህ ክፍል ስሶት መሰረታዊ ጉዳዮች የተካተቱበት ክፍል ነዉ፡፡ በዚህ ርዕስ ሥር በቀዳሚነት የቀረበዉ በተለያዩ ምሁራን የተነደፈዉ ንድፈ ሀሳብ ነዉ፡፡ በመቀጠልም ከዚህ ጥናታዊ ሥራ ጋር ተዛማጅነት ያላቸዉና በታለያየ ጊዜ የተሠሩ ተዛማጅ ጥናቶች ተተንትነዋል፡፡ በመጨረሻም ጥናቱ የሚካሄድበት የዶረኒ ወረዳ አካባቢ ዳራዊ መግለጫም ከዚሁ ጋር ተያይዞ ቀርቧል፡፡

## 2.1. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

አንድን የፎክሎር ዘርፍ ለማጥናት በቅድሚያ ለፎክሎር ዘርፉ ተስማሚ የሆኑትን የንድፈ ሃሳብ ዓይነቶች ለይቶ ማወቅና ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ነው። በመሆኑም በዚህ ንኡስ ርዕስ የባህልን ጽንሰ ሀሳብ፣ የፎክሎር ጥናት ቅኝት፣ ልማድ፣ ጋብቻ በሰው ልጅ ህይወት፣ የድንግልና ምንነት፣ ድንግልና ከጋብቻ አንጻር እንዲሁም ድንግልናን ጠብቆ ለጋብቻ በመብቃት ዙሪያ የሚነሱ አጠቃላይ ሁኔታዎች ከጥናቱ አላማ ጋር በማገናኘት እንደሚከተው ለመዳሰስ ተሞክሯል።

### 2.1.1. የባህል ጽንሰ ሀሳብ

የስነ-ሰብ የትምህርት ዘርፍ ተመራማሪ የሆነው እንግሊዛዊው Tylor እ.ኤ.አ በ1871 ለቃሉ በሰጠው ፍቺ ባህል ማለት ሰው እንደ አንድ የህብረተሰብ አባልነቱ የሚቀስማቸውና የሚያዳብራቸው ልማዶችና ወጎች ሲሆኑ እንደ እምነት፣ እውቀት፣ ጥበብ፣ መስተጋብር፣ እሴቶች፣ ማህበራዊ ህግጋት፣ ወጎች፣ ቋንቋ፣ የጋብቻ፣ ሃዘንና የለቅሶ ሥርዓቶች፣ የአመራረትና አመጋገብ ልማድ፣ የሃይማኖትና ኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲሁም አጠቃላይ የኑሮ ዘይቤን አጠቃሎ የያዘ የአንድ ማህበረሰብ ወይም ህብረተሰብ መገለጫ ነው። ባህል ሰፊና ውስብስብ የሰው ልጅ ከሚኖርበት ማህበረሰብ የሚያገኘው ወይም የሚለምደው እውቀት ነው። በመሆኑም ባህል እምነት፣ ስነጥበብ፣ ስነምግባር፣ ህግና ደንቦች እንዲሁም ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ፣ ኑሮውን በመምራት የሚገለገልባቸውን ቋንቋዎች፣ ወኪሎች፣ የስነምግባር እሴቶችን የሚያጠቃልል ነው። ስለሆነም ባህል ከህብረተሰቡ ጋር ብቻ ተቆራኝቶ የሚገኝ እንጅ ከህብረሰቡ ውጭ ለብቻው የራሱን ህልውና ጠብቆ መኖር የሚችል አይደለም (Tylor, 1871)።

እንዲሁም ሌሎች ተመራማሪዎችም ባህልን ሲገልጹ ከታይለር ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው ትርጉም ሰጥተዉት እናገኛለን። ለምሳሌ Jervis ባህል የሰው ልጅ የማንነቱ መገለጫና ከዓለም ጋር ያለውን መስተጋብር የሚያመለክቱ መንፈሣዊ፣ ቁሳዊ፣ አዕምሮዓዊ፣ ጥበባዊና ገቢራዊ እሴቶች ስብስብ፤ የእርስ በእርስ ግንኙነቶች፣ ዕምነቶች፣ ልማዶችና ባህሪዎች ውስብስብ እንቅስቃሴና ፍቺ ነው።” ሲል፤ አያይዞም “ባህል ከበርካታ ሁኔታዎች ጋር የሚያስተሳስር ፍቺ አለው። ባህል ማለት የአንድ ህብረተሰብ አባላት የሚረከቧቸውን የተጠራቀሙ ዕውቀቶች፣ ዕምነቶች፣ ኪነ-ጥበባት፣ መመሪያዎች፣ አርማዎች፣ አመለካከቶች፣ ስነ-ምግባራት፣ ህግጋት፣ ወጎች፣ ተለምዶዎችና ሰዎቹ የሚገለገሉባቸውን ቁሳዊ ንብረቶችን ጭምር የሚያጠቃልል ውህድ ነው።” በማለት ያብራራል (Jervis ፣2011) ።

የራስወርቅ (2004) “ባህል ለልማት በኢትዮጵያ» በተሰኘው መጽሀፍ ደግሞ ባህል ስልጣኔን፣ እውቀትን፣ እምነትን ስነ-ጥበብን፣ ሞራልን፣ ህግን፣ ወግና ልማድን እንዲሁም ሌሎች ሰው የማህበረሰብ አባል በመሆኑ ምክናያት የቀሰማቸውን ክህሎቶችና ጥናቶችን ጭምር የሚያጠቃልል ውሁድ ነው....ባህል ከአካባቢያችንና ከሌሎች ሰዎች ጋር ያሉንን ግንኙነቶች በተመለከተ የሚመራን የአእምሮ ወይም የህሊና ካርታ ነው በማለት ገልጸውታል።

ከለይ ከተገለጹት ትንታኔዎች እንደምንረዳው የሰው ልጅ አብዛኛውን እውቀቱን የሚያገኘው ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣ ባህል ነው። ለዚህም ነው በተለያየ አካባቢ በሚኖሩ ሰዎች መካከል የሀሳብ ልዩነት የሚፈጠረው ወይም የሚኖረው። በአጠቃላይ አለባበሳችን፣ አመጋገባችን፣ አወራራችን፣ አስተሳሰባችንን ወዘተ የምንወርሰው በአብዛኛው ከባህላችን መሆኑን ነው።

የሰው ልጅ ባህልን ልክ እንደ እምነት እና ዕወቀት የሚያጋጥሙትን ችግሮች የመፍቻ መሳሪያ አድርጎ ሲገለገልበት ከቆየ ረዥም ዘመናትን አስቆጥሯል። የሰው ልጅ ለዘመናት የአያቱንና የቅድመ አያቱን ባህል፣ አመለካከታቸውን፣ አለባበሳቸውን፣ አመጋገባቸውን፣ አነጋገራቸውን፣ እምነታቸውን ሲቀበል እንደ ነበር ይታወሳል።

### 2.1.2. የፎክሎር ጥናት ቅኝት

ፎክሎር የሚለው ቃልም "ፎልክ" ና "ሎር" የሚሉ የሁለት ጽንሰ ሃሳባዊ ቃላት ውህድ ነው (Schoemaker ፣1990) ። ህዝባዊ የሚለው ቃል ቡድናዊ የሆኑ ሰዎችን የያዘ አካል ሲሆን ልማድ ደግሞ በባህል ክፍል ውስጥ የሚመደብ ነው። የሰው ልጅ ማህበራዊ በመሆኑ እንደ ሰው ልጅነታችን ሁላችንም በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ተሳታፊዎች እንደሆን፤ ከዚህም የተነሳ አንዱ ከአንዱ ጋር መግባባትና ግንኙነት መፍጠር እንደሚችል ተጽፏል። እንዲሁም ፎክሎር የሚለው ቃል ማንኛውንም የሕዝብ ቡድን የሚመለከት ሆኖ ቢያንስ አንድ በጋራ የሚያገናኛቸው ጉዳይ ትምህርት፣ ሥራ፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣...ወዘተ ሊሆን ይችላል (Dundes፣1990) ። ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ፎክሎር ማለት ጥበባዊ ተግባቦት ያላቸው የኅብረተሰብ ቡድን መሆኑንና በቡድኑ አባላት መካከል ያለው ግንኙነት ሰዎቹ የሚናገሩትን፣ የሚያደርጉትን፣ የሚሠሩትን ...ወዘተ ጉዳዮች የተመለከተ ነው (Ben Amos፣ 1971) ።

የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) እኤአ 2010 "Basic Texts of the 2003 Convention for the Safeguarding of the Intangible Cultural Heritage" በማለት አንድ ሰነድ አውጥቷል። በሰነዱ ውስጥ "Intangible Cultural Heritage" ተብሎ የቀረበው የፎክሎርን ጽንሰ ሀሳብ የያዘ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ የኢትዮጵያ የቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/92 የፎክሎርን ጽንሰ ሀሳብ ግዙፍነት ከሌላው የሰው ልጅ እውቀት አንጻር ይመለከተዋል። ግዙፍነት የሌለው ቅርስ ማለት በእጅ ለመዳሰስ የሚያዳግት ነገር ግን በዓይን ለማየት፣ በጆሮ ለመስማት የሚቻል ቅርስ ሲሆን የብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ልዩ ልዩ ትርዒትና ጨዋታ፣ ሥነ ቃል፣ የሃይማኖት፣ የእምነት፣ የጋብቻ፣ የሐዘን ሥነ-ሥርዓት፣ ሙዚቃ፣ ድራማና ሌሎች ተመሳሳይ ባህላዊ እሴቶች፣ ወግና ልማድን ይጨምራል በማለት ይተረጉመዋል። በዚህ ትርጉም መሠረት "ኢንታንጅብል" ባህላዊ ቅርስ የማይዳሰስ የሰው ልጅ ማህበራዊና ባህላዊ ክዋኔ ውጤት መሆኑን እንረዳለን።

ፎክሎር አንድ ሕዝብ በማህበራዊና ባህላዊ ሕይወቱ ውስጥ ማሕበረሰቡ የሚገኝበትን ሁኔታ በማንጸባረቁ ረገድ የተለየ ሚና እንዳለው በርካታ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከእነዚህም መረጃዎች ውስጥ ፎክሎር ያለፈውን የሚያወሳ ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ የእውቀት ምንጭ

በመሆኑ በዕለታዊ የሰው ልጅ እንቅስቃሴ ውስጥ ወቅታዊ የትኩረት ጉዳዮችን በማሳየት ባህላዊና ሥነልቦናዊ ጠቀሜታዎች ያሉት በመሆኑ በጭንቀት ምክንያት ድብቅ የሆኑ ጉዳዮችን ሳይቀር ይፋ የማድረግ አቅም እንዳለው በፎክሎር ትንተናው ላይ ያብራራል (Dundes፣1965)። ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ድብቅ ከሆኑት ጉዳዮች ውስጥ ዋናው ከወሲብ ጋር የተያያዙ ተግባራት ሲሆኑ ይህንንም አንድ ግለሰብ የሚማረው ከማህበረሰቡ መሆኑንና ለዚህም የቋንቋ ሚና ከፍተኛ መሆኑን Rosenthal እና Moore (2006)ይገልጻሉ። ስለዚህ፤ ከዚህ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር የአጥኚዋ ተነሳሽነትም መሠረት የሚያደርገዉ፤ እስካሁን ያልተሰነደዉን የዶረኒ ኦሮሞ ማህበረሰብ ፊጥሮ ለዘመናት የተገለገለበትን የማይዳሰስ ባህላዊ ቅርስ፣ በቋንቋ አማካኝነት ለመመርመር፣ ለማሳየት እና ሰንዶ ለማስቀመጥ ያለመ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

### 2.1.3. ልማድ

ልማድ በፎክሎር ጥናት ውስጥ መሰረታዊ ፅንሰ ሀሳብ ነው። ይህን መሰረታዊ ፅንሰ ሃሳብ በመተርጎም ሂደት በርካታ የፎክሎር ባለሙያዎች የተለያዩ ብያኔዎችን ሰጥተዋል። ለምሳሌ Hield (2007) Glassie (1995) ጠቅሰው "የአንድ ቡድን መለያ ሆኖ ተጠብቆ በኖረ ተግባራዊ ልምምድ ውስጥ በሚካሄድ የተስተላልፎ ሂደት ካለ ዘላቂነት ጋር የሚያያዝ ፅንሰ ሀሳብ ነው" ይላሉ። እንደሁም Green(1997) "ልማድ የአንድ ነገር ከአንድ ትውልድ ወደሌላው በጥቂት ለውጥ አለዚያም ያለምንም ለውጥ ኢመደበኛ በሆነ መንገድ የሚተላለፍ ነው" ብሏል። ከዚህ በመነሳት ልማድ፣ በፎክሎር ሙያ ውስጥ ዋና ፅንሰ ሀሳብ የሆነ፣ ከጊዜ ጋር ተያያዥ የሆኑ ሃሳቦችን የሚይዝ፣ በኢመደበኛ ትምህርት የሚገኝና ከተከታታይነትና ለውጥ ጋር የሚያያዝ ፅንሰ ሃሳብ ነው ማለት ይቻላል። ፅንሰ ሀሳቡ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይም፣ በአንድ ቡድን ውስጥ የሚገኙ የባህል ጉዳዮችን መቀባበል ነው ተብሎ ሊገለፅ ይችላል። ይሁንና ከዚህ በተሻለ መልኩ ልማድ ግልፅ ብያኔ ሊያገኝ እንደሚችል የሚጠቁሙት Smith እና Shaffer (2013) "ልማድ የምንቀባበለው ዕውቀትና የዕውቀቱን የምንቀባበልበት ሂደት ነው" እና "ማንነትን የሚፈጥርና የሚተክል ነገር ነው" ሲሉ ይበይኑታል። ብያኔዎችን ሲያብራሩም ልማድ፣ አንድ ቡድን ያለው ሀገር በቀል ዕውቀትና ዕውቀቱን የሚቀባበልበት ሂደት ነው። ቃሉ የማንኛውም ድግግሞሽን የሚፈጥር ሂደት መገለጫ እስከመሆን ይደርሳል። ለምሳሌ ታሪክ፣ ታሪክ የሚነገርበት እንቅስቃሴ ታሪኩ ወይም ታሪክ ነገራው ትርጉም የሚያገኝበት መንገድ፣ እነዚህ ሁሉ ልማድ ይሆናሉ። ከዚህ

በተጨማሪ ፅንሰሃሳቡ በተወሰነ ቡድን ውስጥ ያሉና የሚቀጥሉ ቁሶችን፣ ልማዶችን፣ ቃላዊ ገለፃዎች መቀባበልንና ተከታታይነትን (continuity) ይመለከታል። በዚህ ጥቅስ Smith እና Shaffer (2013) ልማድ፣ አንድ ቡድን ያለውን ሀገር በቀል ዕውቀትና ዕውቀቱን ያገኘበት ኢመደበኛ መንገድ ነው የሚል ሃሳብ የሰጡ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ልማድ፣ ቡድኑ ባለው ዕውቀት ማንነቱን ለመገንባትና ለማጠናከር የሚያገለግለው ጉዳይ እንደሆነ፣ ቡድኖች ልማድን የሚተገብሩት መርጠው በመውሰድ ነው። ይህ በመሆኑ ልምዱ የማንነታቸው መለያ ይሆናል። በአንድ በተወሰነ ቡድን ውስጥ አባላቱ መሳተፋቸው የልማዱ አካል የመሆን ስሜት ይፈጥርባቸዋል። በልማዱ አማካይነትም ማንነታቸው የሚፈጠር ብሎም የሚረጋገጥ ይሆናል። በዚህ የተነሳ ይህ ቡድን ከሌሎች ቡድኖች ተለይቶ ይታያል። እንዲሁም Horner (1990) በበኩላቸው "ልማድ በትውልድ መካከል ያለ የዕውቀትና የአስተሳሰብ ቅብብሎሽ ነው፤ ቅብብሎሹ ግን ካለፈው ዘመን ወደ አሁኑ ብቻ የሚተላለፍ አይደለም፡፡ ይልቁንም በተመሳሳይ ወቅት የሚገኙ ቡድኖች ሊጋሩት ይችላሉ" በማለት የልማድ ቅብብሎሽ በተጓዳኝም ሆነ በተዋረድ በሚገናኙ ቡድኖች መካከል ሊካሄድ እንደሚችል ያስረዳሉ። በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡ ብያኔዎች ልማድ የአንድ ቡድን ዕውቀትና የዕውቀቱ የሽግግር መንገድ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በመሆኑም በዶረኒ ወረዳ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለጋብቻ ለበቁ ሴቶች በሚደረገው ባህላዊ ሥርዓት ውስጥ ማህበረሰቡ የሚተገብራቸው በርካታ ልማዶች አሉ።

### 2.1.4. ጋብቻ በሰው ልጅ ህይወት

ሰው ማህበራዊ እንስሳ ነው። በመሆኑም በተቋም ውስጥ አድጎ የራሱን ተቋም ይመሰርትና የማህብረሰብን ቀጣይነት ያረጋግጣል። ለዚህ ጉዞ መሸጋገሪያ ከሆኑ ድልድዩ መካከል አንዱ ጋብቻ ነው። ጋብቻ በሰዎች መካከል የሚፈጠር ማህበራዊ የአንድነት ሥርዓት ወይም ስምምነት ነው። ሥርዓቱ የሚመሠረተው በሠርግ ሥርአት ወይም በሌላ ዝግጅት ሊሆን ይችላል። የዚህ ተቋም አወቃቀር እንደየ ባህሉ፣ እንደየ ሃይማኖቱ እና እንደየ ጊዜው ይለያያል። በወንድ እና በሴት መካከል ለሚፈጠር ጋብቻ ወንዱ ባል የሚባል ሲሆን ሴቷ ደግሞ ሚስት ትባላለች። ከነዚህ ከማህበራዊ ተቋማት መካከል ሀይማኖትን ብናነሳ ሀይማኖት ልዩ ትኩረት ከቸራቸው ማህበራዊ ጉዳዮች አንዱ ጋብቻ ነው፡፡

ከዚሁ ጋር በማገናኘት የተለያዩ የሃይማኖት መጻሕፍት ስለ ጋብቻ በተለያየ መንገድ ይገልጹታል። ለምሳሌ መጻሃፍ ቅዱስ ስለ ጋብቻ እንዲህ ይላል። የጋብቻ መፈጠር

ዘፍጥረት 2፡23-24 ላይ ተመዝግቦ ይገኛል፣ "አዳምም አለ፣ 'ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፣ ሥጋም ከሥጋዬ ናት፣ እርሷ ከወንድ ተገኝታለችና "ሴት" ትባል።' ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል፣ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።" እግዚአብሔር ሰውን ፈጠረ፣ ከዚያም ሴትን ፈጠረ፣ ትጎዳኘው ዘንድ። ጋብቻ እግዚአብሔር "ያበጀው" ነው፣ "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም" በሚል በመጻፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ ይገኛል (ዘፍጥረት 2፡18)።

ይህ ጥቅስ እንደሚያመለክተው ጋብቻ በፈጣሪ ትዕዛዝ የተገኘ እና ሰው ብቻውን ሲሆን መልካም እንዳልሆነ ያሳያል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በቅዱስ ቁርዓን ውስጥም ጋብቻ የነፍስ ማረፊያ፣ የቀልብ መርጊያና መርኪያ፣ የሕሊና መረጋጊያ መሆኑንና ሁለቱ ጾታዎች በፍቅር፣ በመተዛዘን በመተባበር፣ በመቻቻልና በመመካከር የሚኖሩበት ተቋም እንደሆነ ያሳያል (Meraj፣2018) ። የሁለቱን ጾታዎች ዘልዓለማዊና ተፈጥሯዊ ግንኙነት በቁርአን ውስጥ እንደሚከተለው ተገጿል። "ለእናንተም ከነፍሶቻችሁ (ከጎሶቻችሁ) ሚስቶችን ወደ እነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፣ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው። በዚህ ውስጥ ለሚያስተውሉ ሕዝቦች ተዓምራቶች አልሉ። ጋብቻ የነፍስ ለነፍስ ትስስር ነው። ጠንካራ የግንኙነት ገመድ ነው። አላህ ሁለቱን ነፍሶች እንዲረጋጉ እና እንዲሰክኑ፣ በፍቅር የተሞላ ቤት ውስጥ በጋራ እንዲኖሩ አስተሳስሯቸዋል" (አልሩም፤ 21) ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በጋብቻ እና ቤተሰብ ጉዳዮች ላይ ምርምር ካደረጉት ምሁራን ውስጥ Olson (2006) ጋብቻን እንዲህ ይገልጻል። "ጋብቻ በተፈጥሮ ፈርጀ ብዙ ተቋም ነው።ጋብቻ በሁለት ሰዎች መካከል ሕጋዊ መሠረት ያለውና በመተማመን የሚመሰረት ሲሆን፤ ወሲባዊ ስሜትን ለመካፈልና ለሌሎችም የተለያዩ ኢኮኖያዊ ጥቅሞች በጋራ የሚመራበት ዘዴ መሆኑን ነው።"

ይህም ትንተና የሚያመለክተው ጋብቻ የግንኙነት መገለጫ የአንድነት ማሳያ መሆኑን ነው። ባልና ሚስቶች የሚጋሯቸው ጉዳዮች የሚፈጠርባት ተቋም መሆኑን ነው። በኢሉ አባቦር ዞን በዶረኒ ወረዳ በሚኖረው የኦሮም ማህበረሰብ ዘንድ ጋብቻ ትልቅ ቦታ ያለው ማህበራዊ ተቋም ነው።

### 2.1.5. የድንግልና ምንነት

ወሲባዊ ተሞክሮ በፍፁም የሌላት ሴት "ድንግል" ተብላ እንደምትጠራ ጥናቶች ሲገልጹ፤ ባህሩ (2014) ከፍተኛ የአማርኛ መዝገበ ቃላት በተሰኘው መጽሀፍ ፣ "ድንግል" የሚለውን ቃል ወሲባዊ ተሞክሮ የሌላት ሴት ወይም የሌለው ወንድ በማለት ይበይነዋል። ድንግላዊነት ማለት ድንግል ሆኖ መገኘት ማለት ነው። በእንግሊዘኛውም (virgin) የሚለው የቃሉ መሰረቱ (Virgo) ከሚለው የላቲን ቃል የመነጨ ሲሆን ትርጓሜውም "ወሲባዊ ተሞክሮ የሌላት ሴት" ማለት ነው። ልክ እንደ ላቲኑ ሁሉ የእንግሊዝኛውም ቃል ዕድሜን፣ ፆታንና ወሲባዊነትን ሰፋ አድርጎ የሚገልፅ ቃል ነው። ስለዚህ ድንግልና ማለት አንዲት ሴት ልጅ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ጾታዊ ግንኙነት ፈጽማ አለማወቋን ማሳያ ነው። ይሁን እንጂ አንዳንድ መረጃወች ድንግልና በሴቶች ብቻ እንደማይወሰን ይገልጻሉ። ይንን ሀሳብ በተመለከተ Sommers እና Sommers (2000) እንዲህ ይገልጸዋል። ድንግልና የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው በ13ኛው ክፍለ ዘመን ሲሆን የግብረ ስጋ ግንኙነት አድርጋ ከማታውቅ ሴት ጋር የተያያዘ ነው። ነገር ግን ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ ማንም ግብረ ስጋ ግንኙነት አድርጎ የማያውቅ ወንድም ሆነ ሴት ድንግል ይባላል። ይሁን እንጂ ድንግልና ከሴት ጋር የሚገናኝበት ሁለት ምክንያቶች አሉት። አንደኛ በወንዶች የሚታወቀው ማለትም ከተቃራኒ ጾታ አንጻር ወንዶች የሴቶችን ክብረ ንጽህና ያሳጣሉ በሚል አስተሳሰብ ሲሆን ሁለተኛ ምክንያት ደግሞ ድንግልና ሲወሰድ መገለጫው የደም መፍሰስ ተደርጎ ስለሚወሰድ ነው።

ከላይ ከተገለጸው ሀሳብ የምንረዳው ድንግልና በሴቶች ብቻ የማይወሰን ሲሆን ነገር ግን የሴቶች ድንግልና በግልጽ የሚታወቅና የተለየ ምልክት እንዳለው ያሳያል።

### 2.1.6. ድንግልና ከጋብቻ አንጻር

በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢያች በጋብቻ ወቅት ለድንግልና የሚሰጠው ዋጋ የተለያየ ነው።ለምሳሌ በሰሜን፣ በምዕራብ፣ በምስራቅ እና በአብዛኛው የደቡብ የኢትዮጵያ ክፍሎች ለድንግልና ትልቅ ግምት የሚሰጥ ሲሆን በአንዳንድ የኢትዮጵያ አካባቢዎችና ብሄረሰቦች ዘንድ አንዲት ሴት ልጅ ድንግልናዋን ጠብቃ ለጋብቻ ከበቃች ፈላጊ እንዳጣች ተደርጎ የሚወሰዱበት ሁኔታዎች አሉ። ነገር ግን ድንግልናን እስከ ጋብቻ ዕለት ጠብቆ ማቆየት

ዘለቄታ ያለው ትዳር ለመመስረት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ የተለያዩ መረጃዎች ያሳያሉ።

የድንግልና ነገር ባህላዊ፣ ስነልቦናዊና ማህበራዊ ግንኙነት እንዳሉትም ይታወቃል። "የተለያዩ ማህብረተሰቦች ውስጥ በፍቅር፣ በወሲብና በድንግል ላይ የተመሰረቱ "ቅናቶች" ዓለም አቀፉ የሰው ልጅ መገለጫዎች ናቸው" Donald (1991) ከስነ ልቦና አኳያ ደግሞ Kahn እና London (1991) እንዲህ በማለት ማብራሪያ ይሰጣሉ። ከጋብቻ በፊት ወሲብ የፈፀሙ ሴቶች ብዙዎቹ የትዳር መፍረስ አደጋ እንዳደረሰባቸው ታውቋል። ድንግልናን እስከ ጋብቻ ድረስ መጠበቅ የጥሩ አስተዳደግና የጨዋነት ምልክት ተደርጎ በሚወሰድበት ማህበረሰብ ውስጥም ከጋብቻ በፊት ወሲባዊ ተራክቦን የፈፀሙ ሴቶች ከድንግሎች የበለጠ ለትዳር መፍረስ የተጋለጡ ሆነው ተገኝተዋል።

Smith እና Shaffer (2013) ደግሞ ሴቶች በጋብቻ ዕለት መጀመሪያ ወሲብ መፈጸማቸው በወሲብ እረክቶ በትዳር ለመኖር አስተዋጾ እንዳለው እንደሚከተለው ገልጸውታል። የእንድ ሰው የመጀመሪያው ወሲባዊ ግንኙነት ለቀጣዩ አመታት ለሚኖረው ወሲባዊ ግንኙነት እርካታ ጋር የተገመናኘ ነው። በመሆኑም ሴቶች የመጀመሪያ ጊዜ ወሲባዊ ተራክቧቸው በጋብቻ ዕለት አስደሳች ከሆነ በቀጣይ በትዳር ህይወታቸው ያላቸው ወሲባዊ ግንኙት እርካታ ያለበት መሆኑን የጥናቱ ተሳታፊዎች አረጋግጠዋል።

ከላይ የተጠቀሱት ሃሳቦች እንደሚያሳዩት በትዳር ለመጽናትም ሆነ ስነልቦናዊ ተጽኖ ከሚፈጥሩ ጉዳዮች ነጻ ለመሆን አንዲት ሴት ልጅ ከጋብቻ በፊት ወሲብ መፈጸም እንደሌለባት ያሳያል። በተጨማሪም አንዲት ሴት ልጅ ድንግል ሆና ለትዳር መብቃቷ ስነ ልቦናዊ ተጽኖው ለሴቷ ብቻ ሳይሆን ለወንዱም ጭምር እንደሆነ ማየት ይቻላል። ምክንያቱም አንድ ወንድ ልጅ ምንም እንኳን በትግስት እና ዘመንኩ በሚል ሰበብ ድንግል ያልሆነችን ሴት ቢያገባ አንድ ወቅት የውስጥ ማንነቱ ጎልቶ ይወጣና ግጭት እንደሚፈጠር ወይም ትዳሩ ሊፈርስ እንደሚችል መገመት ይቻላል። በሌላ መልኩ ደግሞ ሴት ልጅ ከጋብቻ በፊት ወሲብ አለመፈጸሟና ከትዳር አጋሯ ጋር ወሲብ መጀመሯ ወይም ከባሏ ውጪ ሌላ ወንድ ባለማወቋ ባላት ወሲባዊ ግንኙነት እንደምትረካ ያመለክታል። ይህንን መነሻ በማድረግ እና በተለያዩ ሀገራት ወጣት ሴቶች ድንግልናቸውን ጠብቀው እስከ ጋብቻ ቀናቸው እንዲቆዩ የተለያዩ ስልቶችን ይጠቀማሉ። አንዳንድ ሀገሮች ውስጥ

አንድ ወንድ አንዲት ልጃገረድን አስገድዶ ቢደፍር ወይንም ድንግልናዋን ቢወስድ እንዲያገባት ወይም ካሳ እንዲከፍል ይደረጋል። ለምሳሌ ደስታ (2006) "የዲዚ ብሄረሰብ የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔ" በሚል ርዕስ ባቀረበው ጥናት የዲዚን ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት "ታርቅ ሲ" ሲገልጽ በዲዚ ብሔረሰብ አንዲት ልጃገረድ ክብሯን ጠብቃ በድንግልና ስታገባ በባህሉ ቦታ የሚሰጣትና ቤተሰቦቿም እጅግ የሚኮሩባት ሲሆን ሴት ልጅን ከጋብቻ በፊት አስገድዶ ድንግልናዋን ወንድ የወሰደ እንደሆነ በጥንት የዲዚ ባህል ለባላባቱ ሰባት ከብቶች፣ ለልጂቱ ቤተሰቦች አንድ ኮርማ በሬ እንዲከፍል ይደረጋል ።

ስለዚህ ከላይ ከተገለጹት ሀሳብ የምንረዳው ሴት ልጅ ድንግልዋን ጠብቃ ለትዳር መብቃቷ ከራሷ አልፎ ለቤተሰቦቿም ክብር እንዳላት የሚያመለክት ሲሆን ያለፍቃዷ ይህን ክብር የሚያስቸራት (ድንግልናዋል) የወሰደ ቅጣት እንደሚጣልበት ያሳያል። በዶረኒ ወረዳ የኦሮሞ ማህበረሰብም አንድ ሴት ልጅ ድንግልናዋን ጠብቃ ለትዳር መብቃት እንዳለባት ያምናል። በመሆኑም ወጣቶች ይህንን ባህላዊ እሴት እንዳይጥሱ ይረዳ ዘንድ የተለያዩ ስልቶች ይጠቀማሉ። ከነዚህም መካከል (Mogos፣ 2011) ስለ ሲርባ ዱርባ (Sirba durba) በጻፈው ጽሁፍ እንደገለጸው "ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ሲርባ ዱርባ (Sirba durba) ጭፈራ የሚላኩት ከወንድማቸው ወይም ከሚያምኑት ከጎረቤት ልጅ ጋር ነው" ።

## 2.1.7. ድንግልናን እስከ ጋብቻ ቀን ጠብቆ ማቆየት ያለው ጠቀሜታ

ወሲብ ተፈጥሯዊ የሆነ ጉዳይ ነው። በመሆኑም የሰው ልጅ ወሲብን ጤነኛ በሆነ መንገድ ሊተገብረው ይገባል። በፍሮይድ ትንታኔ መሰረት ራስን ከመመገብ ቀጥሎ ራስን ማብዛት (ወሲብ) የሰው መሰረታዊ ፍላጎት እንደሆን ያሳያል። የሰው ልጅ የኢንርጂ ሀይል ምንጩ ወይም ሞተሩ ወሲብ ነው። ይህንንም ሃሳብ ገላጋይ (2005) "ወሲብ ጤናማ በሆነ መንገድ መውጫ ካጣ በመጥፎ መውጣቱ አይቀርም። በመሆኑም ወሲብ በመጥፎ መንገድ እንዳይተገበር ትዳር ሁነኛ አማራጭ ነው።" በማለት ይገልጻል።

ከዚህ የምንረዳው ከትዳር ውጪ የሚተገበር ወሲብ ችግር ሊያስከትል እንደሚችል ነው። በመሆኑም ድንግልናን ጠብቆ እስጋብቻ በመቆየት ወሲብ በመጥፎ መንገድ እንዳይተገበር ሌለኛው መቆጣጠሪያ መንገድ እንደሆነ ያስገነዝባል።

ድንግልናን ጠብቆ ለትዳር መብቃት ያለውን ጠቀሜታ አስመልክቶ ከገለጹ ምሁራን መካከል Singer (2003) ሲገልጽ "ድንግልናነ የጋብቻ መቆጣጠሪያ በማድረግ ፣ የሴትን ልጅ የግብረ ስጋ ግንኙነት በመገደብ ፣ የጋብቻ ምርጫዋን በመቆጣጠር ወላጆች እንዲወስኑ ቢሆን እና ድንግልናዋን ያጣች ሴት ክብርን የማግኘት እድሏን ቢጠብ ሴቶች በለጋ እድሚያቸው በግብረ ስጋ አማካኝነት በሚተላለፉ በሽታዎች ለመቆጣጠር ያስችላል።" ሲል ይህንኑ ሀሳብ የተለያዩ ምሁራን እንደሚከተለው ገልጸውታል። በተለያዩ ሀገራት የሴት ልጅ ድንግልና የንጽህና መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል (Sizemb, 2009) (Esra, 2015) (Taressa, 2011)። የድንግልና መፈተሻ የሚደረግባቸው ሀገራትም አሉ (Sizemb, 2009)። የድንግልና መፈተሽ የመጣው ከማህበረሰቡ ድርጊት፣ በቤተሰብና በተቋመት ታግዞ እንዲሁም ኤች አይ ኤድስን ለመከላከል በጤና ተቋማት ከተሰጠው ምላሽ ጋር ይያያዛል። ይህም የሆነው በልጅነት እድሜቸው ግብረ ስጋ ግንኙነት የሚያደርጉ ሴቶች ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱም ነው። ምክንያቱም በለጋ እድሜ ግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ ለተለያዩ የስነ ተዋልዶ ጤና ቀውስ ያጋልጣል (Singer, 2003)።

በጅጋ (2008) በቱለማ ኦሮሞ ስለ ባህላዊ የፍቅር ግንኙነቶች እና ኤች አይ ቪ ኤድስ የሚነገሩና የሚከወኑ የስነቃል ዓይነቶች ይዘት ትንተና ላይ ባደረገው ጥናት ጋብቻን በተመለከተ የተሰበሰቡ ምሳሌያዊ ንግግሮች አጠቃላይ መልዕክት ከጋብቻ ውጭ የሚከናወኑ ወሲባዊ ግንኙነቶች ቅናትና ንቀት የሚያስከትሉ መሆናቸውን እና ለኤች አይ ቪ ቫይረስ ለሌሎችም ልዩ ልዩ አባለዘር በሽታዎች የሚያጋልጡ መሆናቸውን ገልጿል።

በአፍሪካና ደቡብ እስያ አገሮች በአብዛኛው በኤች. አይ. ቪ.. ኤድስ ቫይረስ የተጠቁት ወጣቶች ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል ወጣት ሴቶች ከፍተኛውን ቁጥር መያዛቸውን Rosenthal እና Moore (2006) ይገልጻሉ። በማያያዝም ኤች.አይ ቪ ኤድስ እያደረሰ ባለው ጥፋት በግንባር ቀደምትነት ተጠቂ የሆኑት እድሜያቸው ከ15-24 የሚገኙ ወጣት ሴቶች መሆናቸውን ስትገልጽ እንዲህ ትላለች። "በኤች. አይ. ቪ.. ቫይረስ ከተያዙት ወጣቶች ውስጥ የሴቶቹ ቁጥር ከወንዶቹ በሁለት እጥፍ ይበልጣል" (Paterson፣ 1996) ። በመሆኑም አንድ ሴት ልጅ እስከ ጋብቻ ዕለት ምንም አይነት ግብረ ስጋ ግንኙነት ካልፈጸመች በግብረ ስጋ ግንኙነት አማካኝነት ከሚተላለፉ በሽታዎች እራሷን ትከላከላለች ማለት ነው።

ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች የምንረዳው ድንግናን ጠብቆ ለትዳር መብቃት በግብረ ስጋ ግንኙነት አማካኝነት ከሚተላለፉ በሽታዎችና ከስነ ተዋልዶ ጋር በተያያዘ ሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጉዳትም ለመቆጣጠር ጠቀሜታ እንዳለው ያሳያል።

### 2.1.8. ድንግልና ከሃይማኖታዊ አስተሳሰቦች አንጻር

ለድንግና ከፍተኛ ቦታ ከሚሰጡ ማህበራዊ ተቋማት መካከል በዋነኛነት የሚጠቀሰው ሀይማኖት ነው። በአብዛኛው ሀይማኖት ከጋብቻ በፊት ግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸም ሀጥያት እንደሆነ ይገለጻል። በመጽሀፍ ቅዱስ 1ኛ ቆሮንጦስ 6÷18 "ከዝሙት ሽሹ፤ ዝሙትን የሚሰራ ግን በገዛ ስጋው ላይ ሀጥያት ያደርጋል። እንዲሁም 1ኛ ቆሮንጦስ 7÷2 "ነገር ግን ስለዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው። ሲል የካቶሊክ ቤተክርስቲያንን አስተምሮትን አስመልክቶ ደግሞ Kevin (2017) እንዲህ ይገልጸዋል። ድንግልና ቅዱስ ስጦታ ነውና በክብር ልንጠብቀው የሚገባ ጉዳይ ነው። ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሁሉም ድንግል ልጃገረዶች የድንግል ማሪያም ልጆች ናቸው ብላ ታስተምራልች። በድንግልና እድሚያቸውን ሙሉ የሚኖሩ ሴቶች ትልቅ ክብር በእምነቱ ዘንድ ይሰጣቸዋል። በማለት ቤተ ክርስቲያኗ ታስተምራለች። ይህ ትንታኔ የሚያመለክተው ሀይማኖት ለድንግልና ከፈተኛ ክብርና ቦታ እንደሚሰጥ ነው። ምክንያቱም ድንግልና የተገለፀው ከማርያም ጋር ተያይዞ ነው። በእምነቱ መሰረት ድንግል ማሪያም የተለየች፣ የተከበረች በድንግልና የወለደች ልዩ ሴት ናት። ስለዚህ ድንግልና በእምነት ደረጃም የተለየ ቦታ እንደሚሰጠው ያመላክታል።

## 2.2.የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቤተ መጽሀፍት እና ከእንተርኔት ባደረኩት ዳሰሳ እና ፍለጋ በኢሉአባቦር ዞን በኦሮሞ ማህበረሰብ ድንግልናን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚከወኑ ሥርዓቶችን በተመለከተ በሌሎች አጥኝዎች የተደረገ ጥናት አላገኘሁም። ሆኖም ግን ይህ ጥናት በተደረገበት አካባቢ ባይሆንም በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ በተወሰነ ደረጃ ተመሳሳይነት ያላቸው በሀገር ውሰጥ እና ከሀገር ውጪ የተጠኑ ጥናታዊ ጽሁፎች እንዲሁም መጽሄቶች ላይ የታተሙ ጥናቶች በተለያዩ ብሄረሰብ እና ሀገራት ከድንግልና ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮት ላይ ትኩረት ያደረጉ ጽሁፎች ተዳሰው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

መለስ እና ሌሎች (Yohannes, Tegabu, G/Slassie, & Gidey, 2016) ያሳተሙት ጥናታዊ ጽሁፍ በመቐለ ከተማ ድንግልና በወጣቶች ዘንድ ስላለው ዋጋና ከስነጾታዊ ባህሪያት ጋር ባለው ግንኙነት ላይ ያተኮረ ነው። ጥናቱ እንደሚያሳየው ለድንግልና ዋጋ እንዲሰጠው የሚያደርጉ ዋና ዋና ጉዳዮች የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ፣ ሀይማኖታዊ ቁርኝት ፣ በጉዳዩ ዙሪያ ቀድሞ መረጃ ማግኘት፣ ከወላጅ ጋር ማደግ የመሳሰሉት ናቸው። በተጨማሪም ጥናቱ እንደሚያመለክተው ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር ተያይዞ በወጣቱ ዘንድ ለድንግልና የሚሰጠው ዋጋ እየቀነሰ መምጣቱን ያሳያል። አያይዘውም ድንግል ሴቶች ድንግል ካልሆኑት በበለጠ በማህበረሰቡ ከፍተኛ ክብር እንዳላቸው እና የሚሰጣቸው ክብር ከራሳቸው አልፎ ቤተሰቦቻቸውንም እንደሚያስከብሩ በጥናቱ ተገልጿል። ይህ ጥናት ማህበረሰቡ ለድንግል ሴቶች የተለየ ክብር እንዳላቸው የሚያሳይ መሆኑ እና ማህበረሰቡ ለድንግልና የሚሰጠው ዋጋ በቴክኖሎጂ ሳቢያ እየቀነሰ መምጣቱን መጠቆሙ ጥናቱን ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሲሆን፣ ሌላው የመለስና ሌሎች ጥናት ድንግል ለሆነች ሴት እንደምትከበር እንጂ በሰርጓ ቀን ለክብሯ የሚደረግላት የተለየ ሥርዓት ምን እንደሚመስል አለማሳየቱ፣ ማህበረሰቡ ለድንግልና የተለየ ቦታ በመስጠቱ የሚያገኘውን ፋይዳ ያላሳየ በመሆኑ ጥናቱ ክፍተት ያለበት ይመስለኛል። በመሆኑም ይህንን ክፍተት በጥናቴ ተሟልቷል ብዬ አምናለሁ።

ደስታ (2006) "የዲዚ ብሄረሰብ የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔ" በሚል ርዕስ በኤም.ኤ ዲግሪ ጥናቱን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና እና ስነ-ጹሁፍ ትምህርት ክፍል አቅርቧል። የጥናቱ ዓላማ የዲዚ ብሄርሰብ የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔን ማሳየት ቢሆንም በትንተናው አንድ የብሄረሰቡ ባላባት ሲሞት በውርሰ ጊዜ በማህበረሰቡ ባህል መሰረት የውርስ የመጀመሪያው መስፈርት ወንድ ልጅ መሆን ሲሆን ይህም ወንድ ልጅ ባላባቱ በድንግልና ካገባት ሴት የተወለደ መሆን እንዳለበት ይገልጻል። አያይዞም በውርሱ ወቅት የተመረጠው ወንድ ልጅ ሙሉ በሙሉ የባላባቱን ስልጣን እና ሙሉ ሀብት የሚወርስ ሲሆን በተጨማሪም ከእናቱ በስተቀር የአባቱን ሚስቶች ሁሉንም ይወርሳል። ነገር ግን ወራሹ ሌላ ድንግል ሴት እንዲያገባ ይደረጋል። ምክንያቱም በድንግልና ከሚያገባት ሴት የሚወለደው ልጅ በባህሉ መሰረት ለውርስ መስፈርቱን ስለሚያሟላ ነው። ይሁን እንጂ አጥኚው ወራሹ ያገባት ሴት ድንግል ባትሆን ምን እንደሚሆን፣ ድንግልናዋን ጠብቃ ለጋብቻ ለበቃች ሴት የሚደረግ የተለየ ሥርዓት መኖሩን ወይም አለመኖሩን በተዋቀረ መረጃ አላስቀመጠም።

የአጥኝው ጥናት ስለ ማህበረሰቡ ለድንግልና የሚሰጠውን ዋጋ ማንሳቱ እናድንግልና ለማህበረሰቡ ያለውን ፋይዳ ማሳየቱ  ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። ይሁን እንጂ አጥው ይህ ርዕሰ ጉዳይ የጥናቱ አላማ ባለመሆኑ አስፈላጊነቱን እንጂ ለምን እንደሚደረግ፣ ማህበረሰቡ ድንግልናዋን ጠብቃ ለበቃች ሴት የሚደረጉ ሥርዓተ ክዋኔዎችን  አልዳሰሰም። ስለዚህ የኔ ጥናት በተለያዩ ዘዴዎች እነዚህን ክፍተቶች መድፈን ችሏል የሚል እምነት አለኝ።

ስንቅነሽ (2007 "ባህል ለልማት በበርታ ብሄረሰብ" በሚል ርዕስ በዶክተሬት ዲግሪ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዩጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ጹሁፍ ትምህርት ክፍል አቅርባለች። የጥናቱ ዋና አላማ የበር ታብሔረሰብ አጠቃላይ ባህላዊ እሴቶች ምን እንደሆኑ ማጥናት ሲሆን በዚህ ጥናት ርዕስ ስር የበርታን የጋብቻ ሁኔታ ስታጠና ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች እና ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ላልበቁ ሴቶች የጥሎሽ ልዩነት እንዳለ ያሳያል። እንዲሁም አንድት ሴት ልጅ ለጋብቻ ተፈቅዳ ጥሎሽ ከመገዛቱ በፊት ድንግልናዋን በአካባቢው አዋቂ ሴቶች በመፈተሽ እንዲያረጋግጡ መደረጉን እና በተለያዩ ምክንያቶች ድንግልናቸውን ከጋብቻ በፊት ያጡ ሴቶች በባህሉ መሰረት መዋሸት ስለማይቻል ቀድመው ለአጎታቸው በመንገር አግቢው በግልጽ ተነግሮት ከተስማማ ያለጥሎሽ እንዲያገባት መደረጉንእና ካልተስማማ ግን ጋብቻው ሊደናቀፍ እንደሚችል ተገልጿል። ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳስለው ድንግልናቸውን ጠብቀው ለጋብቻ ለበቁ ሴቶች የሚሰጣቸውን ክብር ማሳየቱ ነው። ነገር ግን ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር የሚበቁ ሴቶች በጋብቻ ወቅት የሚደረግላቸው የተለየ ሥርዓትና ያለጥሎሽ ትዳር ብትመሰርት ትዳሩ በኋላ ላይ ምን ችግር እንደሚገጥመው አልተዳሰሰም። ስለዚህ የኔ ጥናት በተለያዩ ዘዴዎች እነዚህን ክፍተቶች መዳሰስ ችሏል የሚል እምነት አለኝ።

አዜብ (2006) ‹‹የከፍቾ ብሄረሰብ የሴቶና የወንዶች አለባበስና አጋጊያጥ›› በሚል ርዕስ በኤም.ኤ ዲግሪ ጥናቷ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዩጵያ ቋንቋዎችና እና ስነ-ጹሁፍ ትምህርት ክፍል አቅርባለች። በዚህ የከፍቾ ብሄረሰብ ባህላዊ ሁኔታ ስር በቤተሰብ ፍቃድ የሚደረግ ጋብቻን እና የወንድ ቤተሰቦች የጎሳ እኩልነትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ልጃቸውን የምትመጥን ሴት ፈልገው ለማጋባት የሚነሱበትን የጋብቻ አይነት ገልጻለች። በሰርጉ ዕለት ሙሽራዋ  ድንግል ሆና ከተገኘችና ጩኸት ካሰማች የደስታ ጭፈራ

እንደሚጨፈር ከሌላት ግን ልትገረፍ እንደምትችል ተገልጿል። አያይዛም የምስራቹ በወንዱ ቤተሰብ ዘንድ የሚቀር ሳይሆን በሚቀጥለው ቀን ሚዜዎች ከብዙ አጃቢዎች ጋር በመሆን ወደ ሙሽሪት ቤተሰብ ቤት መወሰዱን፤ በደም የተነከረው ጨርቅ ናሙና ሆኖ መቅረቡና በዚህም ወላጆቿ ይከበሩበት እንደነበር ገልጻለች። ምንም እንኳን ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር በአላማ ሆነ በርዕሰ ጉዳዩ ቢለይም ማህበረሰቡ ለድንግልና የሚሰጠውን ዋጋ፣ በሰርግ ወቅት የሚደረገውን ጭፈራ፣ ለሙሽራዋ ሆነ ለቤተሰቦቿ የሚያስገኘውን ክብር አሳይቷል። በነዚህም ጉዳዮች ጥናቱን ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። በአጠቃላይ በአዜብ ጥናት መረጃውን በምን አይነት ዘዴ አንደተሰበሰበ ያለማሳወቅ ችግር ይታያል። እንዲሁም ሥርዓቱ እንዲህ ይፈጸማል ከማለት ዉጪ ሥርዓተ ክወናው አሁን በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ሆነ የሥርዓቱ ባለቤቶች ይህን በማድረጋቸው ምን ፋይዳ እንደሚያገኙ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ አለማሳየቷ ክፍተት ይታይበታል። ስለዚህ የኔ ጥናት ይህንን ጽሁፍ እንደ ተዛማጅ ጥናት በመጠቀም ያሉትን ክፍተቶች ለማሟላት ጥረት ተደርጓል።

Taressa (2011) የቀረበው የዶክተሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት ትኩረት ያደረገው ከሞሮኮ ወደ ስፔን በሚደረገው የስደተኞች ጉዞ በሴቶች ክብርና ጋብቻ ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖ ማሳየት ነው። በጥናቱም በሞሮኮ ያሉ እንዲሁም ወደ ስፔን የተሰደዱ ሞሮኮዊያን ለድንግልና ትልቅ ዋጋ ይሰጡ እንደነበር ተገልጽል። አያይዞም ድንግልና ከቤተሰብ ክብር ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ከመሆኑም አልፎ ለትዳር መጽናት ትልቅ አስተዋጾ አለው ብለው ያምኑ እንደነበር አሳይቷል። በተጨማሪም በጋብቻ ወቅት ወንዱ ሙሽራ የሴቷን ገላ የራሱ ማድረጉን የሚያሳየው የደም መፍሰስን በማሳየት ነው።ሴት ልጅም ድንግልናዋን ጠብቃ ለጋብቻ እለት ከበቃችና ድንግል መሆኗ ሲረጋገጥ ከቤተ ዘመድ ጋር በመሆን ይጨፈራል፤ እልልታውም ይደራል። ይህ ደግሞ እንደ ሞሮኮ ላሉ የእስልምና እምነት ተከታዮች ሀገሮች ድንግልና ያለው ዋጋ ከፍተኛ መሆኑን ይገልጻል።

ይህ ጥናት ማህበረሰቡ ለድንግልና ያለውን ዋጋ ማሳየቱ፣ ድንግልና ለቤተሰብ ከሚያስገኘውም ክብር በላይ ለትዳር መጽናትም ከፍተኛ ሚና እንዳለውም መግለጹ እና ድንግልናዋን ጠብቃ ለትዳር ለበቃች ሴት የሚደረገውን የተለየ ሥርዓት ማሳየቱ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። በተጨማሪም በዚህ ጥናት ሞሮኮአዊያን ባህላቸውን ጠብቀው ከትውልድ ትውልድ ከማሸጋገር አኳያ ጠንካሮች መሆናቸውን በተሰደዱበት ሀገር እንኳ

ባህላቸውን ጠብቀው የሚቆዩ መኖናቸውን መግለጹ የጥናቱ ጥንካሬ ነው። ይሁን እንጂ ጥናቱ ከኢትዮጵያ ውጭ የተሰራ በመሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር የባህልና እና የቋንቋ ልዩነት ይታይበታል። በተጨማሪም ድንግልናዋን ጠብቃ ለጋብቻ ያልበቃች ሴት በማህበረሰቡ የሚደርስባት ተጽኖ ምን እንደሆነ በግልጽ አልተቀመጠም።ስለዚህ የኔ ጥናት እነዚህን ክፍተቶች ይሞላል ተብሎ ይታመናል።

Hajru (2013) ባቀረበው የዶክተሬት ድግሪ ማሚያ ጥናቱ በኮሶቮ ማህበረሰብ እስከ ጋብቻ እለት ድረስ ድንግል ሆኖ መቆየት ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው መሆኑን ገልጾ፤ ከጋብቻ በፊት ድንግልናዋን ያጣች ሴት እንደማትከበር ከዚያም በተጨማሪ ቅጣት ይጣልባታል። ቤተሰቦቿም ክብር የማያገኙ መሆናቸውን እንዲሁንም ሊያገባት የሚፈልግም ሰው እንደማይኖር ተገልጿል። ንብረት የመውረስ መብቷንም እንድታጣ ይደረገል። ነገር ግን እ.አ.አ. ከ1999 የኮሶቮ ጦርነት በኋላ በርካታ የውጭ ሀገር ዜጎችና ወታደሮች ወደ ሀገሪቱ ስለገቡ ለድንግልና ያለው ዋጋ እየቀነሰ በመምጣቱ ጾታዊ ነጻነት እየጨመረ እንደመጣ በማጠቃለያው ገልጿል። ይህ ጥናት በዋነኝነት ትኩረት ያደረገው ከጋብቻ በፊት ድንግልናቸውን ያጡ ሴቶች ላይ የሚደርስባቸውን ጫና እንጂ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለሚያገቡ ሴቶች ለክብራቸው የሚደረገውን የተለየ ሥርዓት አልገለጸም። በተጨማሪም ማህበረሰቡ ለድንግልና የተለየ ትኩረት በመስጠቱ ያገኘውን ፋይዳ አለማሳየቱ የጥናቱ ክፍተት ነው።

ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ማህበረሰቡ ለድንግልና የሚሰጠውን ዋጋ ማሳየቱ ሲሆን ልዩነታቸው ደግሞ ይህ ጥናት ከትዳር በፊት ድንግልናቸውን ላጡ ሴቶች የሚደርስባቸውን ተጽኖ ማሳየት እንጂ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር የበቁ ሴቶች የሚደረግላቸውን የተለየ ሥርዓት አለማሳየቱ እና ማህበረሰቡ የሚያገኘውን ፋይዳ አለመግጹ ከኔ ጥናት ይለያል። ስለዚህ የኔ ጥናት እነዚህ ክፍተቶችን ይሞላል ተብሎ ይታመናል።

Sizemb (2009) ለሁለተኛ ድግሪ ማሚያ ያቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ በደቡብ አፍሪካ የዙሉ ናታል ማህበረሰብ ዘንድ የድንግልና ምርመራ ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደሚከናወን ያረጋግጣል። አብዛኞቹ የማህበረሰቡ አባላት የድንግልና ምርመራ ማድረግ የጠፋውን

ባህላቸው እንዲያንሰራራ የሚያደርጉበት ብቸኛ መንገድ አድርገው ይወስዱታል።የዚህ ጥናት አላማ በወጣት ሴቶችና ወንዶች አንጻር የድንግልና ምርመራ ማድርግ ለምን እንደሚያስፈልግ ማወቅ ነው። የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው በወጣቶች ዘንድ የድንግልና ምርመራ ማድረግ ከፍተኛ ተቀባይነት እንዳለው ያሳያል። አብዛኞች ወጣቶች የድንግልና ምርመራ ማድረግ ከራሳቸው ክብር፣ ግርማ ሞገስ እና ማዕረግ በተጓዳኝ የባህላቸው አካል አድርገው ያዩታል። ይሁን እንጂ የድንግልና ምርመራ ከተጀመረ ወዲህ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል እየተበራከተ መምጣቱን አንዳንዶች ይናገራሉ። በተለይም ድንግልና ምርመራ ማድረግ የእርግዝና መከላከያ መንገድ ተደርጎ ይቆጠራል። ምክንያቱም ምርመራ ያደረገች ሴት የግብረ ስጋ ግንኙነት ለማድረግ ፍራቻ ስለሚያድርባት ነው። አያይዞም የድንግልና ምርመራ በዋነኝነት የሚያተኮር ወጣት ሴቶች ላይ ነው። ምክንያቱም ወጣት ሴቶች ተጋላጭ በሆኑባቸው ዘርፎች ላይ ክህሎታቸውን በማሳደግ እራሳቸውን መከላከል የሚችሉበትን እና የራስ መተማመን ማጎልበት ይችላሉ በሚል ነው። ከዚህም በተጨማሪ በዙሉ ማህበረሰብ የሴት ልጅ ድንግል መሆን መረጋገጡ ቤተሰቦቿ ለጋብቻ ጥሎሽ የሚጠይቁትን ገንዘብ (ሀብት) እንዲጨምር ያደርጋል። በባህሉ መሰረት  ሴት ልጅ ድንግል ከሆነች ለእናቷ ተጨማሪ ከብቶች እንዲሰጡ ይደረጋል። በተቃራኒው ሴት ልጅ ድንግል ሆና ካልተገኘች፣ አባቷ ለማህበረሰብ ኃላፊ ከብቶች መስጠት ይኖርበታል። ምክንያቱም እንደማህብረተሰቡ አመለካከት ልጅቷ የወላጆቿን ብሎም  የሀገሯን  ክብር አልጠበቀችም የሚል እምነት ስላላቸው ነው። በደቡብ አፍሪካ በዙሉና በጥሆሳ ማህበረሰብ ዘንድ ይህ የድግልና ምርመራ የሚካሄደው በአካባቢው ማህበረሰብ መሪ ባለበት በታዋቂና በተከበሩ የአካባቢው አዛውንት ሴቶች ነው። ምክንያቱም በዙሉ ማህበረሰብ ዘንድ ድንግልና የራስና የሀገር  ክብር መጠበቂያና የክብር መገለጫ ተደርጎ ስለሚወሰድ ነው።

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው የድንግልና ምርመራ ላይ ሲሆን፤ ምርመራ መደረጉ ሴቶች ክህሎትን አጎልብተው እራሳቸውን ከመጠበቃቸውም በተጨማሪ ክብሩ ከራሳቸው አልፎ ለሀገርም ክብር እንደሚያስገኝ፣ በጋብቻ ወቅት ክብረ ድንግልናቸውን ጠበቀው ለጋብቻ ለበቁና ላልበቁ  ሴቶች  የሚደረገው የጥሎሽ ልዩነት  እንዲሁም ምርመራው በሀገር ደረጃ በታዋቂ ሰዎች መደረጉ በማህበረሰቡ ለድንግልና ምን ያህል ትኩረት እና ዋጋ እንደተሰጠው ያሳያል። ይህ ጥናት ድንግልናን ለጋብቻ እንደ አንድ መስፈርት ማንሳቱ፣ ማህበረሰቡ ለድንግና የሚሰጠውን ውክልና መዳሰሱና ድንግል መሆን ለሴቶች አልፎም ለሀገር

የሚያስገኘውን ፋይዳ መጠቆሙ ጥናቱን ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። ነገር ግን ጥናቱ ሴት ልጅ ድንግል መሆኗንን መመርመሯን እንጂ አንድ ሴት ልጅ ድንግል ሆና በመገኘቷ በሰርጓ እለትም ሆነ የምርመራው እለት የሚደረግላትን የተለየ ሥርዓትም ሆነ የተለየ ሽልማት እንደሚኖራት አለማሳየቱ፣ በጋብቻ ወቅት ድንግልናቸውን ጠብቀው ላገቡ ሴቶች እና ድንግልናቸውን ጠብቃው ላላገቡ ሴቶች የሚደረገውን የጥሎሽ ልዩነት እንጂ ከትዳር መጽናት ጋር ያለውን ጉዳይ አለማንሳቱ እና ይህ ጥናት ከኢትዮጵያ ውጪ በደቡብ አፍሪካ በዙሉና ጥሆሳ ማህበረሰብ ዘንድ የተደረገ ጥናት በመሆኑ ከኔ ጥናት ጋር የቋንቋ እና የባህል ልዩነትም ይታይበታል። በአጠቃላይ የኔ ጥናት እነዚህን ክፍተቶች ይሞላል ተብሎ ይጠበቃል።

Daniel (2004) ያሳተመው ጥናት ዋና ትኩረት ያደረገው የድንግልና አስተያየት (ቅበላ) የሚያመጣውን ማህበራዊ ችግሮች ማሳየት ላይ ነው። ለድንግልና የሚሰጠው የተዛባ አስተያየት በተለያዩ የአለማችን ክፍሎች አሁንም በሰፊው እንደሚስተዋላል ይገልጻል። ለምሳሌ አድገዋል በሚባሉት ቻይና እና አሜሪካ ለድንግልና የሚሰጠው የተዛባ አስተያየት መኖሩን ያሳያል። በተለይም የሴቶች ድንግልና ከወንዶች ይልቅ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑን ያሳያል። ድንግልና ሴት ልጅ ትዳር የማግኘት (ዋጋዋን) ከማሳደግና ከማሳነስ አንፃር እንዲሁም የተሳካ ትዳር ከመምራት አንፃር ከፍተኛ ቦታ ያለው መሆኑ በጥናቱ ተገልጿዋል። ከጋብቻ በፊት ድንግልናን ማጣት ለጋብቻ መፍረስ ዋና መንስኤ መሆኑም ተዳሷል። ይህ ጽሁፍ ስለድንግልና ዋጋ ማንሳቱ እና ድንግልናን ከጋብቻ ጋር አያይዞ ማቅረቡ እና በትዳር ጸንቶ ለመቆት ድንግልናን ጠብቆ ለትዳር መቃት ያለውን ሚና ማሳየቱ ጽሁፉን ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። ይሁን እንጂ የተለያዩ የጥናት ስልቶችን እና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ለድንግል ሴት የሚደረገውን የተለየ ሥርዓት ከበራ እና ስለ ድንግና ያለው አተያይ በአሁኑ ወቅት ያለበትን ደረጃ በሰፊው አለመዳሰሱ የጽሁ ክፍተቶች ናቸው። ስለዚህ የኔ ጥናት እነዚህን ክፍተቶች አሟልቶ ያቀርባል ተብሎ ይታመናል።

Esra (2015) ባቀረበው ጥናት በቱርክ ማህበረሰብ ዘንድ የሴት ገላ የማህበረሰቡ ንብረት ተደርጎ ይታያል፡፡ የሴት ልጅ ገላ እንደግል አካል ተደርጎ እንደማይታይም ጥናቱ ያመላክታል። በዚህም ሁኔታ ማህበረሰቡ ለድንግልና ያለው ዋጋ ሳይቀየር ቆይቶ፣ አሁንም

በማህበረሰቡ ባህላዊ መስተጋብሮች ውስጥ ተዋህዶ ይገኛል። ይህም በሀገሪቱ ህግና ደንቦች፣ በፍታብሄር ህጎች፣ ሴቶችን ለመግለጽ በሚጠበቁባቸው ቋንቋዎች (አገላለጾች)፣ የድንግልና ምርመራና የድንግልና ቀዶ ጥገና ሂደቶች ውስጥ ይስተዋላል። በዚህም ማህበረሰብ ሴት ልጅ ንጽህናዋን ወይም ጨዋነቷን፣ ለቤተሰብ ያላትን ታማኝነት የምታሳየው ድንግልናዋን እስከ ጋብቻዋ ቀን በመጠበቅ ነው። በመሆኑም እንደማህበረሰቡ ባህል በሰርግ እለት ደም የነካው ማህረብ ካልታየ ሴቶች ከፍተኛ ቅጣት ይደርስባቸዋል። በአጠቃላይ በቱርክ ማህበረሰብ ዘንድ ድንግልናን ጠብቆ እስከ ጋብቻ ዕለት መቆየት የሴቶች የጨዋነት መቆጣጠሪያ ተደርጎ እንደሚወሰድ ጥናቱ ያሳያል።

ይህ ጥንናት ድንግልናን ጠብቆ እስከ ጋበቻ ቀን መድረስ ለሙሽራዋና ለቤተሰቦቿ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚያስገኘውን ፋይዳ መዳሰሱ እና ባህሉ በለውጥ ሂደት ውስጥ መሆኑን መገለጹ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። ነገር ግን ይህ ጥናት በዚህ መልኩ ለጋብቻ በቅተው አሁን በትዳራቸው ምን አይነት ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ አለማሳየቱ፣ድንግልና በቀዶ ጥገና መተካት እንደጀመረ እንጂ በቀዶ ጥገና የተገኘው ድንግልና ከተፈጥሮው ድንግልና ልዩነት መኖሩን እና አለመኖሩን ፣ ካለ ልዩነቱ ምን እንደሆ አለማሳየቱ፣ በሰርግ እለት ደም የነካው ማህረብ ካልታየ ሴቶች የሚደርስባቸውን ቅጣት እንጂ መሀረቡ ከታየ የሚደረግላቸውን የተለየ ሥርዓት አለማሳየቱ የጥናቱ ክፍተቶች ናቸው። በመሆኑም የኔ ጥናት እነዚህን ክፍተቶች ይሞላል ተብሎ ይታመናል።

Carrie (2016) ለኤም.ኤ ዲግሪ ጥናቱ ትኩረት ያደረገው በጥንታዊ የክርስቲያን ቤተክርስቲያን የሴቶችን ሚና ማጤን ነው። የሴቶች ሚና፣ ድንግልና እና ክርስቲያናዊ ጋብቻ የጥናቱ ዋና ዋና ተኩረቶች ናቸው። በቀደምት ጊዜያት፣ ሴቶች ድንግል በመሆናቸው ታላቅ ክብር ይጎናፅፉ እንደነበር ይገልጻል። ምክንያቱም ግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም እንደ ሀጢያት ይቆጠር ስለነበር ነው። በመሆኑም በድንግልና የቆየች ሴት ንፁህ ናት ተብሎ ስለሚታመን ከፍተኛ ክብር ይኖራታል። በሌላ መልኩ ሌሎች የሀይማኖት ጠበብቶች ደግሞ ጋብቻን ለቤተክርስቲያን ልጅ ከመውለድ ጋር ያያይዙታል። እነርሱም ጋብቻ የፈጣሪ ትዕዛዝ እንጂ የሃጢያት ቅጣት አድርገው አያዩትም። በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ትኩረት ድንግልና እና ጋብቻ በሃይማኖታዊ አስተምሮት ውስጥ ያላቸውን እይታ ነው።

ስለዚህ ይህ ጥናት  ድንግልና ላይ ትኩረት ማድረጉ እና ድንግልናቸውን ለጠበቁ ሴቶች የሚሰጣቸውን ክብር ማሳየቱ ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። ነገር ግን  በጋብቻ ወቅት ግብረ ስጋ ግንኙነትን እንደ ሀጥያት መውሰዱ፣ የክርስትና እምነት ላይ ብቻ ማተኮሩ፣ ጥንታዊ መሆኑ እና ለድንግል ሴት የተለየ ክብር እንደሚሰጣት እንጂ ከጋብቻ ጋር አያይዞ ባለመግለጹ  የጥናቱ ክፍተቶች ናቸው። ስለዚህ የኔ ጥናት እነዚህን ክፍተቶች አሟልቷል ተብሎ ይታመናል።

Kathry (2010) ባቀረበው ጽሁፍ  ሮማዊቷ “Vestal Virgin” ነጭ የካህን ልብስ ለባሽ፣ ንጽህናዋ እና ክብሯ ከፍ ያለች ሴት ነበረች። የዚህች ሴት ገፅታ የብዙዎችን ፀሐፊዎች፣ ሰዓሊዎች፣ እና ተመራማሪዎች ትኩረት የሳበ እንደነበረ  በጽሁፉ ተገልጿል።በጽሁፉ እንደተገለጸው እሷ ከድንግልም በላይ እንደ ነበረች ይላሉ፣ እሷ የሮማ ልጅ፣ እናት እና ቅድስት ነበረች ይሏታል። ይህች ሴት ድንግል በመሆኗ፣ እንደ ንፁህ ስለምትታይ ከፍተኛ ተቀባይነትና የፖለቲካ ሀይል እና ክብር ስላስገኘላት፣ የታላቋ ሮማ ኢንፓየር ዘብ ተደርጋ ትቆጠር ነበር። የዚህች ድንግል ሴት ሀያልነትም የሮምን አንድነት ያጠናከረ መሆኑ ይገልፃልይህ ጽሁፍ በድንግልና መኖር በማህበረሰቡ ዘንድ ለአንዲት ሴት ልጅ የሚያስገኘውን ፋይዳ መዳሰሱ ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። ነገር ግን ጽሁፉ ታሪካዊ ሆኖ ታሪኩም  የአንዲት ድንግል ሴትን ታሪክ የሚተርክ እንጂ ሌሎች ተያያዥ መረጃዎች ተቀናጅተው አልቀረቡም። በመሆኑም የድንግልናን ተቀባይነት (ሀያልነት) ከመግለጽ ውጪ ሌሎች ጉዳዮችን ባለመዳሰሱ ክፍተት ይታይበታል። የእኔ ጥናት እነዚህን ክፍተቶች ያሟላል ተብሎ ይታመናል።

## 2.3 የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ

### 2.3.1 የዶረኒ ወረዳ መገኛ

የኢሉአባቦራ ዞን በምዕራብ ኢትዮጵያ ፣በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ ውስጥ ከሚገኙ ዞኖች አንዱ ነው። የዶረኒ ወረዳ በኢሉአባቦራ ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች አንዱ ሲሆን ወረዳው በወንዞች እና በደኖች ተከልሎ ይገኛል። እንዲሁም በዞኑ የሚታወቀው የያዩ ጫካ በከፊል በወረዳው ውስጥ የሚገኝ የተፈጥሮ ሀብት ነው። ወረዳውን በስተምዕራብ የቢሎ ኖፓ ወረዳ፣ በስተደቡብ የያዩ ወረዳ፣ በስተምስራቅ የቡኖ በደሌ ዞን ጮራ ወረዳ እና በስተሰሜን የአልጌ ሳቺ ወረዳ ያዋስኑታል። ወረዳው ከአዲስ አበባ በስተምዕራብ 586 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ

ሲሆን የዞኑ ዋና ከተማ ከሆነችው መቱ ደግሞ በስተምስራቅ አቅታጫ 58 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል። ወረዳው አስራ ሁለት የገጠር ከተማዎችና አንድ የከተማ ቀበሌ አሉት። እነሱም ኤሌሞ ፣በዴሳ፣ ወይራ፣ ቦጮ፣ ሶዮማ፣ ሂና፣ በተሊ፣ ወረቦ፣ ሀሮ፣ ዲዱ፣ ሆዳ አቦ፣ ሬጂ፣ ሲቦና ሲጦ ናቸው።

የዶረኒ ወረዳ የሚኖረው የኦሮሞ ማህበረሰብ የቱሜ ኦሞሮ የዘር ሀረግ ነው። ከኦሮሞ ብሄረሰብ በተጨማሪ ሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ይገኙበታል። በ2001 ዓ .ም በተደረገው የህዝብና ቤት ቆጠራ መሰረት የወረዳው ህዝብ ቁጥር ወንድ 20,395፣ ሴት 20,429 ድምር 40,824 ሲሆን ማህበረሰቡ የኦርቶዶክስ፣ፕሮቴስታንት እና የሙስሊም እምነት ተከታይ ናቸው። ማህበረሰቡ ኑሮውን በግብርና፣ በቡና ምርት እና በከብት እርባታ ስራ ላይ የተመሰረተ ሲሆን የተወሰነው የማህበረሰብ ክፍል ደግሞ በንግድ ስራ ይተዳደራል። የወረዳው የአየር ንብረትም ደጋና ወይናደጋ በመሆናቸው ለኑሮ ምቹ ናቸው። አነስተኛው የወረዳው ክፍል ደጋማ የአየር ንብረት አለው። ወረዳው የተለያዩ የእህል ዘሮችና እንደ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ማሽላ እና ቡና የመሳሰሉት የሚበቅሉበት አካባቢ ነው።

## 2.3.2 በዶረኒ ወረዳ የሚኖረው የኦሮሞ ማህበረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ

በዶረኒ ወረዳ የሚኖረው የኦሮሞ ብሄረሰብ መነሻው በምዕራብ ሸዋ ጀባቲና መጫ ከሚባል ቦታ እንደነበር ይነግራል። በዚሁ ቦታ ዶረኒ የሚባል ሰው ይኖር እንደነበረና ሶስቱ የዶረኒ ልጆች ዛሬ ጮራ ተብሎ በሚጠራው ወረዳ ወደ ዶረኒ እንደገቡ መረጃዎች ያሳያሉ። የዶረኒ ልጆች አሁን ዶረኒ ወረዳ ተብሎ በሚጠራው ቦታ አመጣጥ እንደሚከተለው ነው። በመጀመሪያ ዶረኒ ሶስት ልጆች ነበሩት። እነሱም አጂላ፣ በሪና አሊዪ ናቸው። የሶስቱ ልጆች አባት የሆነው ዶረኒ ወደ ኢሉአባቦር ሳይመጣ በመጫ ጀባቲና ሲቀር ሶስቱ የዶረኒ ልጆች ግን የሚሰፍሩበት ቦታ ለመፈለግ ወደ ዶረኒ ሄዱ። የዶረኒ የበኩር ልጅ ከመጫ ጀባቲና መተው አሁን ዶረኒ በሚባለው ቦታ ሰፈሩ። የዶረኒ የበኩር ልጅ አጂላ በጮራ ወረዳና የዶረኒ ድንበር በሆነው ጨረቻ ከሚባለው ቦታ እስከ ኤሌሞ ወንዝ ሲይዝ በሪ ደግሞ ከኤሌሞ ወንዝ እስከ ወይራና በተሊ ቀበሌ ያለውን ያዘ። የኤሌሞ ልጅ አልዩ ከዛሬዋ አልሞ ከተማ እስከ ሂና ቀበሌ ድረስ እንደያዙ መረጃዎች ያሳያሉ። ለድንበር እንዲመች በደረሱበት ቦታ «ኢጨቻ» ያስቀምጡ እንደነበርም ይነገራል። እነዚህ ነገዶች በስራቸው በርካታ የዘር ሀረግ ነበራቸው። ለምሳሌ አጂላ፤ ጡማኖ፣ ሳቆ፣ ኢናን፣ በዲ፣

ወንበራ ዶገኖ ና አቡኮ የተባሉ የዘር ሀረጎችን በውስጡ ይይዝ ነበር። በተሊ፣ ሁንቡሬ፣ በሪደጋ፣ በሪኦች፣ ቤሮ እና ሀንቦቲን የበሪ የዘር ሀረግ ሲሆኑ የአልዩ ደግሞ ባቦ፣ ወጂ፣ አኖ፣ ሀረሪ፣ ዳዲ፣ ኢላሙ፣ አገሎና ቦኩ ናቸው።ሶስቱ የዶረኒ ልጆች (አጂላ፣ አልዩ እና በሪ) በ18ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ የዘር ሀረጋቸው በዶረኒ ወረዳ በስፋት ይገኛሉ (Mogos፣ 2011) ።

### 2.3.3 የዶረኒ ወረዳ ስያሜ

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የዛሬዋ ዶረኒ ወረዳ ስያሜዋን ያገኘችው ሶስቱ የዶረኒ ልጆች ከምዕራብ ሸዋ በመምጣት በዛሬዋ ዶረኒ ሰፈሩ። ከዚህም በመነሳት ወረዳዋ በሶስቱ የዶረኒ ልጆች አባት በሆነው ዶረኒ ስያሜዋን እንዳገኘች ይነገራል። በተጨማሪም ኤሌሞ የዶረኒ ዋና ከተማ ስትሆን ኤሌሞም ስያሜዋን ያገኘችው ከአልዩ ነገድ መካከል አንዱ የሆነው ኢላሙቱ በዚህ ቦታ ይኖር ስለነበር ነው። ኢላሚቱ ከሚለው በመነሳት ኤሌሞ ተብሎ እንደተሰየመም ይነገራል።

### 2.3.4 ጥንታዊ የዶረኒ አስተዳደር ሥርዓት

ጥንታዊ የዶረኒ አስዳደር ሥርዓት ከገዳ ሥርዓት ጋር የተያያዘ ነበር። ስለዚህ የዶረኒን አስተዳደር ሥርዓት ከመግለጼ በፊት የኢሉአባቦርን የገዳ ሥርዓት ማንሳቱ የተሸለ ይሆናል። የኢሉአባቦር የገዳ አስተዳደር ሲገለጽ ‹‹በመጫ ነገድ ውስጥ ከሚመደቡት የአቶ ቶርበን (Obbo Torban) ልጆች ሌቃ (Leqaa)፣ ሰዮ (Sayyo)፣ ሲቡ (Sibuu)፣ ቱሜ (Tummee)፣ ሊሙ (Limmu) ፣አቦኖ (Abboonnoo) እና ዳኖ (Daannoo) ነበሩ። ከእነዚህ የመጫ ኦሮሞ መካከል በምዕራብ ወለጋ የሚገኘው ሰዮ በሰሜን ምዕራብ ክፍል ወለጋን፣ ሌቃ በምስራቅ ወለጋ ሰፈሩ። በዚህም ምክንያት ቱሜ በኢሉአባር ተስፋፋ። ከቱሜ ነገድ እንደ ባለአባት ሆኖ ኢሉአባቦርን ሲያስተዳድር የነበረው ኢሉ ነበር። ኢሉ ደግሞ ኢሉ ሰግለን በመባል ይታወቅ ነበር። ከሰግን አሉ ልጆች ውስጥ ታላቁ ሀዴሳ (Hadheessoo) ነው። የቱሜ ነገድ የሆኑት ሁሉ ያዩ አዳ ጎዲ የሚባለውን ቦታ የገዳ ሥርዓታቸው መዕከል በማድረግ ዘጠኝ (9) ነገዶችና አርባ አምስት (45) አባላት የጥንቱን የገዳ ሥርዓትን በመመስረት አካባቢያቸውን ያስተዳድሩ ነበር።

በጥንት ጊዜ ዘጠኙ ነገዶች የኢሉ ገዳ ሥርዓት ጉባኤ 45 መቀመጫዎች ያላቸው ሲሆን እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል። እነሱም ኢሉ (Iluu) ዘጠኝ፣ ኖኖ (Noonnoo) ስድስት፣ ጮራ (Cooraa) ስምንት፣ ሱጴ (Suphee) ሁለት፣ ዶረኒ (Doorannii) ሶስት፣ መቱ (Mattuu) አራት፣ ሁሩሙ (Hurrumuu) አምስት፣ ቡኖ (Buunnoo) ሰባት እና ቡሬ (Buree) አንድ መቀመጫ ነበሯቸው። በመዋቅራቸው ውስጥ ያሉ ነገዶችና አባላት ህግ አርቅቀው በገዳ ሥርዓት አካባቢወን ያስተዳድሩ ነበር። ከዚህ የምንረዳው የዶረኒ ወረዳም የራሱ የሆነ የአስተዳደር ሥርዓት እንደነበረው ነው። ይህም ሥርዓት የገዳ አስተዳደር ሥርዓት ነበር። በአሁኑ ጊዜ በያዩ ጉጠቴ ሀሮ ቀበሌ የሚገኘው ኦዳ ጎጊ (Odaa Gogii) በዚያን ዘመን ህግ የሚረቀቅበት ቦታ ነበር። በዚህ ህግ በሚረቀቅበት ቦታ የሚገኘውና ይህንን ህግ በመውሰድ ህዝቡን ያስተዳድር ከነበረው ከሶስቱ የዶረኒ ነገዶች መካከል ሶስት ሰዎች ይላኩ ነበር። እነሱም ከአጅላ ነገድ አንድ ሰው፣ ከባሪ ነገድ አንድ ሰውና ከአልዩ ነገድ አንድ ሰው ይሄዱና የረቀቀውን ህግ ወደ ወረዳው በማምጣት አካባቢውን ያስተዳድሩ ነበር (Mogos፣ 2011) ።

### 2.3.5 ዶረኒ ወረዳ እና የገዳ ሥርዓት ውድቀት

ከ1875 ዓ.ም በኋላ የገዳ ሥርዓትና አገዛዝ እንደ አጠቃላይ በኢሉባቦር ዞን ተግባራዊ እየሆነ አልነበረም። ምክንያቱም ሚኒሊክ በሀገር ደረጃ ማዕከላዊ አስተዳደርን የዘረጋበት ዘመን ስለነበር ነው። በዚህም ምክንያት የአካባቢያዊ አስተዳደር እና የእያንዳንዱ ማህበረሰብ የራሱን ባህላዊ መዋቅር ለማፍረስ የተገደደበት ጊዜ ነበር። በዶረኒ ወረዳም የገዳ ሥርዓትን በቦታው በመገኘት ወስዶ ማስተዳደር ቀረ። በመሆኑም የራሳቸውን አገዛዝ በመተው በወቅቱ በነበረው አህዳዊ አገዛዝ ለመተዳደር ጀመሩ (Mogos፣ 2011) ።

### 2.3.6 የዶረኒ ወረዳ የኦሮሞ ማህበረሰብ የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት

አንድ ህዝብ በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሥርዓቶች ውስጥ የራሱ የሆኑ የባህል እሴቶች አሉት። ከነዚህ እሴቶች መካከል አንዱ የጋብቻ ሥርዓት ነው። የዶረኒ ወረዳ የኦሮሞ ማህበረሰብ በርካታ የጋብቻ አይነቶች አሉት። ከነዚህ መካከል ነቀታ (Naqata)፣ አሴና (Aseenna)፣ ነቂ (Naqii) እና ቡቲ (Butii) ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ የጋብቻ አይነቶች እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል።

ነቀታ (Naqata) በቤተሰብ ስምምነት የሚከውን የጋብቻ አይነት ነው። ነቀታ (Naqata) የጋብቻ አይነት በአብዛኛው በሁለት ተጋቢዎች ቤተሰቦች ስምምነት ይፈጸማል። የሁለቱ ተጋቢዎች ቤተሰቦችም የዘር ሀርግ ተጠናንተው፣ ሽማግሌ ልከው፣ ተደግሶ በሰርግ የሚከወን የጋብቻ አይነት ነው። አሴና (Aseenna) ደግሞ በሁለቱ ተጋቢዎች መፈላለግና መፈቃቀር የሚፈጸም የጋብቻ አይነት ነው። ይህ የጋብቻ አይነት በተለያዩ ምክንያቶች ይከወናል። አንደኛ የልጅቷ ወላጆች ልጅቷን ለመዳር ፍቃደኛ ሳይሆኑ ሲቀሩ፣ ሁለተኛ አግቢው በነቀታ የጋብቻ አይነት ለማግባት ለጥሎሽ እና ለሌሎች ወጪዎች አቅም ሲያጣ፤ ሶስተኛው ደግሞ የሁለቱ ተጋቢዎች ቤተሰቦች የማይፈላለጉ ሲሆኑ እና ሁለቱ ተጋቢዎች የሚፈላለጉ ሲሆን፤ አራተኛው ምክንያት ሁለቱ ተጋቢዎች እየተፈላለጉ ልጅቷ በቤተሰብ አማካኝነት (በነቀታ የጋብቻ አይነት) ሌላ ሰው እንዲያገባት ሲታሰብ ይህ የጋብቻ አይነት ተግባራዊ ሊሆን ይችላል። በመሆኑም ሁለቱ ተጋቢዎች ተስማምተው ሴቷ ወደ ወንዱ ቤት በመሄድ ጋብቻ ትፈጽማለች። ከዚያም በኋላ የወንድ ቤተሰብ ሽምግልና ወደ ልጅቷ ቤተሰብ በመላክ እርቅ እንዲወርድ ይደረጋል። ሌላው የጋብቻ አይነት ነቂ (Naqii) ሲሆን ይህ የጋብቻ አይነት በወጣቱ እና በቤተሰቦቹ ስምምነት ብቻ የሚከዎን ነው። ሽማግሌዎች በጠዋት ከወጣትዋ ቤተሰብ በር ላይ በመቀመጥ የልጅቷ ቤተሰብ በር ሲከፍቱ «የእገሌ ልጅ ልጃችሁን እንደወደዳት እና ሊያገባት እንደሚፈልግ ልኮን ነው» በማለት ሲናገሩ በባህሉ መሰረት ነቂ (Naqii) የተላከባትን ልጃገረድ መከልከል ሽማግሌዎች ይረግማሉ፤ እርግማኑ ደግሞ ለቤተሰቡም ሆነ ለወጣቷ ጥሩ አይደለም ተብሎ ስለሚታመን የልጅቷ ቤተሰቦች እርግማን በመፍራት የሚፈጽሙት የጋብቻ አይነት ነው። ነገር ግን አሁን አሁን ይህ የጋብቻ አይነት ኋላ ቀር ልማድ ነው በሚል እሳቤ ሙሉ በሙሉ ቀርቷል። ሌላው የጋብቻ አይነት ቡቲ (Butii) ነው። ይህ የጋብቻ አይነት ከሴት ልጅና ቤተሰቦቿ ፈቃድ ወጪ የሚከወን የጋብቻ አይነት ነው። በዚህ የጋብቻ አይነት ወጣቷ ገበያ፣ የወንዝ ውሃ ለመቅዳት እንዲሁም እንጨት ለቀማ ስትሄድ በመጠበቅ በጉልበት ጠልፈው በመውሰድ የሚፈጸም የጋብቻ አይነት ነው። በአሁኑ ወቅት ግን ከህግ አቅጣጫ ሲታይ አግባብ አለመሆኑ ታውቆ የጋብቻው አይነት ሙሉ በሙሉ ቀርቷል (Mogos፣ 2011)።

# ምዕራፍ ሶስት

# 3. የጥናቱ ዘዴና አካሄድ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ዘዴ፣ የንሞና አመራረጥ ስልት፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች እና የመረጃው አደረጃጀትና የትንተናው ዘዴ ቀርበዋል።

## 3.1 የጥናቱ ዘዴ (Reseach Method)

ይህ ጥናት በኢ.ሉ አባቦር ዞን ዶረኒ ወረዳ የኦሮሞ ማህበረሰብ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች ስለሚደረገው ሥርዓት፣ ለማህበረሰቡ የሚሰጠዉን ማህበራዊና ስነልቦናዊ ፋይዳ እንዲሁም ሥርዓቱ አሁን ስላለበት ሁኔታ የሚያሳይ ነው ። ጥናቱ ደግሞ በአይነታዊ ስነ ዘዴ (Qualitative Methodology) የሚካሄድ ነው፡፡ በመሆኑም የምርምሩን ዓላማ ከግብ ለማድረግ ገላጭ (descriptive ) የምርምር ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል። ይህንን አስመልክቶ Gray (2018) ገላጭ ጥናት በአንድ አካባቢ ነባራዊ ሁኔታ ያተኮረ መረጃን ከተመረጡ ንሞናዎች ወይም ከሁሉም የጥናቱ አካላይ በሚፈለገው አይነት ለመሰብሰብ የሚያግዝ ነው። በማለት አብራርቷል። ከዚህ በተጨማሪ ገላጭ የጥናት ዘዴ ከሁለት በላይ የሆኑ ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት በአይነታዊ የጥናት መስክ ለሚሰሩ ጥናቶች ገላጭ ጥናት ዘዴን መጠቀም የተሰበሰበዉን መረጃ በስፋት ዘርዝሮ ለማቅረብ ምቹ በመሆኑ ነው።

## 3.2 የንሞና አመራረጥ ስልት

አንድ ተመራማሪ ጥናት ለማካሄድ በሚያስብበት ወቅት ከችግሩ ባልተለየ ሁኔታ ሊያውቃቸው የሚገባቸው ጉዳዮች ጥናቱ በማን ላይ ይካሄዳል? የት ይካሄዳል? የሚሉትን ጉዳዮች ጭምር ናቸው። የጥናቱ ተሳታፊዎች ተለይተውና ተወስነው ካልታወቁ የችግሩን መፍትሄ ለመሻትም ሆነ ራሱን ምርምሩን ለማካሄድ አስቸጋሪ ነው። በመሆኑም አጥኚዋ የጥናቱን ቦታ በዓላማ ተኮር የንሞና አመራረጥ ዘዴ የመረጠች ሲሆን የመረጃ አቀባዮች ንሞና ደግሞ በዓላማ ተኮር የንሞና አመራረጥ ዘዴ እና የጓድ ጥቆማን ተጠቅማለች።

### 3.2.1 የቦታ ንሞና አመራረጥ

ይህ ጥናት የሚካሄደው በኢ.ሉአባቦራ ዞን በዶረኒ ወረዳ ካሉት አስራ ሁለት ቀበሌዎች መካከል አራቱን በመምረጥ እንደሆነ በጥናቱ ወሰን ተገልጿል። አጥኝዋ የመረጃ መሰብሰቢያ ቦታዎችን በአላማ ተኮር የንሞና አመራረጥ ዘዴ መርጣለች። ምክንያቱም ይህ

ዘዴ በጥናቱ ብቻ የሚካተቱ መረጃዎችን ለመምረጥ አመቺ ከመሆኑ የተነሳ ነው። ይህንን አስመልክቶ Etikan እና Musa (2016) የሚከተለውን ጠቅሰዋል። "አላማ ተኮር የንሞና አመራረጥ ዘዴ ሳቢ ወይም ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን አላማን መሰረት አድርጎ ከሌሎች አይነት ነጥሎ የመውሰድ ወይም የመምረጥ ዘዴ ነው።" በመሆኑም አጥኝዋ ይህ ባህላዊ ሥርዓት በዶረኒ ወረዳ ካሉ አስራ ሁለት ቀበሌዎች በአላማ ተኮር የንሞና አመራረጥ ዘዴ አራት ቀበሌዎች ማለትም ኤሌሞ፣ ፋኒ፣ ወይራና ቦሶ ቀበሌዎችን ልትመረጥ ችላለች። ምክንያቱም በእነዚህ ቀበሌዎች የሚኖረው ማህበረሰብ ከሌሎቹ ቀበሌዎች አንጻር ሲታይ በአብዛኛው የኦሮሞ ማህበረሰብ በመሆኑ መረጃ አቀባዮችን እንደልብ እንደምታገኝ እርግጠኛ በመሆኗ ነው። እንዲሁም ሁሉንም የጥናት አካላይ በመረጃ ምንጭነት መጠቀም ከጊዜ፣ ገንዘብ እና ጉልበት አንጻር አስቸጋሪ በመሆኑ ነው።

### 3.2.2 የመረጃ አቀባዮች ንሞና አመራረጥ

አጥኚዋ ጥናቱን ከግብ ለማድረስ ወደ ኢሉአባቦራ ዞን ዶረኒ ወረዳ በመሄድ በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በቂ እውቀት ካላቸው ግለሰቦች እና ከባህልናቱሪዝም ባለሙያዎች ጋር በመሆን ባደረገችው ውይይት ድንግልናቸውን ጠበቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት በአሁኑ ሰዓት ሙሉ በሙሉ የቀረ መሆኑን ተረድታለች። በመሆኑም መረጃዎችን በምልከታ የመረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴ ለመጠቀም የማይቻልበት ሁኔታ መኖሩን ተገንዝባለች። ስለዚህ ባህላዊ ሥርዓቱን ለማጥናት የሚጠቅሙ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የባህሉን ባለቤቶችና በነቀታ (Naqata) የጋብቻ ሥርዓት ጋብቻቸውን የፈጸሙ ግልሰቦችን በመረጃ ሰጪነት መርጣቸዋለች። በመሆኑም ከየቀቤዎቹ ሁለት ሁለት መረጃ አቀባዮችን በታላሚ ንሞና አመራረጥ (purposive sampling) ዘዴ ተመርጠዋል። ምክንያቱም የጥናቱ መረጃ አቀባዮች የብሂረሰቡን ባህል አጠቃላይ ሁኔታ ጠንቅቀው ያውቃሉ ተብለው የተመረጡ የባህሉ ባለቤቶች እና በሥርዓቱ መሰረት ጋብቻቸውን የፈጸሙ ጥንዶች በመሆናቸው ነው። በተጨማሪም ለዚህ ጥናት የጓድ ጥቆማ (Snow ball sampling) ተግባራዊ ሆኗል። ይህ ዘዴ በመጀመሪያ አጥኚዋ በታላሚ ንሞና ዘዴ የተወሰኑ መረጃ አቀባዮችን ከመረጠች በኋላ እነዚህ የተመረጡ መረጃ አቀባዮች ሌሎች መረጃ አቀባዮችን እንዲጠቁሙ የሚደረግበት ዘዴ ነው። ይንን ሀሳብ አስመልክቶ Cresswell እና David (2017) እንዲህ ይገልጹታል።"የጓድ ጥቆማ (Snow ball sampling) አጥኝዋ አንድን መረጃ አቀባይ ስታገኝ መረጃ አቀባዩ ስለ ርዕሰ ጉዳዩ እውቀት ያላቸውን ሌሎች መረጃ አቀባዮች እንዲጠቁማት

የሚደረግበት ስልት ነው።" ይህንኑ መሠረት በማድረግ በዚህ ጥናት ውስጥ በታላሚ ንሞና አመራረጥ ዘዴ የተመረጡ መረጃ አቀባዮች በሥርዓቱ ጋብቻቸውን የፈጸሙና ስለባህሉ ጠንቅቀው የሚያውቁ ሌሎች መረጃ አቀባዮችን እንዲጠቁሙ ተደርጓል። ምክንያቱም የተመረጡ መረጃ አቀባዮች ከአጥኚዋ በበለጠ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ማን ከማን የተሻለ እውቀት እንዳለው በማወቃቸው ነው።

መረጃው በአብዛኛው የተሰበሰበው ከመስክ ሲሆን ተዛማጅነት ያላቸው መረጃዎች (ተዛማጅ ጥናትና ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት) ከቤተ መጽሀፍትና ከድረገጽ ተካሂድዋል። መረጃ አቀባዮች ስለባህሉ ጠንቅቀው ያውቃሉ የተባሉና በሥርዓቱ ጋብቻቸውን የፈጸሙ መረጃ አቀባዮች ከአራቱ ቀበሌዎች ከእያንዳንዳቸው አንድ ወንድና አንድ ሴት በድምሩ ስምንት ቁልፍ መረጃ አቀባዮች በታላሚ ንሞና አመራረጥ (purposive sampling) ዘዴ የተመረጡ ሲሆን የጾታ ስብጥሩ ያስፈለገበት ምክንያት በሥርዓቱ ዙሪያ ከሁለቱም ጾታዎች ያለውን አንድምታ ለማመዛዘን ሲባል ነው። ነገር ግን የቀሩት ሀያዎቹ መረጃ አቀባዮች (ከኤሌሞ ዘጠኝ፣ ከወይራ ሁለት፣ ከቦሎ አራትና ከፋኒ ሶስት) እንዲሁም (ከቦንዳዎ አንድና ከበዴሳ አንድ) በጓድ ጥቆማ (Snow ball sampling) አማካኝነት የተካተቱ በመሆናቸው ከሁሉም ቀበሌዎች የተመረጡ መረጃ አቀባዮች ቁጥር ሆነ የጾታ ስብጥር ተመጣጣኝ ማድረግ አልተቻለም። በተጨማሪም ከነዚህ ሀያ መረጃ አቀባዮች መካከል ሁለቱ ከተመረጡት ቀበሌዎች ውጪ ባላቸው ዕወቀት መሰረት ለመረጃ ምንጭነት ተካተዋል። ከዚህም በተጨማሪ አጥኚዋ በቡድን ተኮር ውይይት ወቅት የፆታና የእድሜ ልዩነት የሚያመጡትን የመረጃ ልዩነት ለማካተትና የጥናቱ ርዕስ ከወሲብ ጋር የተገናኘ በመሆኑ በነጻነት መናገር እንዲችሉ ሲባል ከሁለቱም ፆታዎች በተለያየ የእድሜ ክልል ያሉ መረጃ አቀባዮችን በዓላማ ተኮር የአመራረጥ ዘዴ መልምላለች። በመሆኑም በጥናቱ የተሳተፉ መረጃ አቀባዮች እድሜ ዝቅተኛው 35 ሲሆን ከፍተኛው 86 ነው።

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

እንደጥናቶች ዓይነት መረጃ መስብሰቢያ ዘዴዎች ወይም ቴክኒኮች የተለያዩ ናቸው። ለዚህ ጥናት የተመረጡ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ቃለ መጠይቅ፣ ቡድን ተኮር ውይይት እና ሰነድ ፍተሻ ናቸው። በቃለ መጠይቅ መረጃ በማሰባሰቡ ሂደት በተናጠል ከሚደረገው ቃለ መጠይቅ በተጨማሪ የቡድን ውይይት በመጠቀም የተሟላ መረጃ ለማግኘት ጥረት ተደርጓል።

### 3.3.1 ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ ጠያቂና ተጠያቂ ፊት ለፊት ተቀምጠው የሚያደርጉት የሀሳብ ልውውጥ በመሆኑ ጠያቂው የመላሹን አጠቃላይ እንቅስቃሴ በመከታተል መረጃን የሚያገኝበት መንገድ ነው። ግሬይ ይህንን ሀሳብ "ቃለ መጠይቅ በአጥኚው እና በመረጃ አቀባዮቹ መካከል በቃል የሚካሄድ መረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴ ነው። በቃለ መጠይቅ ጠያቂው የተመራማሪ ሚና ሲኖረው አብዛኛውን ጊዜ አጥኚው ቀደም ተከተል የጠበቁ ጥያቄዎችን በማንሳት መረጃዎችን ይሰበስባል" (Gray, 2018) በማለት ያጠናክረዋል። ቃለ መጠይቅ አይነቶቹ የተለያዩ እና አጠቃቀማቸውም አንድ አይነት አለመሆኑን ግሬይ ይጠቅሳል። ስድስቱ የቃለ መጠይቅ ቴክኒኮች ሲል ግሬይ የሚጠቅሳቸው ዝግ ቃለ መጠይቅ (structured interview)፣ ከፊል ነጻ ቃለ መጠይቅ (semi-structured interview)፣ ቀጥተኛ ያልሆነ ቃለ መጠይቅ (non-directive interview)፣ ተተኳሪ ቃለ መጠይቅ (focus interview) ፣ ኢመደበኛ ቃለ መጠይቅ (informal conversational interview) እና ጥያቄ ተኮር ቃለ መጠይቅ (problem focus interview) ናቸው (Gray ፣2018)። በዚህ ጥናት ቃለ መጠይቅ አገልግሎት ላይ የዋለው ስለ ብሄረሰቡ አጠቃለይ ታሪክና ድንግልናቸውን ጠብቀው ለጋብቻ ለበቁ ሴቶች የሚደረገውን ሥርዓት፣ ባህላዊ ሥርዓቱ ለማህበረሰቡ ያለው ፋይዳና ሥርዓቱ አሁን ስላለበት ሁኔታ ጠንቅቀው ያውቃሉ ተብለው በአግባቡ ከተመረጡ መረጃ አቀባዮች መረጃን ለመሰብሰብ ነው። በመሆኑም ስለ ዶረኒ ወራዳ አጠቃላይ ሁኔታ ያውቃሉ ተብለው ከሚታመንባቸው ከፊል ነጻ ቃለ መጠይቅ እና ቀጥተኛ ያልሆነ የቃለ መጠይቅ አይነቶች በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል። ምክንያቱም ከፊል ነጻ ቃለ መጠይቅ (semi-structured interview) አጥኚዋ የምትጠይቃቸውን ጥያቄዎች በከፊል ተዘጋጅታባቸው እና አስባባቸው የምታቀርብበት ነው። ጥያቄዎቹ በሚቀርቡበት ወቅት ከመረጃ አቀባዮቿ የሚመጡ አዳዲስ ሀሳቦች ካሉ ለመቀበል በከፊል ዝግጁ የምትሆንበት እና ተጨማሪ ጥያቄዎችንም ለመጠየቅ የምትችልበትም ነው። በተጨማሪም አጥኚዋ በቅደም ተከተል ያዘጋጀቻቸውን ጥያቄዎች አፋልሳ በሚመቻት መንገድ ልታቀርብ ትችላለች። ቀጥተኛ ያልሆነ ቃለ-መጠይቅ (non-directive interview) ደግሞ አጥኚዋ የምትጠይቃቸውን ሰዎች ከማግኘቷ በፊት ጥቂት ጥያቄዎችን ብቻ በመያዝ ከምልልሱ በርካታ ጥያቄዎችን የምታመነጭበት እና የምትጠይቅበት ስልት ነው። በተጨማሪም ሁለቱ የቃለ መጠይቅ

ቴክኒኮች (ከፊልነጻ ቃለ መጠይቅ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ቃለ-መጠይቅ) አይነታዊ መረጃን ለመሰብሰብ ተመራጭ ናቸው (Gray ፣2018) ።

### 3.3.2 ቡድን ተኮር ውይይት

ይህ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በቃለ መጠይቅ ያልተሟሉ መረጃዎችን ለማሟላት ፣ እርስበርስ የሚፋለሱትን ሃሳቦች በአግባቡ በመለየት ትክክለኛውን መረጃ ለማረጋገጥ የሚያስችል አይነተኛ ዘዴ በመሆኑ ጥቅም ላይ ውሏል። በመሆኑም በተደረጉት ቡድን ተኮር ውይይቶች የአካባቢውን ታሪክ ያውቃሉ ተብለው የተመሰከረላቸው የባህሉ ባለቤቶችና በባህሉ መሰረት ጋብቻቸውን የፈጸሙ ባልና ሚስቶች ለውይይት ተመርጠዋል። በውይይቱ በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን ትክክለኝነት ለማረጋገጥና አዳዲስ መረጃዎችን ለማግኘት የመወያያ ጥያቄዎች በማዘጋጀት የተቀናጀ መረጃ ለመሰብሰብ አስችሏል። ያለው (2009) በተተኳሪ ቡድን ውይይት እስከ 12 ሰዎችን ማሳተፍ እንደሚቻል ሲገልጽ Gray (2018) Kruegerን (1994) ዋቢ በማድረግ አባላቱ ከ6-12 ቢሆኑ የተሻለ እንደሚሆን ያስረዳል። በዚህ መሰረት ለዚህ ጥናት ቡድን ተኮር ውይይት የተደረገው ከአራቱ ቀበሌዎች የተውጣጡ መረጃ ሰጪዎችን በሶስት ቡድን በማደራጀት ነው። በመሆኑን በመጀመሪያው ቡድን ተኮር ውይይት ስለ ብሄረሰቡ ባህል ጠንቅቀው ያውቃሉ ከተባሉ የባህሉ ባለቤቶችና በባህሉ መሰረት ጋብቻቸውን የፈጸሙ ባልና ሚስቶች ሲሆን አራት ወንድና አምስት ሴት በአጠቃላይ ዘጠኝ አባላትን ያቀፈ የቡድን ውይይት ተካሂዷል። በተጨማሪም ርዕሰ ጉዳዩ ከድንግልና ጉዳይ ጋር የተያያዘና ወሲብ ነክ በመሆኑ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በነጻነት ሀሳባቸው በመግለጽ ይህን ዘዴ የተሳካ ለማድረግ በጾታ በመከፋፈል ስምንት ስምንት አባላት የያዙና ሁለት ቡድን ተኮር ውይይቶች ተደርገዋል። በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የአጥኘዋ ተግባር ለውይይት የተዘጋጁ ጥያቄዎችን በማቅረብ የውይይቱ አባላት ከአላማው እነዳያፈነግጡ መስመር ማስያዝ ፣ግራ የገባቸውን ጥያቄዎች ግልጽ ማድረግና በውይይቱ ሁሉም አባላት ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ነበር።

### 3.3.3 ሰነድ ፍተሻ

ይህ የመረጃ መሰበሰቢያ ዘዴ የጥናቱን ርዕስ መሰርት በማድረግ በቤተ መጽሀፍትና በተለያዩ የመረጃ ማከማቻዎች የሚገኙ (በጽሁፍ፣ በድምጽና በምስል) የተከማቹ መረጃዎችን በመፈተሽ የትንተና አካል የሚሆኑበት ነው። ይህንን ሀሳብ ያለው (2009) ሲገልጸው ‹‹በተለያዩ የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን ትክክለኛነት

ለማረጋጥና ያልተዳሰሱ ጉዳዮች ካሉ ከልዩ ልዩ የፅሁፍ መረጃዎችና ከተለያዩ ሰነዶች መረጃዎችን በማፈላለግ ትንታኔ የሚሰጥበት ስልት ነው።" ይላል።

በመሆኑም የተለያዩ የንድፈ የንድፈ ሃሳብና የስነ ዘዴ መጻሕፍት በሰነድ ፍተሻ የተገኙ ሲሆን በተጨማሪም በዶረኒ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አማካኝነት ተቀርጸው የተሰነዱ ሁለት ቪዲዮዎችና ለባህል ፌስቲቫል የተዘጋጀ "ልዩ እትም" አንድ መጽሄት በሰነድ ፍተሻ ወቅት ተገኝተዋል። አንዱ ቪዲዮና መጽሄቱ የሰርግ ሥርዓት ላይ የሚያተኩሩ ሲሆኑ አንዱ ቪድዮ ደግሞ የሴቶች ባህላዊ ጭፈራ (Sirba Durba) ላይ ያተኩራል። አጥኝዋ እነዚህን መረጃዎች የትንተናው አካል በማድረግ ተጠቅማቸዋለች። የተገኙት መረጃዎች ምንም አይነት የእርማት ተግባር ያለተደረገባቸው ናቸው።

## 3.4 የመረጃ አደረጃጀትና መተንተኛ ዘዴ

### 3.4.1 የመረጃ አደረጃጀት

መረጃ ማደራጀት ከመስክ የተገኙ መረጃዎችን ለትንታኔ በሚመቹ ሁኔታ መድቦ ማስቀመጥን ይመለከታል። በመሆኑም አጥኚዋ የመጀመሪያ ተግባሯ ያደረገችው በቪዲዮ ካሜራና በመቅረጸ ድምጽ የሰበሰበቻቸውን መረጃዎች ወደ ጽሁፍ መቀየር ነበር። መረጃዎቹ ወደ ጽሁፍ ሲቀየሩ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት የሌላቸውን መረጃዎች በማስወገድ፣ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሆነው ያልተሟሉ መረጃዎችን በድጋሚ ከመርጃ አቀባዮች በመጠየቅ በማሟላትና የተሟሉትን ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር የበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት በተመለከተ በኮድ ‹‹ሀ››፣ ሥርዓት ከበራው ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ፋይዳ በኮድ ‹‹ለ›› እንዲሁም ለሥርዓተ ከበራው መጥፋት በምክንያትነት የሚነሱ ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ የሚያመለክቱትን በኮድ ‹‹ሐ›› በመከፋፈል አደራጅታለች።

### 3.4.2 የመረጃ ትንተና

አጥኚዋ ከላይ በተዘረዘሩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በመጠቀም ማለትም በቃለ መጠየቅ፣ በቡድን ተኮር ውይይትና በመዛግብት ፍተሻ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገውን ሥርዓት በተመለከተ መረጃዎችን ሰብስባለች። የወረዳው የባህልና ቱሪዝም ሰራተኛ ከሆኑት ከአቶ ሞገስ ከበደ ጋር ከተደረገው ቃለ መጠየቅ በስተቀር ሁሉም መረጃዎች የተሰበሰቡት በተጠኚዉ ብሂረሰብ (በኦሮምኛ) ቋንቋ ነው። በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት የተሰበሰቡት መረጃዎች እንዲሁም በሰነድ ፍተሻ ወቅት በቪዲዮ

የተገኙ መረጃዎች ለጥናት የሚሆኑት ተመርጠው ወደ ጽሁፍ ከተቀየሩ በኋላ ከኦሮምኛ ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉመዋል። አጥኚዋ ቋንቋውን የምትችል በመሆኗ የትርጉም ስራውን እራሷ ሰርታዋለች። ነገር ግን አንዳንድ ለመተርጎም አስቸጋሪ የሆኑትን ሀሳቦች ሌሎች ሰዎች በትርጉም እንዲያግዟት አድርጋለች።

ለማ (1999) Fineን (1984) ዋቢ በማድረግ እንዳመለከቱት የመደበኛ አቻዊነት እና የፍጹም አቻዊነት ትርጉም ስልቶች ለፎክሎር ትርጉም የተለየ ጠቀሜታ አላቸው። ከነዚህ የትርጉም ስልቶች ለዚህ ጥናት የሚስማማው የመደበኛ አቻዊነት ትርጉም ስልት በመሆኑ መረጃዎቹ የተተረጎሙት በዚህ የትርጉም ስልት ነው።

በመሆኑም ይህን ጥናት ለአንባቢያን በተብራራና ግልጽ በሆነ መረጃ አዘል መልዕክት ለማስተላለፍ አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ተመራጭ ሆኗል። ምክንያቱም የሚጠናውን ጉዳይ በስፋትና በተለያየ መልኩ በዝርዝር ለመተንተን አይነታዊ ዘዴ ምቹ በመሆኑ ነው። በተጨማሪም አይነታዊ ምርምር ተመራማሪዋ አንድን ችግር ትወስድና ውስን የሆኑ የችግሩን ባለቤቶች በመምረጥ ያነሳችውን ችግር በጥልቀትና በስፋት ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመዳሰስ መረጃዎች የሚተነተንበት ስልት በመሆኑ ነው። ለዚህ ጥናት የተደራጁ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት እና ለውጡ ምን እንደሚመስል ማሳየት በሚል አላማ በዋነኝነት በምርምሩ ይዘት በተነሳው መላምት ወይም የምርምርን ጥያቄ መሰረት በማድረግ የተገኘውን ውጤት ለግልጽና በተገቢው ቋንቋ ለማቅረብ ተሞክሯል።

# ምዕራፍ አራት

# 4. የመረጃ ትንተና

## 4.1 ድንግልናቸውን ጠብቀው ለጋብቻ ለበቁ ሴቶች የሚደረግ ሥርዓት ትንተና

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በኢሉ አባቦር ዞን፣ በዶረኒ ወረዳ በሚኖረዉ የኦሮሞ ማህበረሰብ በነቀታ (Naqata) የሰርግ ሥርዓት ድንግልናቸውን ጠብቀው ለጋብቻ ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት ላይ ነው። በመሆኑም በዚህ ክፍል በቃለ መጠይቅ፣ በቡድን ውይይትና በመዛግብት ፍትሻ የተሰበሰቡ መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል።

የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር እንደሚያመለክተው አንድ ግለሰብ ከነበረበት ማህበራዊ ደረጃ ወደ ቀጣዩ ደረጃ የሚሸጋገርባቸው ሁነቶች መኖራቸውን ነው። ከሽግግሮቹ አንዱ ለአቅመ አዳም ወይም ለአቅመ ሄዋን መድረስ ነው። በዚህም መሰረት አንድ ሰው ለአቅመ አዳም ወይም ሄይዋን ሲደረስ ጋብቻ እንዲፈጽም በማህበረሰቡ ይጠበቃል። ጋብቻ የማህበራዊ ሕይወት መሠረት እና የትውልድ ማስቀጠያ ነው። ጋብቻ በተቃራኒ ፆታ መካከል ለቤተሰብ ምሥረታ እና ለሌሎችም ጠቀሜታዎች ሲባል የሚመሰረት ተቋም ነው።

በጋብቻ እና ቤተሰብ ጉዳዮች ላይ ምርምር ካደረጉት ምሁራን ውስጥ Olson (2001) ጋብቻን እንዲህ ይገልጻል። "ጋብቻ በተፈጥሮው ፈርጀ ብዙ ተቋም ነው።ጋብቻ በሁለት ሰዎች መካከል ሕጋዊ መሠረት ያለውና በመተማመን የሚመሰረት ሲሆን፤ ወሲባዊ ስሜትን ለመካፈልና ለሌሎችም የተለያዩ ኢኮኖያዊ ጥቅሞች በጋራ የሚመራበት ተቋም መሆኑን ነው።" በመሆኑም ጋብቻ ሰዎች በማህበራዊ ህይወታቸው ተቀባይነት እንዲኖራቸውና ሥርዓት ያለው ሕይወት እንዲኖሩ የሚያደርግ ነው።

ጋብቻ በኦሮሞ ብሄረሰብ ዘንድ "ጋኢላ" የሚል መጠሪያ አለው፡፡ በኢሉ አባቦር ዞን፣ በዶረኒ ወረዳ የሚኖረዉ የኦሮሞ ማህበረሰብ ባህሉን ጠብቆ ከቆየባቸውና የህይወት ፍልስፍናውን ከሚገልጽባቸው ልማዳዊ ድርጊቶች አንዱ ጋብቻ ሲሆን፤ ማህበሰቡ ለጋብቻ ትልቅ ቦታና አክብሮት አለው። አቶ ኢታና ማሞ ማህበረሰቡ ስለ ጋብቻ ያለውን አስተሳሰብ እንዲህ በማለት ይገልጹታል።

ጋብቻ በሰው ልጅ ህይወት ከፍተኛ ቦታ አለው። ጋብቻ የሰው ልጅ ዘሩን የሚያስቀጥልበት ዋና መንገድ በመሆኑ ማህበረሰቡ እንደ ቅዱስ ዘር ማስቀጠያ ተቋም ያየዋል። በመሆኑም ማህበረሰቡ ለጋብቻ ከሚሰጠው ዋጋ የተነሳም፤ ልጁን ለጋብቻ ዕለት ከመድረሱ/ሷ በፊት የትዳር አጋር ቅደመ ጥናት ያደርጋል። ምክንያቱም ማህበረሰቡ ልጅን አሳድጎ ለጋብቻ ማብቃት እንደ ትልቅ ስኬት ስለሚወስድ ነው (ቃለ መጠይቅ በ5/11/2011ዓ. ም.) ።

በኢሉ አባቦር ዞን፣ በዶረኒ ወረዳ የሚኖረዉ የኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ በርካታ የጋብቻ አይነቶች አሉ። ከነዚህ መካከል ነቀታ (Naqata)፣ አሴና (Aseenna)፣ቡቲ (Butii) እና ነቂ (Naqi) ተጠቃሾች ናቸው። ከነዚህ የጋብቻ አይነቶች ውስጥ ትልቅ የአከባበር ሥርዓት ያለው በነቀታ (Naqata) የሚደረገው የጋብቻ አይነት ነው። በመሆኑም የዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ የሆነው ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት በነቀታ (Naqata) የጋብቻ አይነት ይከወናል፡፡

ባህሩ (2014) ከፍተኛ የአማርኛ መዝገበ ቃላት በተሰኘው መጽሀፍ ፣ “ድንግል” የሚለውን ቃል ወሲባዊ ተሞክሮ የሌላት ሴት ወይም የሌለው ወንድ በማለት ይበይነዋል። በአብዛኛው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ዘንድ አንዲት ሴት ልጅ ድንግልናዋን ጠብቃ ለትዳር መብቃት እንዳለባት ይታመናል። እንዲሁም Hajru (2013) በጥናቱ በኮሶቮ ማህበረሰብ ዘንድ እስከ ጋብቻ ዕለት ድረስ ድንግል ሆኖ መቆየት ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው መሆኑን ገልጿል። የዶረኒ ኦሮሞ ማህበረሰብ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለጋብቻ ለሚበቁ ሴቶች ቀደም ባለው ጊዜ ከፍተኛ ቦታ (አክብሮት) ይሰጣቸው ነበር። ለምሳሌ ማህበረሰቡ ድንግልናን ጠብቆ ለጋብቻ መብቃትን አስመልክቶ የነበረውን ፍልስፍና በተመለከተ ወ/ሮ ፋናዬ ወርቂ እንዲህ ይገልጹታል።

> በማህሰቡ ዘንድ ድንግልናን ጠብቆ ለትዳር መብቃት የጨዋነትና የታማኝነት መገለጫ ነበር። በመሆኑም አንዲት ሴት ልጅ ድንግልናዋን ጠብቃ ለትዳር ከበቃች፣ ጨዋ፣ ታማኝ እና ጠንቃቃ መሆኗን ያሳያል። እንዲሁም ለቤተሰቦቿ፣ ለባሏ ቤተሰቦች እና ለማህበረሰቡ ክብር የምትጨነቅ መሆኗን ያመለክት ነበር (ቃለ መጠይቅ በ7/11/2011ዓ. ም.) ።

ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው አንዲት ሴት ልጅ ድንግልናዋን ጠብቃ ለትዳር ስትበቃ ከራሷ ክብር አልፋ የቤተሰቦቿን ብሎም የማህበረሰቡን ባህል ማክበሯን ነው።
ይህንኑ መሰረት በማድረግ በነቀታ (Naqata) የጋብቻ አይነት በማህበሰቡ ዘንድ ይፈጸም የነበረውን ሥርዓት ከድንግልና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን በመለየት ቅድመ ጋብቻ፣ ጊዜ ጋብቻና ድህረ ጋብቻ በሚል ዋና ዋና ምድቦች ለይተን እንቃኛለን።

### 4.1.1 ቅድመ ጋብቻ

#### 4.1.1.1 የትዳር አጋር መረጣ

በነቀታ (Naqata) የጋብቻ አይነት አንድ ወጣት ትዳር ለመመስረት እድሜው ሲደርስ ስለ ወጣቱ የትዳር ሁኔታ ወላጆቹ ከቤተ ዘመድ ጋር ይወያያሉ። ከዚያም ወላጆቹም የእሱን ለትዳር መድረስ ካመኑበት «ልጃችን የማንን ልጅ ያግባ?» የሚለውን ጥያቄ በማንሳት ይወያያሉ። የዚህን ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት ከቤተዘመድ ጋር መወያየት የግድ ይሆናል። ቤተሰቡ ለጋብቻ የመረጣትን ልጅ በልጅቷ ቤተሰብና በልጁ ቤተሰብ መካከል ዝምድና አለመኖሩን፣ ውበቷን፣ የወላድ ዘር መሆኗን፣ ሙያዋንና ባህል አክባሪነቷን ይፈትሻሉ። እንደ ማህበረሰቡ ባህል አክባሪ ከሚመዘንባቸው ጉዳዮች የሴት ልጅ የጨዋነት ተምሳሌት የሆነውን ድንግልናዋን ጠብቃ ወይም የሴትነት ማዕረጓን የጠበቀች መሆኗም እንደ አንድ መስፈርት በመውሰድ ወላጆች ስለ ልጅቷ ያጣሩ ነበር።ይህንን ሀሳብ በተመለከተ አቶ ታደሰ ሁንዴ እንዲህ ይገልጹታል፡፡

> እስከ 1980ዎቹ አጋማሽ ድረስ አንድ ወንድ ልጅ ለጋብቻ መድረሱን የሚመረምሩት ቤተ ተዘመዶች ነበሩ። ማለትም አባት፣ እናት፣ አጎቶች እና አክስቶች ናቸዉ። ወንድ ልጅ ለትዳር መድረሱን ቤተሰቦቹ መርምረው ከተረዱ በኋላ፤ ለልጃቸዉ ሚስት የምትሆን ልጃገረድ ማፈላለግ ይጀምራሉ። ለልጃቸዉ የትዳር አጋር ትሆናለች ያሏትን ልጃገረድ የቤተሰብ ሁኔታ እና የአያት ቅድመ አያት ዘር ሀረግ ያጠናሉ። ዘሯን ካጠኑ በኋላ በአካባቢ ሰዎች አማካኝነት ወደ ልጅቷ ቤተሰብ ቤት በመሄድ፣ የልጅቷን ባህል አክባሪነት (ጨዋነት) ወይም እራሷን በድንግልና ጠብቃ ለትዳር በቅታ እራሷን፣ ወላጆቿን ብሎም የትዳር አጋሯን ማኩራት ትችላለች? የሚለውን በጥልቀትና በቅርበት ያጠኑ ነበር (ቃለ መጠይቅ በ12/11/2011ዓ. ም.) ።

በ5/11/2011 በተደረገ ቡድን ተኮር ውይይት ለማወቅ እንደተቻለው ማህበረሰቡ ዘንድ ወላጆች ወንድ ልጃቸውን ትዳር እንዲመሰርት ሲወስኑ መጀመሪያ ልጃቸው የማንን ልጅ ማግባት እንዳለበት (በዘር፣ በሀብት፣ በጎሳ) ብሎም ከጨዋ ተወለዳ ጨዋ ያሳደጋት ከኛ ጋር በጋብቻ ስትተሳሰርም በጨዋነቷ የኛን ቤተሰብ ማስጠራት የምትችለው የማን ልጅ ናት? የሚሉቱን ጥያቄዎች በማንሳት ከቤተሰብ ጋር በመወያየት ይወስኑ ነበር። ሽምግልና ከመላካቸው በፊት ስለልጅቷ ጭዋነት (ድንግልናዋን በመጠበቅ ደረጃ በሀሜት እንኳ ስሟ ያልተነሳ መሆኗን) እና ባህል አክባሪነት ከጎረቤት ያጣሩ ነበር።



ፎቶ 1. አቶ ታደሰ ሁንዴና ባለቤታቸው ወ/ሮ አባይነሽ መርጋ ቃለ መጠይቅ ሲደረግላቸው

ከላይ ከቀረቡት ማስረጃዎች የምንረዳው ነቀታ (Naqata) የጋብቻ ሥርዓት የሚፈጸመው ወላጆች በወሰኑት ወይም በመረጡት ሲሆን በወላጆች ምርጫም የዘር ሀረግ እስከ ቅድመ አያት እንደሚጠና እንዲሁም የልጅቷን ማንነትም (ጨዋነቷን፣ ባህል አክባሪነቷን፣ የአስተዳደግ ሁኔታዋ) በአጠቃላይ ሙሉ ስብዕናዋን በተለያየ መልኩ እንደሚያጠኑ ነው። ወላጆች ሞያዋ፣ መልኳ ይበሉ እንጂ ስብዕናዋን ሲያጠኑ በተለይ ከማንም ወንድ ጋር ግንኙነት የሌላት መሆኗ ትኩረት ከሚደረጉባቸው ጉዳዮች አንዱ መሆኑን ያሳያል።

ቤተዘመድ ተወያይቶ ለልጃቸው የትዳር አጋር የምትሆን መርጠው ከወሰኑ በኋላ ሽማግሌዎች ተመርጠው ወደ ልጅቷ ቤተሰብ ይላካሉ። ሽማግሌዎቹም ቀጠሮ ይዘው ወደተመረጠችው ልጅ ቤተሰብ ቤት በመሄድ “ልጃችሁን ለልጃችን” በማለት ጥያቄ ያቀርባሉ። ነገር ግን በባህሉ መሰረት የሴቷ ቤተሰብ ለሽማግሌዎች በዕለቱ መልስ መስጠት ስለማይጠበቅባቸው ‹‹ከዘመድና ከጎረቤት እንማከር›› በማለት ለአስራ አምስት ቀን ቀነቀጠሮ አስይዘው ሽማግሌዎቹን በክብር ይሸኟቸዋል። የልጅቷ ቤተሰብም ልጃቸው ለትዳር

እንደታጨች የማን ልጅ እንዳጫት ለቤተዘመድ በመንገር ከቤተ ዘመድ ጋር ይወያያሉ። ልክ እንደ ወንዱ ቤተሰብ ሁሉ የልጅቱ ቤተሰብም የልጁን የዘር ሀረግ፣ ስብዕናውን፣ "ሊያስተዳርራት ይችላል?፣ በምንስ ያስተዳድራታል? ቤተሰቦቹ የኑሮ ደረጃቸው ለልጃቸውም የሚተርፉ ናቸው?" በማለት ባላቸው አስራ አምስት ቀን ሲያጣሩ ስለልጃቸውም "ልጃችን ድንገት ተሳስታ ከሌላ ሰው ግንኙነት ይሆራት ይሆን፣ ታዋርደን ይሆን? እነእገሌን የመሰሉ ሰዎች በትዳር ሊዛመዱን ፈልገው በድንገት እንዳናጣቸው?" በማለት በተለይ እናትና አባት በድብቅ ይማከራሉ። ይህን ሀሳብ በ 15/11/2011ዓ.ም በተደረገ ቡደን ተኮር ውይይት "እናት እና አባት ለሴት ልጃቸው ሽምግልና ሲላክ ስለ ልጃቸው ጋብቻ በስጋትም ጭምር ይመካከራሉ፤ በተለይ እናት በአብዛኛው ከሴት ልጇ ጋር ቅርበት ስለሚኖራት በሴትነት ብልሃቷ ልጇን ቀስ ብላ በመመርመር ታጣራለች " በማለት ገልጸዋል። የልጅቷ ቤተሰቦች ስለ ልጁም ‹‹ልጁ ለልጃችን ይሆናል አይሆንም?›› በማለት ከቤተዘመድ ይማከራሉ። ይህን ውይይት ከተወያዩ በኋላም ስለ ልጁ በቂ መረጃ ሲያገኙ የልጅቷ አባት «ይህ ልጅ ለልጃችን ይሆናል» በማለት ይወስናሉ። ሽማግሌዎች ለሽምግልና ሲላኩ ስለተላኩት ጉዳይ ከማስረዳታቸው በተጨማሪ ስለልጅቷ ጨዋነትም ለማረጋገጥ በተለያየ ስልት ልጅቷን ይፈትኑ እንደነበር አቶ ታደሰ ሁንዴ ፣ታዴሰ ቀንአ እና ወ/ሮ ደስታ ማሞ እንዲህ ይገልጹታል።

> ለሽምግልና የተላኩ ሽማግሌዎች ከሚያደርጓቸው ተግባራት መካከል ዋናው የልጅቷን ጠንቃቃነት ለመፈተሽ ይረዳቸዉ ዘንድ ለጥርስ መፋቂያነት የሚጠቅም ረጅም እንጨት ወይም ሙካ ኡርጌሳ "Muka urgeesaa" ልጅቷ ከምትዘዋወርበት ቦታ ላይ ያስቀምጣሉ። ልጅቷ እንጨቱን አይታ አንስታ ካስቀመጠችው አስተዳደጓ ጥሩ እና ጠንካራ በመሆኑ እሷም ጠንቃቃ፣ ስነ ሥርዓት ያላት እና ባህሏን አክባሪ መሆኗን ያረጋግጣሉ። ለሽማግሌዎቹም በራሳቸው መፈተኛ ያረጋገጡትን ለልጁ ወላጆች ልጃቸዉ ከዚች ልጅ ጋር ጋብቻ መፈጸሙ መልካም እንደሆነ ይገልጻሉ። ልጅቷ ለሁሉም ሰው ክብር ያላት፣ ባህሏን አክባሪ፣ አስተዋይ ሴት መሆኗን ይመሰክራሉ። ባዩት ነገር ደስታኛ በመሆናቸው ከሴትዋ ቤተሰብ ቀነ ቀጠሮ ይይዛሉ። በተቃራኒዉ ደግሞ ልጅቷ ሽማግሌዎች ያስቀመጡትን ሙካ ኡርጌሳ "Muka urgeesaa" አይታውም ሆነ ሳታየው ሳታነሳ ተራምዳዉ ካለፈች ለትዳር የማትሆን እንዝህላል መሆኗን ያረጋግጣሉ፤ተመልሰዉም አይመጡም። የልጅቷ ቤተሰብም ባህሉን ስለሚያውቁት ሽማግሌዎች ተመልሰው አለመምጣታቸው ልጃቸው

በስውር ተፈትና ፈተናውን ማለፍ እንዳልቻለች ያረጋግጣሉ። (ቃለ መጠየቅ 12/11/2011፣7/11/2011 እና 13/11/2011)።

ይህ እንጨት ለፈተናው የተመረጠበት ምክንያት አንድም እንጨቱ በተፈጥሮው ጥሩ መዓዛ ያለው በመሆኑ ለምትታጨው ልጃገርድ ጥሩ እድል እንዲገጥማት (ፈተናውን እንድታልፍ) በመመኘት ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ እንጨቱ ለመፋቂያነት ስለሚያገለግል ማንኛውም የቤተሰብ አባል ወደ ቤት ሊያስገባው ይችላል። በመሆኑም ሽማግሌዎች ልጅቷ ሳትጠራጠር አስተዋይነቷን ለመፈተን ስለሚጠቅማቸው ተመራጭ ሆኗል።

ከጋብቻ በፊት ለሙሽሪትም ሆነ ለሙሽሪት ቤተሰብ ሌላው ፈታኝ ጉዳይ ደግሞ የሀሜተኞች ጉዳይ ነው። ሀሜተኞች (ወረኞች) በወንዱም በሴቷም ቤተሰብ ዘንድ ዉዥምብር ይፈጥራሉ። ምክንያቱም ለጋብቻ የደረሰች ልጅ ፈላጊዋ ብዙ በመሆኑ ወሬኞች እገሌን አግቢ እገሌን አታግቢ እያሉ ያወዛግቧታል። በሌላ መልኩ ደግሞ "ከነእገሌጋ ግንኙነት ነበራት ጨዋ አይደለችም፣ በሰርጓ እለት ቤተሰቦቿን ታዋርዳለች" ይላሉ። ይህ ደግሞ ለልጅቷም ሆነ ለቤተሰቦቿ ፈታኝ ጊዜ ይሆናል። በልጅቷ በኩል ከወላጆቿ ስምምነት ውጪ በአሴና (Aseenna) እንድታገባ ሊያደርጋትም ይችላል። ለወላጆቿ ደግሞ ምናልባት ሀሜቱን ከሰሙ ለልጃቸው የተላከውን የትዳር ጥያቄ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ እንዳይሆኑ (ስለ ልጃቸው ስጋት እንዲፈጠርባቸው) ያደርጋቸዋል። ልጁቷን በሚፈልጓት ወንዶች ዘንድም ልጅቷን ላለማጣት ሲሉ ቡቲ (Buutii) ወይም ነቂ (Naqii) ሊሞክሩ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ ነው እንግዲህ እናት ልጇን በብልሀት የምትመረምረው። ምክንያቱም በባህሉ መሰረት የወንድ ቤተሰብ ስለልጃቸው በነዚህ ሰዎች እንደሚያጣሩ እርግጠኛ በመሆናቸው ነው።

ሽማግሌዎች ለልጅቷ ያዘጋጁላትን ስውር ፈተና ካለፈች የቀጠሮ ጊዜያቸውን በመጠበቅ (በማክበር) በቀጠሮው ቀን ይሄዳሉ። የልጅቷ ቤተሰብም ተዘጋጅተው ይጠብቃሉ። ከዚያም የልጅቷ አባትም ከቤተዘመድ እንደተመካከሩ ለሽማግሌዎች ይናገራሉ። አያይዘውም በባህሉ መሰረት ልጅቷ እና ልጁ አብረው መሆን መቻላቸውንና አለመቻላቸውን ሚልኪ (Milkii) ለማየትና ብቅል ለማብቀል ጊዜ እንዲሰጣቸው ከሽማግሌዎች ፍቃድ ይጠይቃሉ። በባህሉ መሰረት ሚልኪ (Milkii) የሚታየው ማክሰኞ፣ ሀሙስ እና እሁድ ብቻ በመሆኑ በዚህ የጋብቻ ሥርዓት የአንድ ሳምንት ጊዜ እንኳ ዋጋ አለው። ምክንያቱም በማህበረሰብ ዘንድ እሁድ ቀን ፈጣሪን ማምለኪያ ቀን በመሆኑ በሬ አይጠመድም ፣ እርሻ አይታረስም፤ ሀሙስ

በተለምዶ የቀን ቅዱስ ተብሎ ስለሚታመን ሲሆን ማክሰኞ ቀን ሙሉ ቀን በመሆኑ ነው። በመሆኑም በማህበረሰቡ የጋብቻ ዕለታቸውንም በነዚህ ሶስት ቀናት ያደርጋሉ።

### 4.1.1.2 ሚልኪ (Milkii) ማየት

በዶረኒ ወረዳ ኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ ሚልኪ ማየት ተአምር እንደማየት ይቆጠራል። ማህበረሰቡ ሚልኪን ጥሩ እና መጥፎ በማለት በሁለት ይከፍላቸዋል።ሽማግሌዎች ለሽምግልና ሲሄዱ በእንስራ ሙሉ ውሃ የተሸከመች ሴት፣ ልጅ ያዘለች እናት፣ እንጨት በወገቧ የተሸከመች ሴት፣ የተጫነ ፈረስ እና ከብት መንገድ ላይ ካጋጠማቸው ሚልኪያቸው ጥሩ ነው ተብሎ ይታመናል። በሌላ መልኩ ደግሞ ልጓም ያለው ፈረስ፣ ሴት ውሻ ፣ ብቻውን ተከናንቦ የሚጓዝ ሰው ካጋጠማቸው እና የዱር እንስሳት ካቋረጧቸው የመጥፎ ሚልኪ ማሳያ ናቸው። በሁለቱም መንገድ የተቀመጡት የሚልኪ ማሳያዎች እያንዳንዳቸው የትዳር መተንበያ አላቸው። ለምሳሌ በእንስራ ሙሉ ውሃ የተሸከመች ሴት፣ ያልጎደለ፣ ያልተቀነሰ ነገር ያመለክታል። በማህበረሰቡ ደግሞ ድንግልናን ጠብቆ ለትዳር መብቃት በትዳር ጸንቶ ለመቆየት ከሚያስችሉ ጉዳዮች አንዱና ዋነኛው ነው በሚለው ያምናል። ስለዚህ እንስራውን የተሸከመችው ሴት መሆኗ እንዲሁም እንስራው ሙሉ መሆኑ ለጋብቻ ያጯት ሴት ድንግልናዋን የጠበቀች መሆኗን ስለሚያመላክታችው ትዳሩ ስኬታማ እና ዘላቂነት ያለው መሆኑን ያረጋግጣሉ። በመሆኑም ሽማግሌዎች ቀጠሯቸውን አክብረው ሉቢ (lubbii) ለማድረስ ይዘጋጃሉ።

የመጥፎ ሚልኪ ወካዮች ካጋጠሟቸው ለምሳሌ ብቻውን ተከናንቦ የሚጓዝ ሰው መከናነቡ መደበቅን ወይም ሊያሳየው ያልፈለገው ነገር መኖሩን ያሳያል። በመሆኑም የዚህ ሚልኪ (Milkii) ማሳያው በግልጽ የማይታይ ነገር ግን ወጣቶቹ ቢጋቡ በትዳር ህይዎታቸው ላይ እንቅፋት የሚሆን አንዳች የተደበቀ ነገር እንዳለ ያመለክታል። አንዲት ሴት ልጅ ድንግል መሆኗና አለመሆኗ በአይን በማየት መለየት አይቻልም። ስለዚህ ምናልባትም ይህ የሰውየው መከናነብ የልጅቷን ድንግል አለመሆንን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል ። ስለዚህ ጋብቻው ሊቀር ይችላል።ይሁን እንጂ ሚልኪው (Milkiin) ጥሩ አልሆነም ብሎ ጋብቻው በመቅረቱ ተጠያቂዎቹ ሚልኪው (Milkiin) ጥሩ እንዳልሆነ ስለሚያውቁ መቅረታቸውን በአሉታዊ አይመለከቱትም፤ ለወደፊትም በጠያቂና በተጠያቂ መካከል በሚኖራቸው ማህበራዊ ህይወት የሚያጋጥማቸው አሉታዊ ተጽኖም አይኖርም። ይህም የሆነበት ምክንያት ማህበረሰቡ

ከጋብቻ በፊት ሚልኪ (Milkii) መታየቱ ለተጋቢዎቹ ትዳር መስመርና መፍረስ ከፍተኛ አስተዋጾ እንዳለውና ትዳር ተመስርቶ ፍቺ መፈጸሙ የሚኖረው ተጽኖ ከፍተኛ እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው። በማህበረሰቡ ዘንድ ከጋብቻ በፊት ሚልኪ (Milkii) መታየቱ ለትዳር መስመር የነበረውን ጠቀሜታ አቶ ረጋሳ ገመቹ እንዲህ በማለት ይገልጹታል።

> ሚልኪ ማየት ለጋብቻው ስኬትም ሆነ ትዳሩን ለመወሰን አንዱ ማሳያ ነው። በመሆኑም የሁለቱን ተጋቢዎች የጋብቻ ዕለት ከመወሰኑ በፊት ሚልኪ ማየት የግድ ይሆናል። ምክንያቱም ሁለቱ ተጋቢዎች ሚልኪ ሳይታይላቸው ዝም ብለው በአጋጣሚ ጋብቻ ከመሰረቱ የወደፊት የትዳር ህይወታቸው የተሳካ አይሆነም። ነገር ግን ሚልኪ ታይቶላቸው ሚልኪው ጥሩ ሆኖ ሲጋቡ በትዳር ህይወታችው ምንም ችግር ሳይገጥማቸው ይኖራሉ። ብዙ ጊዜ ሰዎች በተጋቡ ከተወሰኑ ቀናት በኋላ ምክንያቱ በውል ባልታወቀ ነገር ሲለያዩ ይታያል። በመሆኑም ከጋብቻ በፊት ሚልኪ ማየት ተጋቢዎች ትዳር መስርተው ግጭት ወይም ፍቺ እንዳይገጥማቸው ያደርጋል። ነገር ግን ሚልኪ ታይቶ ሚልኪው ጥሩ ሁኖ ከተጋቡ የወደፊት የህይወት ዘመናቸው ችግር ሳይገጥማቸው በድሎት ይኖራሉ ተብሎ ይታመናል (ቃለ መጠይቅ 12/11/2011ዓ.ም.) ።

ከለይ ከተገለጸው አስተያየት የምንረዳው በማህበረሰቡ ሚልኪ ማየት በአሉታዊም ሆነ በአዎንታዊ ጎን የሚገኘውን የገጠመኝ ትርጓሜ፣ የወደፊቱን የጋብቻ ሁኔታ በትክክል የሚተነብይ ንግርት መሆኑን በጽኑ እንደሚያምኑበት ያሳያል።

#### 4.1.1.3 ሉቢ (Lubbii) ማድረስ

ሚልኪው ከታየ በኋላ ሽማግሌዎች የአንድ ወር ቀጠሮአቸው ሲደርስ ሉቢ (lubbii) ያደርሳሉ። በፊት ሲመላለሱ የነበሩ ሽማግሌች ድፍን ቡና፣ አሞሌ ጨው እና እርጥብ ሳር ይዘው ወደ ሴቷ ቤተሰብ ቤት ይሄዳሉ። እነዚህ ሽማግሌዎች የወሰዷቸው ነገሮች ሉቢ (lubbii) ይባላሉ።ሽማግሌያች ይዘውት የሚሄዱት አሞሌ ጨውም ያልተሸረፈ ሲሆን ቡናውም ያልተቀሸረ ነው።ይህም በማህበረሰቡ አመለካከት ድፍን ነገር ድንግልና ያላትን ሴት ወክሎ ያሳያል። የቡናው አለመቀሸርም ሆነ ያልተሸረፈ አሞሌ ጨው ይዞ መምጣት ምንም ያልጎደላት (ክብሯን፣ድንግልናዋን) የጠበቀች ልጃገረድ እንደሚፈልጉ፣ እርጥብ ሳሩም የልምላሜና የጥሩ ተስፋ መገለጫ እንደነበር በ5/11/2011 በተደረገ ቡደን ተኮር ወይይት ተገልጿል።



ፎቶ 2. በሥርዓቱ ጋብቻቸውን የፈጸሙ እናቶች በቡድን ተኮር ወይይት መረጃ ሲሰጡ።

ሽማግሌዎች ሉቢ (lubbii) በሚያደርሱበት ዕለት የሴቷ ቤተሰብም ብቅል አብቅለው፣ ቡና አፍልተው፣ ምግብ አዘጋጅተው ይጠብቋቸዋል። ቤተሰቦቿም ሚልኪው (Milkiin) ጥሩ መሆኑን ካመኑበኋላ ሽማግሌዎች ያመጡትን ተቀብለው ያስቀምጣሉ።ሽማግሌዎችም የተዘጋጀላቸውን የግብዣ ምግብ ከተመገቡ በኋላ ተጋቢዎቹ ቀለበት የሚያስሩበትን ቀን ከአንድ ወይም ከሁለት ወር በኋላ እንዲሆን ይወስናሉ። የልጅቷ ቤተሰቦች ሚልኪው ጥሩ መሆኑን እና አለመሆኑን ለመወሰን ያስችላቸው የነበረውን ሁኔታ በተመለከተ አቶ ረጋሳ ገመቹ እና አልማዝ ደጀኔ እንዲህ ይገልጹታል፡፡

> በእኛ ማህበረሰብ የሁለቱ ተጋቢዎች ቤተዘመዶች ከተጠናኑ በኋላ የልጅቷ ቤተሰብ ሚልኪ (Milkii) የማየት ተግባራት ያከናዉናሉ። በዚህም ልጃቸው ጥሩ የትዳር አጋር እንደሚገጠማት በልጃቸው በኩልም ምንም የሚያሰጋ ነገር እንደሌለ ያረጋግጣሉ። ይህንንም የሚያረጋግጡት በብቅሉ አበቃቀል ሁኔታ ነው፡፡ ብቅሉ ሲበቅል ተስተካክሎ እና ሙሉ ለሙሉ ከበቀለ፤ የተጋቢዎቹ የትዳር ህይወት የተስተካከለ ይሆናል ተብሎ ይታመናል። በመሆኑም ብቅሉ የትዳር ህይወታችውን ስላመለከታቸው የቀለበት ቀኑን ወስነው ይለያያሉ። በተቃራኒው ብቅሉ ሳይበቅል ቀርቶ ወይም ከበሰበሰ በልጃቸውም ሆነ በልጁ በኩል ችግር እንዳለ ስለሚያረጋግጥላቸው ጋብቻውን ይተውታል (ቃለ መጠይቅ 12/11/2011ዓ.ም.እና 5/11/2011ዓ.ም) ።

ይህንን ሀሳብ አቶ ታደሰ ቀንአ እንዲህ በማለት ያጠናክራሉ፤ ትዝብታቸውንም አያይዘው ይገልጻሉ።

> በድሮ ጊዜ ጋብቻ ከመወሰኑ በፊት በጥንቃቄ ሚልኪ ታይቶ፣ ብቅል ተበቅሎ ትዳር ስለሚመሰረት እንዳሁን ትዳር ፍቺ አይበዛም ነበር። አሁን አሁን ግን ጋብቻውም፣ ትዳሩም መጠናናት ስለሌለው ፍቺ በየቀኑ ያጋጥማል። ሚልኪ (Milkii) ታይቶ ጋብቻ ሲመሰረት ግን ሁሉም ነገር ቀድሞ ስለሚታወቅ ትዳሩ የሰመረ ይሆናል (ቃለ መጠይቅ 7/11/2011ዓ.ም. ) ።

ከላይ ከተገለጹት ሀሳቦች የምንረዳው ብቅል የዘር መቀጠልን የሚያመለክት አካባቢያዊ ትዕምርት መሆኑን ከዚህ ተተኳሪ ማህበረሰብ እምነት መረዳት ይቻላል። ከጋብቻ በኋላ ይህንን ማህበራዊ ተቋም ከሚያፈርሱት ምክንያቶች ውስጥ ልጅ አለመውለድ አንዱ ነው። ስለዚህ ማህበረሰቡ ይህ ችግር ከመፈጠሩ ወይም ተጋብቶ መፋታት ከመደረሱ በፊት ለዘመናት ባካበተው ባህላዊ ትውፊቱ፣ ሚልኪ (Milkii) የማየት ልማዱ አስቀድሞ እንደሚያስቀር ያመላክታል። ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ በትዳር ዙሪያ ያሉት ችግሮች ከድንግልና ክብር ማጣት ጋር ተያይዞ እየከሰሙ ሚልኪ (Milki) የማየት ባህል መቅረት እንደሆነ ከማህበረሰቡ አስተያየት ማረጋገጥ ተችሏል።

### 4.1.1.4 የቀለበት ሥርዓት

ለቀለበት የተያዘው ቀነ ቀጠሮ ሲደርስ ሽማግሌዎች ከልጁ አባት ጋር በመሆን የብር ቀለበት፣ ጉሜ (Gumee) ወይም የብር መስቀል በመያዝ ቀለበት ለማሰር ወደ ሴቷ ቤተሰብ ቤት ይሄዳሉ። እነዚህ ቁሶች ሙሽራው ሙሽሪትን ቀለበት የሚያስርበት ቁሶች ናቸው። በዕለቱ የሙሽራው ጓደኞች አብረው ወደ ሙሽሪት ቤት ይሄዳሉ። ሙሽሪትም ከጓደኞቿ ጋር በመሆን በቤተሰቦቿ ቤት ትጠብቃለች። ሽማግሌዎች በልጅቷ ቤተሰቦች የተዘጋጀውን ምግብ ከተመገቡ በኋላ ጓዳ ተቀምጣ የነበረችው ሙሽራ ወደ ፊትለፊት (ወደ ሽማግሌዎች) እንድትመጣ ይደረጋል። ሽማግሌዎች ያመጡት ድፍን ቡና ለምግብነት ለማዘጋጀት እየተቆላ ሳለ ‹‹ቡናው ተንጣጥቷል ፈጣሪን ለምኑ›› ይባላል። ሽማግሌዎችም ሙሽራው እና ሙሽሪትን ይመረቃሉ። ከዚያም የተቆላው ቡና ለምግብነት ተዘጋጅቶ ቡና ቀላ (Buna qalaa) ይበላል። በመቀጠል የልጁ አባትም ቀለበት ወይም የአንገት ማተብ ለሙሽሪት ያስሩላታል። ይህ ማለት ልጅቷ ቀለበት አሰረች ወይም ለጋብቻ ተዘጋጀች የሚለውን

ማሳያ ነው። በተጨማሪም በዚህ የቀለበት (የቃል ኪዳን) ቀን ሙሽራው በሰርጉ ዕለት ለሙሽሪት ሙሉ አልባሳትና ጌጦች ለቤተሰቦቿ ደግሞ ለእያንዳንዱ አንድ አንድ ቡሉኮ(Bulukko) ማሟላት እንዳለበት ይነገረዋል። በተጨማሪም በሰርጉ ዕለት ለሙሽራዋ አንድ ወይፈን ይዞ እንዲቀርብ ቃል ያስገቡታል። እንደ ሙሽራው አቅም ሰርጉ ከአንድ አመትና ከሁለት አመት በኋላ ሊሆን እንደሚችል ይወሰናል።

ሌላው በቀለበት ዕለት በሁለቱ ተጋቢዎች መካከል መቀራረብን ይፈጥር ዘንድ ባህላዊ ጭውውት ይደረጋል። በዚህ ባህላዊ ጭውውት መካከል ሙሽሪት ሴትነቷን፣ ሙሽራው ወንድነቱን የመለየት አጋጣሚ ይፈጠር እንደነበር ወ/ሮ አልማዝ ደጀኔ እና ፋናዬ ወርቁ እንዲህ ይገልጹታል።

> በድሮ ጊዜ በአጋጣሚ ካልሆነ ሁለቱ ተጋቢዎች ለመጀመሪያ ጊዜ የሚተያዩት በቀለበቱ ቀን ነው። በመሆኑም በዕለቱ ሁለቱ ተጋቢዎች ፊት ለፊት መተያየት እንዲችሉ ሆነው ይቀመጣሉ። ከሙሽሪት ጎንም ጓደኞቿ ወይም ዱራቡቱ (Dura butuu) አብረው ይቀመጣሉ። በዚህ ጊዜ በሁለቱ ተጋቢዎች ፊት ለፊት በሁለት ቅል ጠላ፣ በሁለት ቅል ወተት ይቀመጣል። ተጋቢዎቹ በቅል የተቀመጠውን ወተት እርስ በርስ እንዲረጫጩ እና ትኩር ተባብለው እንዲተያዩ ይደረጋል። በዚህ ጊዜ ሙሽሪትም ሆነች ሙሽራው አይኑን ከአይኗ/አይኗን ከአይኑ እንድታነሳ/እንዲያነሳ አይፈቀድም። ምንም እንኳ ድርጊቱ ባህል ሆኖ እንደጫወታ ቢታይም ምናልባት እሷ ደፍራ ማየት ካልቻለች  ችግር አለባት በሴትነቷ አትተማመንም (ድንግል አይደለችም) ሙሽራውም በሙሉ አይን ማየት ካልቻለ በወንድነቱ አልተማመነም የጎደለው ነገር አለ ተብሎ ይታመናል። ይህ የመፈታተኛ ጫወታ ከተጠናቀቀ በኋላ ሙሽራው መቶ ብር ወይም አምሳ ብር ከእርጥብ ሳር ጋር በማድረግ ሙሽሪት ጉልበት ላይ ያስቀምጣል። ብሩ ስጦታ ነው። እርጥቡ ሳር ደግሞ ለወደፊት የትዳር ህይወታቸው የብልጽግናና የመልካም ምኞት መግለጫ ነው። አብረዋት ለተቀመጡ ጓደኞቿም አቅሙ የቻለውን ያክል ጉልበታቸው ላይ ብር ያስቀምጣል። ይህ ሁኔታ ቁብሳ ወሊፊዱ (Qubsaa wali fidu) ይባላል (ቃለ መጠይቅ 5/11/2011ዓ.ም እና 7/11/2011ዓ.ም)።

ከላይ ከተገለጸው ሀሳብ የምንረዳው የነቀታ (Naqata)፣ የጋብቻ ሥርዓት ከአሴና (Aseenna) እና ከነቂ (Naqi) የበለጠ ክብር ያለው የጋብቻ ሥርዓት በመሆኑ በማህበረሰቡ ዘንድ

የተጋቢዎች የእርስ በርስ አለመተዋወቅ መገለጫ ሥርዓቶች መከናወኛዎችን እናስታውላለን። የቤተሰብ ምርጫ የተጋቢዎች ምርጫ ሆኖ እስኪሰማቸው ድረስ ሙሽሮችን በመተያየት በአዲስ ፍቅር ውስጥ የሚጥል ዘዴ ያሉባቸውንም ስነ ልቦናዊ ችግሮች የሚፈትኑበት አጋጣሚ በዱራ ቡቱ (Dura butuu) የታጀበ እንደሆነ ማጤን ይቻላል። ጥንዶች በትዳራቸው ጸንተው እንዲቆዩ ከጋብቻ በፊት ያሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሰረት መሆናቸውንም ያሳያል።

የሰርጉ ቀጠሮ ቀን ከመድረሱ በፊት አመት በዓል ቢመጣ ሽማግሌዎች ቡና እና አሞሌ ጨው ይዘው የሙሽሪትን ቤተሰብ ሄደው በመጠየቅ እና በሽምግልና ወቅት ያልተነገሩ ስለቤተሰቡ ሁኔታ በመንገር የሴቷ ቤተሰብ እናየወንዱ ቤተሰብ ግንኙነት የማጠናከር ስራን ይሰራሉ። እንዲሁም የሰርጉ ቀን ከመድረሱ በፊት ሽማግሌዎች ለድግስ የሚሆን ብር ከወንዱ ቤተሰብ በመውሰድ ለሴቷ ቤተሰብ ያደርሳሉ። ብዙ ጊዜ ለድግስ የሚሰጠው ብር ለሙሽራዋ የልብስ ሳጥን፣ ጉንዶ፣ ሻርፌ (Sharfee)፣ አገልግልና የመሳሰሉት በስጦታነት ለሙሽራዋ የሚበረከቱ ቁሶችን ለመግዛት ይውላል። እነዚህን ቁሳቁሶች በመልሱ ዕለት የሙሽራዋ ጓደኞች ሙሽራው ቤት ያደርሳሉ።

#### 4.1.1.5 ሚዜ መረጣ

የነቀታ (Naqata) የሰርግ ሥርዓት ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች ሚዜ መረጣ አንዱ እንደ ነበር ይነገራል። በባህሉ መሰረት የሙሽራውን ሚዜ የሚመርጠው የሙሽራው አባት ሲሆን ሙሽራው አባት ከሌላው ግን እናት የአባትን ቦታ በመተካት ዝምድና የሌለው ሰው (ባዕድ) ፈልጎ ለሚዜነት ይጠየቃል። የተመረጠው ሚዜ ደግሞ ሌሎች ሚዜዎችን ይመርጣል። ተጨማሪ የሚመረጡት ሚዜዎች ሁለትም ሶስትም ሊሆኑ ይችላሉ። ሁሉም ግን ልክ እንደ አንደኛ ሚዜው ባዕድ መሆን አለባቸው። ሚዜዎች ከጋብቻ በኋላ ለሁለቱም ሙሽሮች እንደዘመድ ይቆጠራሉ። ባዕድ የተመረጠበት ምክንያትም ከባዕድ ጋር ዝምድና ለመፍጠር ስለሚፈለግ ነው። የተመረጡት ሚዜዎች በተለይ ለሙሽሪት ልክ እንደ ወንድም ይቆጠራሉ።

### 4.1.1.6 የሙሽሮች አመጋገብ

በነበረው የጋብቻ ሥርዓት ሴት ልጅ ለጋብቻ ታጭታ ወር ያህል ሲቀራት ቤተሰቦችዋ አቅማቸው በፈቀደ መጠን የተለየ ምግብ ያዘጋጁላታል። ምግቡም ጥቁር ጤፍ በእጅ ተፈጭቶ ቂጣው በደረቁ ተጋግሮ በቅቤ እየተለወሰ ነበር። ደረቅ ቂጣ የተመረጠበት ምክንያት አንድም ሙሽራዋ ጥንካሬ እንዲኖራት ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ አማቶቿ ቤት ስትሄድ ለመጸዳዳት ትቸገራለች ተብሎ ስለሚታመን ነው። ሙሽራውም "ቤት ሰሪ እና ሰርገኛ ደም የለውም" ስለሚባል የተለያዩ ጉልበት የሚሰጡ ምግቦች ዘመዶቹ ይቀልቡታል። ይህንን ሀሳብ በተመለከተ ወ/ሮ አልምዝ ደጀኔ እና ወ/ሮ ደስታ ማሞ እንድህ ይገልጹታል፡፡

> ድሮ ድሮ ሴት ልጅ የምትድር እናት ከወር አስቀድማ ለልጇ ቅቤ አንጥራ፣ ጥቁር ጤፍ ፈጭታ ከሌላው ቤተሰብ በተለየ መልኩ ቂጣ በቅቤ እየፈተፈተች ትመግባታለች። ምክንያቱም  በዛን ዘመን ሴት በሙሽርነቷ ጊዜ እንደፈለገች ወደ ውጭ ወጥታ ሽንት ቤት መጠቀም ስለማትችል እና በሰርጓ ዕለት ጥንካሬ እንዲኖራትም ታስቦ ነው። ሙሽራውም ጥሩ (ያለው ቤተሰብ ልጅ) ከሆነ ታርዶ ካልሆነ ጉልበት የሚሰጡ (ምስር፣ባቄላ ወዘተ) ምግቦች እና ጠላ እንዲያስጠጣው በርበሬያቸው ሞቅ እየተደረገ እየተሰሩ በደንብ ይቀለባል። (ቃለመጠይቅ 5/11/2011ዓ.ም እና 13/11/2011ዓ.ም)

ከላይ ከተሰጠው ማብራሪያ የምንረዳው የታጨችው ወጣት ከቤተሰብ በተለየ ሁኔታ ጥቁር ጤፍን መመገቧ ከመጸዳዳት ችግር እና ከአቅም ጋር የተያያዘ ብቻ እንዳልሆነ መገንዘብ ይችላል። ምክንያቱም የታጨላት ሰው እንደቤተሰቡ አቅም ገንቢ ምግቦች እየተመረጡለት ይቀለባል። ለምን ቢባል  ለመጀመሪያ ጊዜ አንሶላ መጋፈፉ እንዲሁ የሚከናወን አይደለም፤ አቅም ይጠይቃል። በዚህ ቀን የሴትዋ ተፈጠሮ የደም መፍሰስ ይዳርጋታል። በሳይንሱ ደግሞ ጥቁር ጤፍ "አይረን"ን እንደሚተካ ይታወቃል። በመሆኑም የደምን "አይረን" የተባለውን ማዕድን የሚተካውን ይህንን ጥቁር ጤፍ ማህበረሰቡ ከብዙ ዘመናት ጀመሮ በልምድ አውቆት እየተጠቀመበት እንደሆነ ማሰብ የሚቻልበተ አጋጣሚ ሆኖ እናገኘዋለን።

### 4.1.1.7 ሲርባ ዱርባ (Sirba Durbaa)

የሰርጉ ቀን ከመድረሱ ከሁለት ሳምንት ወይም ከአንድ ወር በፊት በሁለቱም ቤተሰቦች የድግሱ ቅድመ ዝግጅት ይጠናቀቃል። ሲርባ ዱርባ (**sirba durbaa**) ፣አራብሶ (Arrabsoo)

በሁለቱም ቤተሰቦች መኖሪያ ግቢ ውስጥ መጨፈር ይጀመራል።ይህም የሚሆነው የሰርጉን ድባብ ለመፍጠር እና ሙሽሮቹ ብቸኝነት እንዳይሰማቸው ለማድረግ ሲባል ነው።

### 4.1.2 ጊዜ ሰርግ

በሰርጉ ዕለትም ሙሽራው ከሚዜዎቹና ከጓደኞቹ ጋር በመሆን ሙሽራዋን ለማምጣት ይሄዳል። በባህሉ መሰረት አንድ ሰው ከቤት ከመውጣቱ በፊት በሄደበት እንዲቀናው እና በቀኝ እንዲያውለው በእናት እና በአባቱ ወይም በሽማግሌዎች ተመርቆ መውጣት ይኖርበታል። በመሆኑም ቀለበት ያሰረው ወጣት በሰርጉ ቀን ሙሽሪትን ለማምጣት ከመሄዱ በፊት እናት እና አባቱ እርጥብ ሳር፣ ያልተቀሸረ ቡና ፣ድፍን ባቄላ እና ሞልተው የተቀዱ አራት ቅል ጠላ በማቅረብ የሙሽራውን እና የሚዜዎቹን እጅ በመያዝ

| **በመገኛ ቋንቋ** (Afaan Oromootin) | **በአማርኛ ትርጉም** |
|---|---|
| *Karaa nagaa deemaa* | መንገዳችሁ ሰላም ይሁን |
| *Iji hamaan isin hin argin* | ከክፉ አይን ይጠብቃችሁ |
| Gaa'illi gaa'ila milkii isiniif ha ta'u! | ጋብቻችሁ የሰመረ ይሁንላችሁ |
| Hamaan isin irraa ha goru | ከክፉ ያርቃችሁ |
| Dubbadhaa arraba tolaa | የተናገራችሁት ተደማጭነት ያግኝ |
| Deemaa milkii tolaa | ሂዱ ገድ ይቅናችሁ |

Nagaan bahaa,nagaan milka'aa galaa በደህና ወጥታችሁ ተሳክቶላችሁ በደህና ግቡ

በማለት ይመርቋቸዋል። መሆኑም በሙሉ ቁጥር ሞልቶ የተቀዳ ጠላ የተሟላ ትዳርን፤ ድፍን ባቄላ እና ያልተቀሸረ ቡና ያልተነካች (ድንግል) ሴት እንድትገጥመው መልካም ምኞት መግለጫ ሆነው ይወክላሉ። በተጨማሪም ያልተከካው ባቄላ መዋደድን (ልብ ለልብ መገናኘትን) ያሳያል። ከተመረቁ በኋላ ሙሽራው ከአጃቢዎቹ ጋር በመሆን በፈረስ ፣ ለልጅቷ እና ለቤተሰቦቿ የተዘጋጀውን የስጦታ እቃ በመያዝ እየጨፈሩ ይሄዳሉ። ሰርገኞች የሙሽሪት ቤተሰብ እንደደረሱ የሙሽሪት ታናናሽ ወንድሞች እና የአካባቢ ወጣቶች የአጥር በር በመዝጋት አናስገባም ሲሉ ሰርገኞቹ ታግለው ወጣቶቹ አሸንፈው መግባት

ከቻሉ ይገባሉ።ካልቻሉ ግን የመግቢያ ብር በመስጠት እንዲገቡ ይደረጋሉ። ወደ ውስጥ እንደገቡ ወጣት ሴቶች ተሰብስበው አራብሶ (arrabsoo) እያዜሙ ይጠብቋቸዋል። በሙሽሪት ቤተሰቦች ሚዜዎቹ ሲሞገሱ ሙሽራው ግን ይሰደባል። ወጣቶች በሲርባ ዱርባ (sirba durbaa) ሙሽራውን ከሚሰድቡበት መካከል

| **በመገኛ ቋንቋ (Afaan Oromootin)** | **በአማርኛ ትርጉም** |
|---|---|
| Aabbee yaa gurbaa | አንተ ወጣት |
| Maal fuuchuu dhuftee | ምን ልትወስድ መጣህ |
| Fuudhi waa lafaa | አንሳ ቆሻሻ ከመሬት |
| Dadhabaa fafaa | ቀርፋፋ ደካማ |
| **አዝማች** | |
| Gabaabaa gufuu | አጭር እንቅፋት |
| Balbalaan cufuu | በሩን ይዘጉበታል |
| Dheeraa fokkisaa | አስቀያሚ ረጅም |
| Qabaa gombisaa | ያዙና አስጎንብሱት |
| **አዝማች** | |
| Jaarsi abbaa keetiis | የአባትህ ሽማግሌዎችም |
| Halkan marmaaree | ለሊት ተመላልሶ |
| Guyyaa marmaaree | ቀን ተመላልሶ |
| Obboleettii koon gargar nabaase | ከእህቴ ነጠሉኝ…እያሉ ቂጭታቸው |

ይገልጻሉ። ከዚያም ለሙሽሪት የመጣው ጥሎሽ እርክክብ ይደረጋል። በርክክቡ ወቅት ሽማግሌዎች ይመጥናል፣ አይመጥንም በማለት ይወስናሉ። የማይመጥን ከሆነ ብር እንዲያሲዝ ይደረጋል። በዚህ ጊዜ ጓደኞቿ እንዲህ በማለት ያበሽቁታል።

| **በመገኛ ቋንቋ (Afaan Oromootin)** | **በአማርኛ ትርጉም** |
|---|---|
| Amaamota ishee uraa'e | አንት ሰርገኛ ሆይ |
| Birrii tokkoon aduun moluu kee uraa'i | በአንድ ብር መላጣህን እበሳዋለሁ |
| Hiriyaa hin qabdu hin liqeeffattuu | ጓደኛ የለህም? አትበደርም? |

Anuu keennen sifuraa — እኔው ሰጥቼ እገላግልሃለሁ

Siqi ija abbaakoo dura — ዞር በል ከአባቴ ፊት ለፊት

Fulloo fardaa kan shaashee — የሻሼ ፎሎ ፈረስ

Sareen garbaa kunoo gadi yaate — ወደ ውጭ ወጡ እነዚህ ባሪያ ውሾች

እያሉ ጎደኞቿ ሲያዜሙ ሙሽራው እና ሚዜዎቹ ጉልበት እየሳሙ ለሙሽሪት ቤተሰብ ጋቢ ወይም ቡሉኮ (Bulukko) ሲያበረክቱም ጎደኞቿ ሙሽራውን በዜማ ያበሽቁታል።

| **በመገኛ ቋንቋ (Afaan Oromootin)** | **በአማርኛ ትርጉም** |
|---|---|
| Harka fudhan abbaakooti gooromsayi | የአባቴ መጠየቂያ ወይፈን ነው |
| Harka fudhan haadhakooti dibichaayi | የእናቴ መጠየቂያ ጊድር ነው |
| Maal abbaakee dinqa ijaajjitee roqomtaayi | ጓዳ ተገትረህ ምንአባክያንቀጠቅጥሃል? |
| Sirra ijaajjeen akka abbaakee sigorsaayi | ከላይህ ላይ ቆሜ እንደ አባትህ ልምከርህ ወይ? |

በዚህ ጊዜም ሲርባ ዱርባ (sirbi durbaa)፣ደለጋ (Delaga) እና ሌሎች ጭፈራዎች ይጨፈራሉ። ሙሽራዋም በጭፈራው መሀል ትገኛለች። ሙሽራዋ የቤተሰቦቿን ቤት ጥላ ስለምትሄድ ስለመለየት ታዜማለች። በዜማዋ መሀል በእንጉርጉሮ ለቤተሰቦቿ እና ለጓደኞቿ የስንብት መልዕክቷን ታስተላልፋለች። ወ/ሮ እጅጋየሁ ወዳጆ በዕለቱ በሙሽሪት ቤተሰብ ቤት የሚኖረውን ድባብ በትውስታ እንዲህ ይገልጹታል።

> ሙሽሪት ከጓደኞቿ መሀል ሆና ስታዜም የወንድሟ ወይም የአጎቷ ሚስት መታ ትወስዳትና ገላዋን ታጥባታለች። ገላዋን ስታጥባትም "ምሽት ድንግልና ሲወሰድ የህመም ስሜት አለው ነገር ግን ለአንቺም ሆነ ለሱ ቤተሰቦች የኩራት መገለጫ ስለሆነ ምንም አትፍሪ አይዞሽ" በማለት ታበረታታታለች። በዚህ ጊዜ ሙሽራዋ ምርር ብላ ታለቅሳለች። ከዚያም የመሞሸሪያ ልብሷን ለብሳ ወደ ፊትለፊት ስትመጣ ዘመዶቿ፣ጓደኞቿ ሁሉም ያለቅሳሉ ለቅሶውም እንደ አሁኑ "ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ አይነት" ሳይሆን ሁሉም ስለሚያለቅስ በጭፈራ ደርቶ የነበረው አዳራሽ በሀዘን ይቀየራል(ቃለ መጠይቅ15/11/2011ዓ. ም.) ።

ከላይ ከተጠቀሰው ሀሳብ የምንረዳው ማህበረሰቡ የጫጉላ ቤት አንሶላ መጋፈፉ ከመጀመሩ በፊት ሙሽሪት ሁለንተናዊ ዝግጅት እንድታደርግ ልምድ ባላቸው ሰዎች (ትዳር በመሰረቱ ሴቶች) በምክር ስነልቦናዊ ግንባታ ያደርግ እንደነበር ያሳያል።

ሁሉም ነገር ሲጠናቀቅ ግብዣ ይደረጋል። ከግብዣው በኋላ ያልተቆረሰ እንጀራ በመሶብ በማስቀመጥ፣ በአራት ቅል ጠላ በመሙላት እና ሙሽራው እና ሙሽሪትን ብቅል በማስያዝ ሽማግሌዎች እንደሚከተለው ይመርቃሉ።

| **በመገኛ ቋንቋ** (Afaan Oromootin) | **በአማርኛ ትርጉም** |
|---|---|
| *Qabattanii nagaa qabadhaa!* | ይዛችኋል ጤና ይኑራችሁ |
| *Halkan Abjuu qabadhaa!* | ምሽት ህልም አልሙ |
| *Umurii Harraagessaa qabaadhaa!* | የሰጎን እድሜ ይስጣችሁ |
| Manaa isinii ha tolu! | ቤቱ ይመቻችሁ |
| Alaa isinii ha tolu! | ዉጪው ይመቻችሁ |
| Keessatti Adii cuuphadhaa, | ውስጥ ነጭ (ጮማ) ግመጡ |
| Alatti Adii uffadhaa | ዉጭ ነጭ ልበሱ |
| Bonaa-Ganna lalisaa! | በጋ ክረምት ለምልሙ |
| Hamaa keessan hiddii fardi irra ejjate ha ta'u! | ጠላታችሁን ፈረስ የረገጠው ሀረግ ያድርግላችሁ |
| Daaraa Bubbeen fuudhe ha ta'u. | አውሎንፋስ የውሰደው አመድ ያድርገው |
| Hamaafi hamtuu isinirraa ha qabu, | ከከፉ ይጠብቃችሁ |
| Afaan keessan haadhaafi qadaada ha ta'u! | አፋችሁን ሙጫና ክዳን ያድርግላችሁ |

ሽማግሌዎች ሲመርቁ የቀረበው ያልተቆረሰ እንጀራ እና በአራት ቅል የሞላው ጠላ የእንጀራው አለመቆረስ እንዲሁም የጠላው አለመጉደል የልጅቷን ድንግልና (ሙሉ መሆኗን) ሲያመለክት በሌላ መልኩ ደግሞ ትዳራቸው ሙሉ እንዲሆን መልካም ምኞታቸውን ያሳያል። ብቅሉም ልጅ እንዲያገኙ መመኘታቸውን ያመለክታል።

ሚዜዎቹም ደግሞ ሰም አብርተው ለምርቃት ይቀርባሉ። በመቀጠልም በባህሉ መሰረት ሚዜዎቹ ለሙሽራዋ እንደ ወንድም ስለሚቆጠሩ የሙሽራዋን እጆች በመያዝ እና እየነደደ

ያለውን ሰም በማጥፋት እንደ ወንድም ሆነው የወንድምነትን ድርሻን ሊወጡ ቃል ይገባሉ። “የገባሁትን ቃል ካጠፍኩ እንደዚህ ሰም ያጥፋኝ” በማለት ይምላሉ፤ቃልም ይገባሉ። ሽማግሌዎቹም የመጨረሻውን ምርቃት ይመርቃሉ።

ከተመረቁ በኋላ ሚዜዎቹ ሙሽሮቹን ፈረስ ላይ አስቀምጠው ጉዞ ሊጀምሩ ሲሉ ልጃገረዶች ለሙሽራዋ ከመጣው እቃ ውስጥ ሰፌዱን በመውሰድ ሙሽራውን መሳደብ ይጀምራሉ። በዚህ ጊዜ የሙሽራው ጓደኞች ፈረሳቸውን በማስጋለብ እና የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ሰፌዱን ለመቀማት ይሞክራሉ። ጥለው ከሄዱ በጣም ስለሚናቁ በሀይል ጉልበታቸው ተጠቅመው ቀምተው እየጨፈሩ ይሄዳሉ። ሰፌዱ በጣም የምታምርና ለመያዝ ምቹ በመሆኗ ከሌሎች ቁሶች በተለየ ተመራጭ ሆናለች። ውክልናዋም ለሙሽሪት ነው። ምክንያቱም ሙሽሪት በሰርጓ ዕለት በመዋቢያ ቁሶች ስለምትዋብ የበለጠ ታምራለች። ሰፌዱም ለስጦታነት የምትሰጥ በመሆኗ በጥንቃቄ ትሰፋለች። ስለዚህ ፍልሚያው የሚያመለክተው በወንዱ ወገን እንወስዳልን ሲሆን የሴቷ ወገን ደግሞ አንሰጥም የሚለውን ለማመልከት ነው። ይህ በሁለቱ ወገን መካከል የሚደረገው ፉክክር ጉንዶ ቦሬ (*Gundoo Booree*) ይባላል።

ሰርገኞቹ በሙሽራው ቤተሰብ ቤት ሲደርሱ ከሙሽሪት ቤተሰብ ቤት በተቃራኒ ሚዜዎቹውን ሲሳደቡ ሙሽራውን ያወዲሱታል። ሙሽሪትን ደግሞ፤

| | |
|---|---|
| በመገኛ ቋንቋ | *Intalloo kaleessa yoonaa; kaattiiree lagatti kaattii* |
| በአማርኛ | ትናንት ይህኔ ወጣቷ ወንዝ ልትሄድ ተነስታለች |
| Afaan Oromootin | *Cuqqaaltee huuroo cuqqaaltee,galtiiree,manatti galtii?* |
| በአማርኛ | ከደነችው እንስራውን ከደነችው፤ትገባለች እንዴ ወደቤት ትገባለች? |
| Afaan Oromootin | *Cuqqaaltee ulfa cuqqaaltee,da’ee koo nan badeem jettii!* |
| በአማርኛ | ደበቃ እርግዝናዋን ደብቃ እናቴ ተዋረድኩ ትላለች |
| Afaan Oromootin | *Abbayeen hin rafeem jettii,durbummaan hin badeem jettii* |
| በአማርኛ | አባዬ ተኝቷል ድንግልናዬ ተውሰደኮ ትላለች |
| Afaan Oromootin | *Qoy yaa ilmoo koo hin badduu jettee* |

| | |
|---|---|
| በአማርኛ | ቆይ ልጄ አልተወሰደም ትላታለች |
| Afaan Oromootin | *Gad baatee qullubbii buttee* |
| በአማርኛ | ወጣ ብላ ነጭ ሽንኩርት አምጥታ |
| Afaan Oromootin | *Ol galtee shunkurtii buttee* |
| በአማርኛ | ገባ በላ ሽንኩርት አምጥታ |

አዝማች

| | |
|---|---|
| Afaan Oromootin | *Nadhii ilmoo ishee obaastee* |
| በአማርኛ | ልጇን ጠጅ  አጠጥታ |
| faan Oromootin | *Dhiiga ilmoo ishee irra lolaastee* |
| በአማርኛ | ከልጇ ገላ ላይ ደም አፍስሳ |
| Afaan Oromootin | *Saree Abbaa jissaa badhaastee* |
| በአማርኛ | ለአቶ ጅሳ ውሻ ሸለመችው |
| Afaan Oromootin | *Yaa jissaa baga badhaatee* |
| በአማርኛ | አንተ ጅሳ እንኳን ከበርክ |
| Afaan Oromootin | *Yaa intalaa baga mancaatee* |
| በአማርኛ | አንቺ ወጣት እንኳን ተዋረድሽ. . . እያሉ ይሰድቧታል። |

ሰርገኞቹ  በወንድ ሙሽራ ቤተሰብ ቤት እንደ ደረሱ የሰሌን ወይም የቁርበት ምንጣፍ ተነጥፎ እንዲቀመጡበት ይደረጋል። ቤተሰብም ወተት፣ማርና ምግብ አዘጋጅተው ይጠብቋቸዋል። በተነጠፈላቸው ምንጣፍ ላይም ከፈረስ ወርደው ሙሽሪትና ሚዜዎች ይቀመጣሉ። የወንድ ሙሽራ ግን ከሴቷ ሙሽራ ጎን ወንበር ላይ ይቀመጣል። ይህም የሆነበት ምክንያት በድሮ ጊዜ የወንዶች የበላይነት ጎልቶ ይታይ ስለነበር ነው። በተቀመጡበት ቦታም የሰፈር ሽማግሌዎችና ቤተሰብ ይመርቋቸዋል። የምርቃቱ ይዘትም ሙሽሮቹ ልጅ እንዲወልዱና ህይወታቸው የተሳካ እንዲሆን ነው። የሙሽራው አባት ይዘው ከሚመርቁበት ወተት በመጎንጬት ሁለቱን ሙሽሮች ይረጯባቸዋል። የሙሽራው እናት ደግሞ

ቡናቀላ (Buna qalaa) ያጎርሷቸዋል። በሙሽራው ቤትም ልክ እንደ ሴቷ ቤተሰብ ቤት የተለያዩ ጭፈራዎች ይጨፈራሉ። የምርቃት ሥርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ ሙሽራው ሙሽሪትን ወደጫጉላ ቤት ይዟት እንዲገባ ይነገራዋል።

#### 4.1.2.1 ረኮ ቀሉ (Rakoo Qaluu)

በባህሉ መሰረት ሁለቱ ተጋቢዎች ግብረ ስጋ ግንኙነት ፈጽመዉ ድንግልና የመውሰዱ ሂደት ረኮ ቀሉ (rakoo qaluu) ይባላል። ሙሽሮቹ ወደ ጫጉላ ቤት ሲገቡም ሙሽራው ካለው በግ አርዶ ከሌለው ደግሞ ጨፌ ቆርጦ ይገባል። ሙሽራው ወደ ጫጉላ ቤት ለመግባት ከመቀመጫው እንደተነሳ ተቀምጦበት የነበረዉን ወንበር ሙሽሪት ገፍትራ ትጥለዋለች። ሙሽሪት ወንበሩን መጣሏ "ጫጉላ ቤት እንተያያለን ምንም ገነህ ብትቀመጥም በጫጉላ ቤት ጫወታ እኔ እረታሃለሁ" የሚለውን ያሳያል። እሷ የጣለችዉን ወንበር የሙሽራው ያገባች ታላቅ እህት ወይም የወንድም ሚስት ሁለቱ አማራጮች በሌሉበት የአጎት ሚስት ወደ ጫጉላ ቤት ታስገባዋለች። ወደ ጫጉላ ቤት ከገቡ በኋላም ሙሽራው እዛው ወንበር ላይ ይቀመጣል። ከዚያም ቀጥሎ ኢልማ ፉራ (Ilmaa furaa) የሚባል ሥርዓት ይከናወናል። ይህ ሥርዓት ከግብረ ስጋ ግንኙነት በፊት የሙሽራው እናት የሙሽሪትን መቀነት ትፈታለች። መቀነቷን ከፈታች በኋላ "ድንግል ከሆንሽ ጥጃ ወይም ላም እሰጥሻለሁ" በማለት የስጦታ ቃል ትገባለታለች። ይህ ስጦታ የሙሽሪት የግል ስጦታ ነው። ምናልባ+ት ትዳሩ በፍቺ ቢጠናቀቅ እንኳ ይህንን ስጦታ ባል የመካፈል መብት የለውም። ከዚያም የሙሽራዋን ድንግልና የሚወሰደው በአብዛኛው ከምሽቱ አራት ሰዓት በኋላ ነው። ምክንያቱም አንድም በድሮ ጊዜ ሰርገኛ ወደ ሙሽራው ቤተሰብ ቤት የሚገባው አምሽቶ በመሆኑ ህጻናት ስለሚተኙ ሲሆን በሌላ መልኩ በዚህ ስዓት ሰርገኞች በልተው ጠጥተው ጭፈራውን ስለሚያደምቁት ነው። በዚህ ስዓት ሁሉም ጫጉላ ቤቱን ለቀው ይወጡና ውጭ ላይ ጭፈራ ይደራል። ሙሽሮቹ ግብረስጋ ግንኙነት ይፈጽማሉ። በዚህ ጊዜ ሙሽራዋ ድንግል ከሆነች ደም ይፈሳታል።

ደም፤ በሥርዓቶቹም ሆነ አጠቃላይ በማህበረሰቡ የተለያዩ ፅንሰ ሃሳብ ይይዛል። የመቀደስ እና የመርከስ ብሎም ነጻ የመውጣት እሳቤ አለው። ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች ድንግልናቸው ሲወሰድ የሚታየው ደም ነጻ መውጣትን ያሳያል። ሴቶቹ ከነበሩበት ህገ ወጥ ያለመፈጸም ፍጹም ቀንበር በዛ ቀን ከባላቸው ጋር የልባቸውን በማድረግ በሚፈሰው ደም ነጻነታቸን ያገኛሉ። በሌላ በኩል ደምና ቃል ኪዳን ባልና ሚስት

የመተሳሰሪያቸው እንደመሆናቸው ይህ ዕለት ኪዳን የሚፈጽሙበት ቀን ይሆናል። በተጨማሪም ደሙ በጨርቁ ላይ መታየቱ ክብርን ወይም አለመደፈርን ያሳያል።

በባህሉ መሰረት በመጀመሪያ ሙሽሪት ከወላጆቿ ቤት ወደ ሙሽራው ቤት ስትወሰድ ወላጆችዋ አብረዋት የሚሄዱ ሁለት ወጣት ወንዶች ያዘጋጃሉ። እነዚህ ሁለት ወጣቶች ሙሽሮቹ ወደ ጫጉላ ቤት ሲገቡ ከቤተ ዘመድ ጋር በመሆን የምስራቹን ይጠባበቃሉ። በወንዱ ወገን የተመረጠችው ሴት (ሙሽሪት የሙሽራውን ወንበር ስትጥለው ያነሳችው ሴት) ከሙሽሮቹ ጋር ወደ ጫጉላ ቤት ትገባና በጫጉላው በስተኋላ ከቅርብ እርቀት ሆና ትከታተላለች። በመጨርሻ ሙሽሪት ድንግል ከሆነች የተመረጠችው ሴት የሸማ ጨርቁን የምስራች (ደም) አስነክታ "እልል" እያለች ወደ ሚዜዎቹ ታመጣለች። ይቺ ሴት የምታረጋግጠው የሙሽራዋን ድንግልና ብቻ ሳይሆን ምናልባት ሙሽራው በድንጋጤ፣ በህመም ምክንያት የአቅም ማነስ ገጥሞት ድንግልና መውሰድ ባይችል ችግሩ የወንዱ መሆኑን ለሽማግሌዎች ታረጋግጣለች። ልጅቷ ድንግል ሆና ሙሽራው ድንግልናዋን መዉሰድ ካልቻለ የልጁ ቤተሰብ ያዝናሉ፤ይናደዳሉ። ነገር ግን በሽማግሌዎች ተመክሮና የተለያዩ ስሜት ሰጪ ምግቦች እየተመገበ በአምስት ቀናት ውስጥ ድንግልናዋን እንዲወስድ ይደረጋል። እስከ አምስተኛው ቀን መውሰድ ካልቻለ ይህ ችግር እንዲፈጠር ያደረገው የእናት አባቱ ውቃቢ ነው ተብሎ ስለሚታመን ውቃቢው ይለመናል። በነዚህ ሁኔታዎች ሙሽራው ድንግልና መውሰድ የሚችልበት ሁኔታዎች ይፈጠራል። ማህበረሰቡ ከነዚህ አማራጮች በፍጹም አያልፍም ብለው ያምናሉ። በተለይ የእናት አባት ውቃቢ ከተለመነ ሁሌም እንደሚሳክ ይታመናል። በአጋጣሚ ግን ቢፈጠር ዋርሳ "Waarsaa" የሚወስድ ይሆናል። የሙሽራዋም ቤተሰብ ሁኔታውን ስለሚያውቁ እስከ አምስት ቀን የምስራቹን በትግስት ይጠብቃሉ ድንግል ሆና ድንግልናዋን መዉሰድ ከቻለ ቤተሰብ ይደሰታሉ።

ድንግልና የመውሰዱ ሁኔታ ሲከናወን  የአዳራሹን አካባቢ ሁኔታ ወ/ሮ አልማዝ ደጀኔ ፣ ወ/ሮ ደስታ ማሞ እና ንጉሴ ኡርጂ እንዲህ በማለት በትዝታ ይገልጹታል።

> በዚህ ምሽት ለሙሽሮቹ የተደበላለቀ ስሜት እንዲኖራችው የተለያዩ ክዋኔዎች ይከወናሉ። ከውጭ ያለዉ የሲርባ ዱርባ (Sirbaa Durbaa) ድምቀት፣ ትጮሃለች አትጮህም የሚለዉን ለማረጋገጥ የሚደረገው ሁኔታ፣ ሚዜዎች እና የሙሽራው ወንድም ደግሞ እነዚህን የሙሽሪትን ጩኸት ለማዳመጥ ጫጉላ ቤቱን የከበቡትን ልጆች ለማባረር የሚያደርጉት ጥረት ከፍተኛ ነው። ሙሽራዋ ድንግል ከሆነች ዳሱ

> በእልልታ፣ በሆታ ያለው ድምቀት እና ሁሉም ሰው ለሙሽሮች ስጦታ እንዲሰጣቸው ሚዜዎች የሚያደርጉት ርብርብ ምሽቱን ደማቅ ያደርገዋል። ታዲያ ሙሽራው ይህንን ሁሄታ ስለሚያውቅ በድንጋጤ ድንግልናዋን መውሰድ ሊያቅተው ይችላል። (ቃለ መጠይቅ 5/11/2011 ዓ.ም፤ 7/11/2011 ዓ.ም፣ 10/11/2011 ዓ.ም)።

ይህኑኑ ሀሳብ አቶ ታደሰ ቀንኣ እንዲህ በማለት ያጠናክሩታል።

> ሙሽሮቹ ወደ ጫጉላ ቤት ሲገቡ ጀምሮ ሁሉም ሰው የምስራቹን በጉጉት ይጠባበቃል።ሙሽራዋ ድንግል መሆኗ በተመረጠችው ሴት ተረጋግጦ ሚዜዎች እየዞሩ ሲጨፍሩ ቁጭ ብሎ የሚመለከት የለም፤ ሁሉም ደስተኛ ይሆናል። በእልልታ፣ በሆታ፣ ስጦታ በመስጠት፣ በተለያዩ ጭፈራዎች ሁሉም ይሳተፋል። እናቶች በደለጋ (Dalagaa)፣ወጣቶች በሲርባ ዱርባ (Sirbaa Durbaa) ምኑ ከምን ይለያል? ሚዜዎች ከሁሉም ሰው የተሻለ ነገር(ዳጎስ ያለ ገንዘብ፣ ጊደር፣ ወይፈን፣ መሬት) ለመቀበል የሚያደርጉት ሙከራ እንኳን ለወላጅ ዘመድ ቀርቶ ለባዕድም ትልቅ ደስታ ይፈጥር ነበር (ቃለ መጠየቅ 7/11/2011 ዓ.ም)።

በ15/11/2011 ዓ.ም. በተደረገ ቡድን ተኮር ውይይትም ሙሽሪት ድንግል ሆና ከተገኘች አዳራሹ በእልልታ፣ በጭፈራ እና በደስታ በከፍተኛ ሁኔታ ይደምቅ እንደነበር ተረጋግጧል።

ሙሽሪት ድንግል ሆና ካልተገኘች ግን ሚዜዎች ይደናገጣሉ። ሙሽራው በጣም ስለሚናደድ ጫጉላ ቤቱን ዘግቶ ሲገርፋት ያመሻል። በመጨረሻም ከአካባቢው ለመጥፋት ሙከራ ያደርጋል። የልጁ ቤተሰቦችም ልጅቷን ወደቤተሰቦቿ ለመሸኘት ይመካከራሉ። በዚህ መካከል ሽማግሌዎች ጉዳዩን እንዲያዉቁ ይደረጋል። ከዚያም ሽማግሌዎች በጉዳዩ ጣልቃ በመግባት የማግባባት ስራ ይሰራሉ። ምክንያቱም ጋብቻው የዘር ሀርግ በመጠናናት ስለተመሰረተ የሚፈርሰው የሁለቱ ጥንዶች ትዳር ብቻ ሳይሆን ተፈላልገው በጋብቻ ዝምድና የፈጠሩት ወላጆችም ይለያያሉ። ስለዚህ ሽማግሌዎች ለሙሽራዉ ሌላ ሚስት እንደሚያጋቡት ቃል በመግባት ለጉዳዩ እልባት ይሰጡታል። ይህም የሚሆነው በአካባቢው ማህበረሰብ ባህል መሰረት፤ አንድ ወንድ ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት ስለሚችል ነው። በዚህ ጊዜ ደግሞ ሁሉም ሰው በሁኔታው ስለሚደናገጥ አዳራሹ ቀዝቃዛ ይሆናል። በሌላ መልኩ በባህሉ መሰረት ሙሽሪት ድንግል ሆና ካልተገኘች ከቤተሰቦቿ በተላኩ ወጣቶች

የተሸረፈ ብርሌ ወደ ቤተሰቦቿ ቤት ይላካል። ነገር ግን እነዚህ ወጣቶች ስለሚሳቀቁ ወደሙሽሪት ቤተሰብ ቤት ለመሄድ አይደፍሩም። ብርሌ በማህበረሰቡ ለየት ያለ ክብር ይሰጠዋል። ለዚህም ማሳያ የሚሆነው ቁሱ በማህበረሰቡ ያለው የአገልግሎት ደረጃ ነው። የብርሌ አገልግሎት ለተከበረ  መጠጥ መጠጫነት ሲሆን መጠጡ የሚቀርበው ለተከበረ ሰውና በተከበረ አውድ ነው። በብርሌ ጠጅ ይጠጣል። ጠጅ ደግሞ የመኳንንት፣የነገስታትና በአጠቃላይ የተከበሩ ሰዎች መጠጥ ነው ተብሎ ይታመናል። ይህ መጠጥ ለሰርግ ታዳሚዎችም ሆነ በነገስታት ቤት እንዲሁም ለበዓላት ለነዚህ የተከበሩ ሰዎች የሚቀርበው በብርሌ ነው። ምክንያቱን ቁሱ የመቅረቢያ አውዱም የተመረጠ በመሆኑ ነው። ይሁን እንጂ ቁሱ ተሰባሪ በመሆኑ እንደ አገልግሎቱ ሁሉ ሲቀመጥ ጥንቃቄን ይሻል። በመሆኑም በማህበረሰቡ አንዲት ሴት ልጅ ድንግልናዋን ጠብቃ ለትዳር ስትበቃ ያልተሸረፈ ብርሌ፣ በተቃራኒው ድንግልናዋን ጠብቃ ካልተገኘች የተሸረፈ ብርሌ ለቤተሰቦቿ ይላካል። ይህ የተከበረ እቃ ከሌሎች ቁሶች ተመርጦ ለዚህ ተግባር እንዲወል መደረጉ የድንግልናን ክብር በጉልህ ያሳያል። ምክንያቱም ቁሱ ከአቀማመጡ አንጻር በትንቃቄ ከተያዘ ረጅም ጊዜ መቆየት የሚችል መሆኑ፣ ከአገልግሎት አንጻርም ለተከበሩና ለተመረጡ ሰዎች የሚቀርብ መሆኑ እንዳለበት ይታመናል። በማህበረሰቡ እምነት ደግሞ አንዲት ሴት ልጅ ድንግልናዋን መስጠት(ማስረከብ) ያለባት በቤተሰቦቿ በጥንቃቄ ለተመረጠ ሰው ሲሆን ጊዜው ደግሞ በተከበረ ዕለት ማለትም በሰርጓ ቀን መሆን እንዳለበት መታመኑ ቁሱ ለዚህ ተግባር የዋለበትን ምክንያት ያሳያል።

ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ላልበቁ ሴትች የነበረውን የአከባበር ሁኔታ አቶ አሰፋ ጉደታ እንዲህ ይገልጹታል።

> ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት በነበረበት ዘመን በአጋጣሚ ከሺ ሴት አንድ እንኳ በሰርጓ ዕለት ድንግል ያልሆነች ሴት አትገኝም ነበር። ምክንያቱም ማህበረሰቡ ለሥርዓቱ  የሚሰጠው ዋጋ ከፍተኛ ስለነበር ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ባህላቸውን አክብረው እራሳቸውን ይጠብቁ ነበር። ከዚህ ይልቅ በዛን ዘመን አንድ ወጣት አንድን ሴት ልጅ ከወደደና እሷ ካልወደደችውና ሊያገባት ከፈለገ ይጠልፋታል። በሌላ በኩል ደግሞ ወጣቶቹ (ወንድና ሴት) ተዋደው ቤተሰብ ጋብቻውን ካልፈቀደ አሊያም ልጁ ለመደገሻ ገንዘብ ከሌለው ሁለቱ ወጣቶች በአሴና (Aseenna) የጋብቻ አይነት ይጋባሉ።

በነቀታ (Naqata) የጋብቻ አይነት ጋብቻ የፈጸመች ሴት ድንግል ሆና መገኘቷ የግድ ነበር። ሆና ካልተገኘች የትዳር አጋሯ ምሽቱን "ለማን አስረክብሽው ነው? እኔንና ቤተሰቦቼን የደፈረው ማነው? መጀመሪያ ለምን አልተናገርሽም" እያለ በአለንጋ ሲገርፋት ያመሻል። የአዳራሹ ድባብም ቀዝቃዛ ይሆናል።ድንግል ሳትሆን ያገባችን ሴት የባሏ ዘመዶች "ክብራችንን አሳልፋ ለሌላ ሰው ሰጥታለች" ብለው ስለሚያምኑ በጣም ይጠሏታል። በመሆኑም ትዳሩ ዘለቄታ አይኖረውም (ቃለ መጠየቅ 12/11/2011 ዓ.ም)።

ከላይ ከተገለጹት ሀሳቦች የምንረዳው ማህበረሰቡ ለድንግልና ያለው ቦታ ከፍተኛ በመሆኑ አንዲት ሴት ልጅ ደንግል ሆና ለትዳር ስትበቃ ደስታቸውን እና አክብሮታቸውን በሥርዓተ ከበራው ላይ በተለያየ መልኩ ይገልጹላታል። በተቃራኒው ድንግልናዋን ጠብቃ ለትዳር ካልበቃች ማህበረሰቡ በእጅጉ እንደሚያወግዛት እና በባልዋ ላይ በፈጠረችው ስነ ልቦናዊ ተጽኖ አካላዊ ቅጣት እንደሚደርስባት ያሳያል።

### 4.1.2.2 አርጋ ሚዜ (Argaa Minzee)

የሙሽሪትን ድንግል መሆን ምክንያት በማድረግ ሚዜዎች ጨፍረው ከሙሽራው እና ከሙሽሪት ቤተ ዘመዶች የሚሰበስቡት ስጦታ አርጋ ሚዜ (Argaa Minzee) ይባላል። በዚህ ሂደት ሚዜዎች የተለያዩ ስጦታዎችን ከሙሽሮቹ ቤተሰቦች ይሰበስባሉ። ምሽቱን (በሙሽራው ቤተሰብ ቤት) ምስራቹን ለማረጋገጥ የተቀመጠችው ሴት የደም ሽማውን አምጥታ ለሚዜዎች እንደሰጠች ሚዜዎች ጭፈራ እና ስጦታ መቀበል የሚጀመሩት ከሙሽራው አባትና እናት ነው።አባትና እናት በአብዛኛው የሚሰጡት ጊደር ነው። ጊድር የሚሰጥበት ምክንያት ወልዳ ተራብታ ሀብት ትሆናለች ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። ጊደር ከሌላቸው ወይፈን ይስጣሉ ይህም የሚሆነው ወይፈኑ ከበሬ በተሻለ ብዙ ጊዜ ስለሚታረስበት ነው። ቤተሰቡ ጊደር ወይም ወይፈን ከሌላቸው ሁለት እግር ይሰጣሉ። ማለትም የጊደር ወይም የወይፈን ግማሽ ለመስጠት ቃል ይገባሉ። በዚህ መሰረት ሁሉም የሰርጉ ታዳሚዎች ለሙሽሮቹ ስጦታ ይሰጣሉ። ይህንን ሀሳብ በተመለከተ ወ/ሮ አልማዝ ደጀኔ፣ ወ/ሮ ፋናዬ ወርቁ እና አቶ ታደሰ ሁንዴ እንዲህ ይገልጹታል፡፡

ሥርዓተ ከበራው በነበረበት ወቅት ምሽት ሚዜዎች ምስራቹን (የደም ሽማውን) ይዘው ሲጨፍሩ ጭፈራውን የሚጀምሩት ከሙሽራው እናት እና አባት ፊት ነው።

እናት አባት የሚሰጡት ጊደር ወይም ወይፈን ነው። ብዙ ጊዜ እንዲሰጡ የሚፈለገው ጊደር ነው። ካልሆነ እንዳቅማቸው ወይፈንም፣ በሬም፣ በግም፣ ብርም ይሰጣሉ። በዚህ ሁኔታ ሚዜዎች ከተሰበሰበው ታዳሚ አስር ብርም፣ አምስት ብርም፣ አንድ ብርም፣ አምስት ብርም ሳንቲምም ቢሆን ይወስዳሉ። ሚዜዎች ማንንም አያልፉም የለኝም ካለ ከልብሳቸው ቁልፍ ቆርጠው እንዲሰጡ ያደርጋሉ። ምንም አይነት ገንዘብ አይናቅም ብቻ ሁሉም ያቅሙን እንዲሰጥ ያደረጋል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ምሽት ከሰርገኛው ጋር  ከሙሽራዋ ቤተሰብ የተላኩት ወጣቶች ሙሽሪት ድንግል ከሆነች ጠዋት በለሊት ወደ ሙሽሪት ቤተሰብ ቤት በመሄድ የምስራቹን ያበስራሉ። ከዚያም ጎረቤት እና ዘመድ አዝማድ ለምስራቹ ስጦታ ለመስጠት ሚዜዎቹን ይጠባበቃሉ። ሚዜዎቹም  ምንም ያልተሸረፈ  ብርሌ ይዘው እየጨፈሩ ወደ ሙሽሪት ቤተሰብ ቤት ይሄዳሉ።ታዲያ ሚዜዎች እየጨፈሩ ሲመጡ የሴትዋ ቤተ ዘመድ ከአባት እና እናት ጀምሮ በዝምድና ተዋረድ ይቀመጡና በእልልታና በሆታ ይቀበሏቸዋል። ሚዜዎቹም የደም ሸማውን እያሳዩ “ምስራች” ሲሉ የተቀመጡት ደግሞ “ኬሳ ሲላቹ” ይሉዋቸዋል። “ምስራች” የሚለው ይሄው የምስራቹ የሚለውን እሳቤ ሲኖረው “ኬሳ ሲላቹ” የሚለው ደግሞ ከውስጥ ስጦታ እንስጣችሁ? የሚለውን እሳቤ ያሳያል። በመቀጠል ሚዜዎች እንዲህ እያሉ ያዜማሉ።

| **በመገኛ ቋንቋ** (Afaan Oromootin) | **የአማርኛ ትርጉም** |
|---|---|
| Yaa abaaboo yaa abaaboo kooo | አበባ አበባዬ |
| Gurbaan keenya daraareera | ልጃችን አብቧል |
| Intallis milkoofteetti | ሙሽሪትም ተሳክቶላታል |
| Daraarteetti | አብባለች |
| Milkoofteetti | ተሳክቶላታል |
| Gurbaanis gurbaa | ወንዱም ወንድ ነው፣ |
| Intallis durba | ልጅቷም ድንግል ናት። |

ከዚያ እንደሙሽራው ቤተሰብ ሁሉ የሙሽሪት አባት እና እናት ጊደር ወይም ወይፈን ይሰጣሉ። ሌላውም የሙሽሪት ቤተ ዘመዶች አቅማቸው በፈቀደላቸው መጠን ከመሬት እስከ ልብስ ቁልፍ ድረስ ይሰጧቸዋል (ቃለ መጠይቅ 5/11/2011 ዓ.ም፤ 7/11/2011 ዓ.ም፤ 12/11/2011 ዓ.ም)።

ከላይ ከተገለጸው ሀሳብ የምንረዳው ሙሽሪት በሰርጓ ዕለት ድንግል ሆና ስትገኝ የሙሽራውና የሙሽሪት ቤተሰቦች እኩል ተሳትፎ እንዳላቸውና፤ ማህበረሰቡም የሙሽሪትን ጨዋነትና ክብር አስመልክቶ ለሙሽሮቹ የተለያዩ ስጦታዎች እንደሚያበረክቱላቸው ያሳያል።

### 4.1.3 ድህረ ሰርግ

በባህሉ መሰረት ሙሽሪት እስከ አምስተኛው ቀን ከጫጉላ አትወጣም፡፡ በአምስተኛው ቀን በጠዋት ተነስታ ቡና ታፈላለች። ጎረቤት ይጠራል። ዘመዶቿም ሊጠይቋት ይመጣሉ። በዕለቱ ዘመዶቿና ጎረቤቶቿ ባሉበት ለሙሽሪት የክብር ስም ይወጣላታል። ስሙን የሚያወጣው የልጁ እናት እና አባት ናቸው። ይህ ስም ከወጣ ቀን ጀምሮ ጎረቤቱ እና ቤተሰቡ ሙሽሪትን በዚህ ስም ይጠሯታል። ሊጠይቋት የመጡት ዘመዶቿ መልስ የሚመለሱበትን ቀን አስቆርጠው ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ። በመልሱ ቀን ሙሽራው በግ ይዞ ሲሄድ የሙሽራዋ ቤተሰብ ደግሞ ምግብ  አዘጋጅተው ይጠብቃሉ። በመልሱ ቀን ሚዜዎቹ አብረው  የሚሄዱ  ሲሆን አንድ ቀን አድረው ይመለሳሉ። ከዚህ በኋላ ሁለቱ ቤተሰቦች ተዛመዱ ማለት ነው።

## 4.2 ሲርባ ዱርባ (Sirba Durba) እና ድንግና

በኢሉአባቦር ዞን በዶረኒ ወረዳ የሚኖረዉ ኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ ከሚዘወተሩ ወይም ከሚታወቁ ባህላዊ ጭፈራዎች አንዱ ሲርባ ዱረባ (Sirba Durba ) ነው። ይህ ጭፈራ በአብዛኛው በበዓላት ወቅት በተለይ በጥምቀት፣ በፍልሰታ፣ በመስቀልና በመሳሳሉት የሚጨፈር ሲሆን በሰረግ ወቅትም ለሰረግ ማድመቂያነት ይጨፈራል። ወቅቱም በአብዛኛው ከምሽቱ አንድ ስዓት እሰከ ሌሊቱ ዘጠኝ ስዓት ይጨፈራል። በቀን የሚጨፈረው ለሰረግ ማድመቂያነት የሚጨፈር ከሆነ ብቻ ነው።ይህም ባህላዊ ጭፈራ ባላገቡ ወጣቶች ብቻ እና በምሽት የሚጨፈር በመሆኑ ከሌሎች የአካባቢው ባህላዊ

ጭፈራዎች ይለያል፡፡ በባህሉ መሰረት ይህን ባህላዊ ጭፈራ የምታቋቁመው ያላገባች ወጣት ሴት ናት። ሲረባ ዱረባ (Sirba Durba ) ወይም የልጃገረዶች ጭፈራ የሚለውን ስያሜ ያገኘውም ከዚሁ በመነሳት እንደሆነ ይነገራል። በመሆኑም በባህሉ መሰረት ጭፈራውን እንድታቋቁም ከአባቷ ፍቃድ ያገኘች ልጃገረድ ጭፈራው ምሽት በመሆኑ የተኛ ሰው እንዳይረበሽ ከመኖሪያ ቤት እርቃ፣ የሰው ማሳ እንዳይረጋገጥ እህል ያልተዘራበት ሜዳማ ቦታ ፈልጋ ጭፈራውን ታቋቁማለች።

በመጀመሪያ ዘፈኑ ከመጀመሩ በፊት የሰፈር ወጣቶች ምሽት የሚገናኙበትን ቦታ በገበያ፣ በተለያዩ ማህበራዊ መገናኛ ቦታዎች ይቀጣጠራሉ። የምሽት ጭፈራውን ለመጨፈር የሚያስፈልጉ የሙዚቃ መሳሪያዎች ለሴቶች ድቤ (Dibbee) ለወንዶች ደግሞ ዱላ ወይም ጦር ናቸው። ነገር ግን፣ ጦር ስለታማ ሰለሆነ ብዙም ተመራጭ አይደለም። ምሽት ዘፈኑን የምታቋቁመው (የምታስጀምረው) ልጃገረድ ከጎረቤት ልጆች ጋር በመሆን "ድቤ" ስትመታ የቀሩት የጎረቤት ልጆች በፉጨት፣ ፉጋ (እንደዋሽንት ያለ የሙዚቃ መሳሪያ) በመንፋት ወጣቶች ከየአካባቢው ወደ ጭፈራው ስፍራ እንዲሰበሰቡ ያደረጋሉ። ከዚያም ጭፈራው ይጀመራል። የጭፈራው የአጨፋፈር ስልትም የተለያየ ሂደት አለው። በመጀመሪያ ወንዶች በአንድ በኩል ሴቶች በሌላ በኩል በሁለት ረድፍ ይቆማሉ። የወንዶቹና የሴቶቹ ቁጥር እኩል መሆን አለበት፡፡ ከዚያም ሴቶች ቀስ አደርገው ድቤያቸውን "ድብ ድብ" እያደረጉ ሲመቱ፣ወንዶች ደግሞ ዱላቸውን በደረታችው ትክክል በመያዝ "ሂ ሂ ሂ" በማለት ይጀመራሉ። በዜማ የሚባሉ ሰነ ቃላዊ ግጥሞችን ልጃገረዶቹ እና ወንዶቹ በየተራ እየተቀባበሉ ይጨፍራሉ። አጨፋፈሩ ቀዝቀዝ ብሎ ይጀመረና እየደራ ሲሄድ ሴቶች ሹሩባቸውን እያዘናፈሉ ከፊት ወደኋላ አንገታቸውን ሲያወዛውዙ፣ ወንዶቹ ደግሞ መላ አካላቸውን እያንቀሳቀሱ በጋራ ይጨፈራሉ።

 

ፎቶ 4. "የሲርባ ዱርባ" የአጨፋፈር ስልት (የዶረኒ አዊሶ ሰደን ቡድን) ከሰነድ (Mogos, 2011 E.C. )

ጭፈራው እየደመቀ ሲሄድ የሁለቱም ጾታዎች አካላዊ እንቅስቃሴ እየጨመረ ይሄዳል፡፡ በዚህ ጊዜ ሁለቱም ጾታዎች በርከክ በማለት ተጠጋግተው ይጨፍራሉ፡፡ ከዚያ በኋላ አንዱ አብራው የምትጨፈረውን በሌለኛዋ እየቀያየረ በጋራ ይጨፍራሉ። አሁን ጭፈራው የበለጠ ይደምቃል። ልጃገረዶቹ አንገታቸው ተበጥሶ የሚወድቅ እስኪመስል ድረስ እያንቀሳቀሱ ድቤያቸውን በፍጥነት ይመታሉ፣ ወንዶቹ ደግሞ መላ ሰውነታቸውን እንደ እስክስታ አይነት ያንቀጠቅጣሉ። ነገር ግን በቅይይሩ ወቀት የዘመድ ልጅ እና የጎረቤት ልጅ ካጋጠመች አብሮ መጨፈር ፍጹም የተከለከለ ነው፡፡ ምክንያቱም የአጨፋፈር ስልቱ የስጋ ዝምድና ካላቸው ጋር አብሮ ስለማይሄድ ነው። አጨፋፈሩ በአብዛኛው ከፍቅረኛ (ከከንፈር ወዳጅ) ጋር ሲሆን አልፎ አልፎ ግን የከንፈር ወዳጅ ያልሆኑትም በጋራ ይጨፍሩታል፡፡ በተለይ ሴት እየተቀያየሩ በሚጨፍሩበት ወቅት ይህ ነገር ይፈጠራል። አንድ ወንድ ዘፈኑ ደርቶ እየተጨፈረ ሳለ በመሃል ፍቅረኛውን (የከንፈር ወዳጁን) ወስዶ ሊሰማት ይችላል። ጭፈራው ሲጠናቀቅ ግን ሁሉም ፍቅረኛሞች (የከንፈር ወዳጆች) ጥንድ ጥንድ በመሆን ለየብቻ ተነጥለው በያዙት ነጠላ ወይም ሻሽ በመጠቅለል ይሳሳማሉ። በዚህ ወቅት አንዳንድ ፍቅረኛ (የከንፈር ወዳጅ) የሌላቸው ወንዶች በቅናት መንፈስ ጸብ ሊያስነሱ ይችላሉ። ነገር ግን ጸቡ ከጓደኛ እርቅ የዘለለ አይሆንም። ፍቅረኛሞቹ ሲሳሳሙ ከረሜላ ወይም ኮረሪማ በአፋቸው በመቀባበል ይሳሳማሉ። ኮረሪማውን ጥሩ ጠረን ለመፍጠር ሲገለገሉበት ከረሜላው ደግሞ ጣዕም ለመፍጠር ሲባል ይጠቀሙበታል። ሲሳሳሙም ከንፈራቸውን እርስበርስ በማጣጣም ይሳሳማሉ (በሰነድ ፍተሻ ከተገኘ ከቪድዮ የተወሰደ መረጃ)።

ባህላዊ ጭፈራው ወጣት ሴቶች ከንፈር ወዳጅ በመያዝ፣ በመሳሳም እና እንደፈለጉ እንዲጨፍሩ ማድረጉ ወጣቶች ባህሉ ያደላቸውን ከፍተኛ ነጻነት መሆኑን ያመለክታል። በተቃራኒው ደግሞ ጭፈራው አጨፋፈሩ  ከከንፈር ወዳጅ ጋር መሆኑ ያውም ጭፈራው ሲደምቅ መሳሳማቸው ፣ ጊዜው ሌሊት መሆኑ እና ትልቅ ሰው በሌለበት ወጣቶችን የወሲብ ፈላጎታቸውን በእጅጉ ይፈታተናቸዋል። ይህ ደግሞ ብሂረሰቡ አንድ ሴት ልጅ ድንግልናዋን ጠብቃ ለትዳር መብቃት እንዳለባት ያስቀመጠውን ባህላዊ ደንብ ከሚጥስበት አጋጣሚዎች

እንዱ ይሆናል። ወጣቶቹም እነዚህን ሁለት ባህላዊ ጽንፎች ለማስታረቅ ሲሉ ከፍተኛ ፈተና ውስጥ ይገባሉ። ይሁን እንጂ ወጣቶቹ የማህበረሰቡን ባህላዊ እሴት በማክበር እራሳቸው ሲጠብቁ ማህበረሰቡ ደግሞ ወጣትነት ቁጥጥር የሚሻ መሆኑን በመገንዘብ ወጣት ልጆቻቸው ለመከታተል የሚያስችሉ መንገዶችን አዘጋጅተዋል። ከነዚህ መንገዶች መካከል ወጣቶች ሴቶች ሲርባ ዱርባ (sirba durbaa) ሲሄዱ ከታላቅ መንድማቸው ወይም በጣም ከሚያምኑትና ሊጠብቃት ይችላል ብለው ከሚያስቡት የጎረቤት ልጅ ጋር እንድትሄድ ትደረጋለች። ይህ የሆነበት ምክንያት አንድም በባህሉ መሰረት አንድ ሴት ለትዳር መብቃት ያለባት ድንግልናዋን ጠብቃ መሆን ስላለበት በስሜት ተገፋፍታ ከጋብቻ በፊት ግብረ ስጋ ግንኙነት በመፈጸም የራሷንም ሆነ የወላጆቿ ወግ ማዕረግ እንዳትጥስ ለማድረግ ጠባቂ እንዳለባት በስነ ልቦና እራሷን እንድታሳምን ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ ጭፈራው በምሽት በመሆኑ ብቻዋን ከሄደች ለተለያዩ ችግሮች ትጋለጣለች በሚል ስጋት ነው። ይህንን ሀሳብ በተመለከተ አቶ ታደሰ ሁንዴ እንዲህ ይገልጹታል።

> ባህላዊ ጭፈራው አሁን አሁን ሙሉ በሙሉ ጠፍቷል በሚባልበት ደረጃ ላይ እየደረሰ ነው። በድሮ ጊዜ በዚህ ወረዳ በጣም በሰፊው ይጨፈር ነበር። ታዲያ በዚያ ጊዜ አንድ ሴት ልጅ ሲርባ ዱርባ (sirba durbaa) ስትሄድ ይዟት የሚሄደዉ ታላቅ ወንድም፣ የቅርብ የዘመድ ልጅ ወይም የሚታመን የጎረቤት ልጅ ብቻ ነው። ሴት ልጅ ቤተሰቦቿ ከማያምኑት ሰዉ ጋር ሲርባ ዱርባ (sirba durbaa) ከሄደች ነዉር እንደፈጸመች ይቆጠራል። በስህተት እንኳ ይህን ተግባር ከፈጸመች የተረገመች ትሆናለች ተብሎ ይታመናል። ይዞ የሚሄደው ወጣትም ልጅቷን ከጥቃት የመከላከል ሃላፊነት አለበት። የአንድ ሰፈር ልጅ፤ የሌላ ሰፈር ልጅን ለመተናኮስ ሙከራ ካደረገ ልጅቷን ይዞ የመጣዉ ወጣት ጓደኞቹን በማስተባበር በዱላ ይደበድቡታል። በዚህ ምክንያት የቡድን ጠብም ሊነሳና የጭፈራ ሥርዓቱ ሊቋረጥ ይችላል። ይህ በእንዲህ እያለ ሲርባ ዱርባ በነጻነት የፍቅር ጓደኛቸውን የሚያገኙበት በመሆኑ አብሮ የመሳሳም፣ የመጨፈርም መብት አላቸው። ከመሳሳም የዘለለ ሌላ ነገር መፈጸም (ግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸም) ነውር መሆኑን ስለሚያውቁ ሁሉም በሃላፊነት ያከናዉናሉ። አንድ ወንድ የከንፈር ወዳጁን ሊያገባም ላያገባትም ይችላል። በመሆኑም መሳም እንጂ ፈጽሞ ወሲባዊ ግንኙነት ሊፈጽም አይችልም። በባህሉ መሰረት ሴት ልጅም ከአረማመዷ ጀምሮ ራሷን ጠብቃና ተቆጥባ እንድትኖር ይታመናል። ስለዚህ ባህሏን አክብራ ለሊት እንኳን ስትጨፍር ብታድር

የማህበረሰቡን ባህላዊ እሴት ጠብቃ ትኖራለች። ባህሏን የማታከብር ሴት ልጅ የተዋረደችና የጋብቻ ጥያቄ እንኳን የሚቀርብላት እስከማጣት ልትደርስ ትችላለች። በሌላ መልኩ ደግሞ ሴት ልጅ ከጋብቻ በፊት የግብረስጋ ግንኙነት ከፈጸመች የቤተሰቦቿን ክብር አዋርዳለች ስለምትባልና ከዚህ ውግዘት ለመዳን ራሷን ትጠብቃለች። አንዲት ሴት ልጅ ከከንፈር ወዳጇ ጋር እንኳን ብትተኛ ምንም ነገር እንዳትፈጸም ትጠነቀቃለች። ወንዱም ቢሆን የፈለገውን ያክል በስሜት ቢነሳሳ የከንፈር ወዳጁን ከመሳም የዘለለ ወሲባዊ ግንኙነት አይፈጽምም። ምክንያቱም በባህሉ መሰረት ከጋብቻ በፊት ግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸም አስነዋሪ በመሆኑ በሀገር ሽማግሌዎች ይረገማሉ። በመሆኑም ማህበረሰቡም አንድ ሴት ልጅ ይህንን ከፍተኛ ፈተና ተቋቁማ ለትዳር በመበቃቷ አድናቆቱን እና ሙገሳውን በጋብቻ ወቅት በስጦታ ያረጋግጥላታል። (ቃለ መጠይቅ 12/11/2011 ዓ.ም)

ይህንኑ ሀሳብ ወ/ሮ ደስታ ማሞ እንዲህ ያጠናክሩታል፡፡

ሲርባ ዱርባ (sirba durbaa) ከማዝናናቱ ባሻገር ለወጣቶች ከነጻነት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው። ምክንያቱም በእኛ ጊዜ በዚህ አካባቢም ያሉ ሌሎች ብሄሮችም ሆኑ በአገር ደረጃ ለሴቶች የሚሰጠው ነጻነት ዝቅተኛ ነበር። ነገር ግን በዚህ ባህላዊ ጭፈራ አንድ ሴት ልጅ በነጻነት፣ የከንፈር ወደጅ የምትይዝበት እና እንደፈለገች ጨፍራ የምትገባበት ባህል የሰጣት ነጻነት ነው። ታዲያ ባህሉ ለሴቶች ነጻነት ይስጥ እንጂ ሴቶች እራሳቸውን እንዲጠብቁ ደግሞ የራሱ የሆነ መጠበቂያ ስልት አለው። ለምሳሌ ማንኛዋም ሴት የፈለገችውን ያህል በነጻነት እንደፈለገች ብትጨፍርም ጨዋ(ድንግል) ሆና ለትዳር መብቃት ይጠበቅባታ። ያንን ሆና እንድትገኝ ሌሎች ወጣቶች እንዳይተናኮሏት ወደ ጭፈራ ስፍራው ስትሄድ ወላጆች የሚልኳት ከታላቅ ወንድም ወይም ከሚያምኑት የሰፈር ልጅ ጋር ሲሆን እነዚህ አማራጮች በሌሉበት ከጭፈራው የምታገድበት ሁኔታም ነበር (ቃለ መጠይቅ 13/11/2011 ዓ.ም)።

በሌላ መልኩ ደግሞ ባህላዊ ጭፈራው ምንም እንኳን ከነጻነት አንጻር ከፍተኛ ሚና ቢኖረውም ወጣቶችን ለወሲብ የመገፋፋት አቅምም እንዳለው ወ/ሮ አልማዝ ደጀኔ እንዲህ ይገልጹታል።

ሲርባ ዱርባ (sirba durba) በሚጨፈርበት ወቅት አጨፋፈሩ ሴትና ወንድ ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚከወን ነው። ከጭፈራ በኋላ መሳሳም አለ። ሌላው አንድ ልጃገረድ ሁሌም አብሯት የሚጨፍር የራሷ የሆነ ወንድ አላት።ይህ ሰው ከጭፈራውም ባለፈ የከንፈር ወዳጇ ነው። የከንፈር መዳጅ ደግሞ ሊያገባትም ላያገባትም ይችላል። ምክንያቱም በድሮ ጊዜ የወጣቶችን የጋብቻ ሁኔታ የሚወስኑት ወላጆች ስለነበሩ ያን ሰው ላታገባው ትችላለች። ይሁን እንጂ እሷም ሆነች የከንፈር ወዳጇ ባህሉን በሚገባ ስለሚያውቁት (የባህላዊ እሴትን) ስለሚጠብቁ ድንግልናዋን ሳትጠብቅ ለትዳር የበቃች ሴት ምን ያህል በማህበረሰቡ ትችትና ነቀፋ እንደሚደርስባት እና ወላጆቿንም እንደምታሶቅስ ስለሚያዉቁ ለወላጆቿና ለእሷ ክብር ሲሉ ሁለቱም እራሳቸውን ከወሲብ ይቆጥባሉ። እንዲውም የከንፈር ወዳጇ ሌሎች ወንዶች እንዳይተናኮሷት እንደ ጠባቂ ይሆናት ነበር (ቃለ መጠይቅ 05/11/2011 ዓ.ም)።

ከላይ ከተገለጹት ሀሳቦች እንደምንረዳው ባህላዊ ጭፈራው ምንም እንኳን ወጣቶች ነጻነታችውን የሚያውጁበት ቢሆንም ወጣት ሴቶች ባህል ያስቀመጠላቸውን ድንግልናን ጠብቆ ለትዳር የመበቃት ገደብ በከፈተኛ ሁኔታ ይፈታተናል፡፡ ምክንያቱም ወንድ እና ሴት አንገት ለአንገት ተጠጋግቶ መጨፈር፣መሳሳም፣ከረሜላ እና ኮረሪማ የወሲብ ስሜትን የመቅስቀስ ባህሪ ያላቸው ነገሮች ናቸው። በሌላ መልኩ ደግሞ በተገለጹት ሀሳቦች እነዚህ ሁለት የሚቃረኑ ጉዳችዮን ማህበረሰቡ ለማጣጣም የሚጠቀምባቸውን መንገዶች በወቀቱ ወጣቶችም እንደሚቀበሉትና ተግባራዊ እንደሚያደርጉት ያሳያል።አንድ ግለሰብ ወሲብ የሚፈጽመው ያለበትን ማህበረሰብ ባህል ተከትሎ ነው። በመሆኑም የወሲባዊ ዝንባሌ ልምዳችን ቅርጽ የሚይዘው ከሚኖርበት ማህበረሰብ አስተሳሰብ የሚመነጭ ነው።

በዚህ አስተሳሰብ መሠረት የሰው ልጅ ወሲባዊ ፍላጎት ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ቀስ በቀስ እያደገ የሚመጣ እና በማህበረሰቡ ባህል መሠረት የሚፈጸም መሆኑን Kantor (1999) ይገልጻል። በመሆኑም ወጣቶች ያደጉበት ማህበረሰብ የሰጣቸውን በነጻነት የመጨፈር፣ የመሳሳም ሁኔታዎች እራሳቸውን ጠብቀው በጥንቃቄ እንደሚጠቀሙና ባህል ያስቀመጠባቸውን ድንግልናን ጠብቆ ለትዳር መብቃት ደግሞ የባህል ቃልኪዳናቸውን በማክበር በጨዋነት ለትዳር እንደሚበቁ ያሳያል።

## 4.3. የኢሉባቦር ዞን በዶረኒ ወረዳ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት ማህበራዊ ጠቀሜታ

በኢሉአባቦር ዞን፣ በዶረኒ ወረዳ የኦሮሞ ማህበረሰብ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት ትልቅ ማህበራዊ ፋይዳ አለው። በማህበረሰቡ ባህል መሰረት ሴት ልጅ ሴት እስከጋብቻ ዕለቷ ድንግልናውን ጠብቃ ከተገኘች በአካባቢው ማህበረሰብ ከፍተኛ ክብር እና ሙገሳ ታገኛለች። በተቃራኒው ድንግልናዋን ጠብቃ ለጋብቻ ዕለት ባትገኝ የመገረፍ ቅጣት ይደርስባታል። ማህበረሰቡ ድንግል ለሆነች ሴት የሚከውነው ሥርዓተ ከበራ ማህበራዊ አንድነት የመፍጠር ፋይዳው ከፈተኛ ነው።

### 4.3.1. ጠንካራ ማህበራዊ ግንኙነትን ከመፍጠር አኳያ ያለው ጠቀሜታ

ማህበረሰቡ አንድነቱን ከሚያጠናክርባቸው መንገዶች አንዱ ሰርግ ነው። ሰርግ ለማህበረሰቡ የእርስ በርስ ግንኙንት መጠናከርና ማህበራዊ ህይወትን ከማስተሳሰር ረገድ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ከበራ ሁልጊዜም የሚከበረው በሰርግ ሥርዓት ጊዜ ነው። በሰርግ ጊዜ ደግሞ ሰዎች መሰባሰባቸው አይቀሬ ነው። በዚህ ጊዜ ደግሞ ስራ አብሮ የመስራቱ፣ አብሮ የመመገቡ፣አብሮ የመጨፈሩ እድሉ ከፈተኛ ነው፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ድንግልናቸውን ጠበቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች በሚደርገው ሥርዓትም በምሽት በሙሽራው ቤተሰብ ቤት እና ጠዋት በሙሽሪት ቤተሰብ ቤት በሚደረገው የምስራች መግለጫ ሰዎች በጭፈራ፣ በእለለታ፣ ስጦታ በመስጠት በጋራ ያከብራሉ። ለምስራቹ ስጦታ ለመስጠት ተሳታፊ በመሆን የደስታው አካል መሆናቸውን ያሳያሉ። በተጨማሪም ጋብቻው የዘር ሀርግ በመጠናናት ስለተመሰረተ ጥምረቱ የሁለቱ ጥንዶች ብቻ ሳይሆን ተፈላልገው በጋብቻ ዝምድና የፈጠሩት ወላጆችም ጭምር ነው። ይህ ደግሞ በተጋቢዎች መካከል መተማመንን በመፍጠሩ የትዳር መፍረስ (ፍችን) ይከላከል ነበር። በዚህም መሰረት በህብረተሰቡ ዘንድ ጠንካራ የማህብራዊ ኑሮ እንዲኖር ያደርጋል። ይንን ሀሳብ በተመለከተ ወ/ሮ ንጉሴ ኡርጂ እንዲህ ይገልጻሉ።

> ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች በሚደረገው ሥርዓት ሁሉም በጋራ ዕለቱን ያደምቀዋል። ምሽት በሙሽራው ቤተሰብ ቤት እናቶች፣ ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች፣ህጻናት ሁሉም በጋራ ያከብራሉ። ጠዋትም በሙሽሪት ቤተሰብ ቤት

የምስራቹን ለማብሰር የተላኩ ወጣቶች ሲመጡ ለምስራቹ ለሙሽሪት ሽልማት ለመስጠት በሰርጉ ዕለት የተገኙ ዘመድ አዝማዶች፣ ጎረቤት ተሰብስበው ሁሉም ስጦታ ይሰጣሉ።ይህ ደግሞ ማህበራዊ ግንኙነት ከማጠናከር አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በተጨማሪም ሙሽሪት ድንግል ስትሆን በባሏም ሆነ በባሏ ዘመዶች ከፍተኛ ተቀባይነት ስለሚኖራት ማህበራዊ ህይወታቸው የተጠናከረ ነው (ቃለ መጠይቅ 10/11/2011 ዓ.ም) ።

ከላይ ከተገለጸው ሀሳብ የምንረዳው ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት በዕለቱ ሁሉም በሚያደርገው ተሳትፎ ብቻ ሳይሆን ድንግል ሆና በመገኘቷ በአማቶቿ ዘንድ የሚኖራት ተቀባይነት ማህበራዊ ግንኙነትን ከማጠናከር አንጻር ከፍተኛ ሚና እንዳለው ያሳያል።

## 4.3.2. ከስነልቦና አኳያ ያለው ፋይዳ

ድንግልና በሁለቱ ተጋቢዎች መካከል ያለው ስነልቦናዊ መረጋጋትና መተማመን ወይም የትዳርን መፍረስን ከመቀነስ አንጻር ጠቀሜታው የጎላ ነው። ምክንያቱም ትዳር የሚመሰረተው በሁለት ተጋቢዎች መካከል ይሁን እንጂ ስለትዳሩ መጽናትም ሆነ መፍረስ የሚኖሩበት ማህበረሰብ አመለካከት የሚፈጥረው ስነልቦናዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው። ከጋብቻ በፊት ወሲብ የፈፀሙ ሴቶች ብዙዎቹ የትዳር መፍረስ አደጋ እንዳደረሰባቸው መረጃዎች ያሳያሉ። ድንግልናን እስከ ጋብቻ ድረስ መጠበቅ የጥሩ አስተዳደግና የጨዋነት ምልክት ተደርጎ በሚወሰድበት ማህበረሰብ ውስጥም ከጋብቻ በፊት ወሲባዊ ተራክቦን የፈፀሙ ሴቶች ከድንግሎች የበለጠ ለትዳር መፍረስ የተጋለጡ ሆነው ተገኝተዋል (Kahn እና London ፣ 1991) ።

በዚህም መሰረት አንዲት ሴት ልጅ ድንግልናዋን ጠብቃ ለትዳር ስትበቃ ከአካባቢው ማህበረሰብ እና የባሏ ቤተሰብ ዘንድ የተለየ ፍቅር እና አክብሮት ታገኛለች። የሙሽራው ቤተሰቦች ልጃችንን አስከበረችው፣ አኮራችው በሚል ምክንያት ሲሆን ማህበረሰቡ ደግሞ ባህልና ወጓን አከበረች በሚል እሳቤ ነው። ይህ ደግሞ ሙሽራዋን የመረጋጋት እና በራስ የመተማመን ስሜት ስለሚፈጥር በትዳሯ ጸንታ እንድትኖር ያደርጋል። ይህ ሁኔታ በትዳራቸው እንዲጸኑ አስተዋጾው ከፍታኛ ነው።ይህንን ሀሳብ በተመለከተ አቶ ታደሰ ሁንዴ እንዲህ ይገልጹታል።

> አንድ ሴት ልጅ ድንግልናዋን ጠብቃ ለትዳር ስትበቃ የባሏ ቤተሰቦች (አማቶቿም) "እኛጋ ነው ደሟ የፈሰሰው" ብለው ከራሳቸው ዘመድ በበለጠ ይሳሱላታል፤ ይወዷታል። ሙሽራውም የፈለገው ያህል ሙያ ባይኖራት እንደምንም ያስተምሯታል እንጂ በክፉ አያነሷትም። ይህ ደግሞ ሙሽራዋ ተረጋግታ ትዳሯን እንድትመራ ከፍተኛ አስተዋጽ አለው (ቃለ መጠይቅ 12/11/2011 ዓ.ም)።

ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት ክብር ከማስገኘት አኳያም ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። ማንኛውም ወላጅ ልጁን ሲያሳድግ የሚቆጣጠረው በሁለት ምክንያት ነው። አንድም ልጆች የህይወት ልምድ ስለሌላቸው ነገሮችን ካለማስተዋል ለመጥፎ ተግባር እንዳይጋለጡ ሲሆን፣ በሌላ መልኩ ደግሞ በልጆቻቸው አማካኝነት ክብርና ዝናን ለመጎናጸፍ ነው። በመሆኑም አንድ ሴት ክብሯን ጠብቃ ለትዳር ስትበቃ ወላጆች የአስተዳደግ ጥንካሬያቸውን ስለሚያረጋግጥላቸው ክብር ይሰማቸዋል። ይህንን ሀሳብ አቶ ኢታና ማሞ እንዲህ ይገልጹታል።

> ወላጆች ለሰርግ ወጪ አውጥተው ልጃቸውን ይድራሉ። ይህንን የሚያደርጉት የተለየ ጥቅም ለማግኘት ሳይሆን ልጆቻቸውን ለማስደሰት ሲሉ ነው። ነገር ግን በምላሹ በልጃቸው መከበር ይፈልጋሉ። ክብር የሚገኘው ደግሞ በጨዋ ልጅ ነው። ምክንያቱም አንድ ሰው ልጅህን ለልጄ ብሎ በጋብቻ ሲዛመድህ ያየው ወላጅን እንጂ ልጅቷን አይደለም። ስለዚህ ልጅህ ድንግልናዋን ጠብቃ ለትዳር ከበቃች "የገሌ ልጅ" ጨዋ፣ ጠንካራ አሳዳጊ ያላት ተብለህ ትከበራለህ፤ ክብሯን ጠብቃ ካልተገኘች ደግሞ አሳዳጊ የበደላት ተብሎ ክብርህን ታጣለህ። ስለዚህ ወላጅ የሚከበረውም የሚዋረደውም በልጁ በመሆኑ ድንግል ሆና ለትዳር የበቃች ሴት ከራሷ አልፎ ለወላጅ ክብር ትሆናለች (ቃለ መጠይቅ 05/11/2011 ዓ.ም)።

ይህንን ሀሳብ አቶ ታደሰ ቀንአ እንዲህ ያጠናክሩታል።

> ወንድ ልጅ በጨጉላ ቤት ድንግል ሴት ሲያገኝ ለሱም ሆነ ለቤተሰቦቹ ትልቅ ክብር አለው። ወላጆች የምስራቹን አይተው ያላቸውን ጥሩ ገንዘብ (ጊደር፣ ወይፈን) የሚሰጡት በልጃቸው ክብርን ስላገኙ ነው። በድሮ ጊዜ ሴት ልጅ ድረህ ጠዋት የምስራች ለማሳየት ያልተሸረፈ ብርሌ ሲመጣ በአካባቢ ማህበረሰብ ክብር ታገኛለህ።

> ወንድ ልጅም ስትድር የተዛመደው ከጨዋ ቤተሰብ ነው ተብለህ ትከበራለህ (ቃለ መጠይቅ 07/11/2011 ዓ.ም)።

ወ/ሮ ንጉሴ ኡርጂ ድንግልናን ጠብቆ ለትዳር መብቃት ከራስ አልፎ ለወላጅ ያለውን ክብር እንዲህ ይገልጹታል።

> ሴት ልጅ ድንግልናዋን ጠብቃ ለትዳር መብቃቷ ለራሷ በራስ መተማመንን፣ አሸናፊነትን፣ ደስታን ሲያስገኝ ለቤተሰቦቿ ደግሞ ክብር ያስገኝላታል፡፡ በሷ ምክንያት ቤተሰቦቿ ሲደሰቱ፣ ሲከበሩ እና ዝና ሲያገኙ ማወቋ ድንግልናዋ ሲወሰድ የሚሰማትን የህመም ስሜት እንኳን እንድትረሳው እና የህመም ስሜቱን እንደትቋቋመው ያደርጋታል። ለምሳሌ የኔ ቤተሰቦች ሶስት ሴት ልጆቻቸውን በዚህ መልኩ ድረው ሶስታችንም የምስራች ልከናል። ቤተሰቦቻችንም እስካሁን ድረስ በአካባቢው ማህበረሰብ ለተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ሁሌም እየተመረጡ በልጆቻቸው ተከብረው ይኖራሉ። አሁን ሥርዓት ትኩረት መሰጠቱ ሲቀር ሁሉም ነገር አብሮ ቀርቷል (ቃለ መጠይቅ 10/11/2011 ዓ.ም)።

ድንግልናን ጠብቆ ለትዳር መብቃት ሌላው ስነልቦናዊ ፋይዳ ደስታ መፍጠሩ ነው። አንድ ወንድ ልጅ በጫጉላ ቤት አንሶላ በሚጋፈፉበት ወቅት የትዳር አጋሩ ድንግል ሆኖ ሲያገኛት የሚሰማው ደስታ ከፍተኛ ነው። ምክንያቱም ማንም ያልነካትን ሴት የግሉ እንዳደረገ ስለሚያስብ የአሸናፊነት ስሜት ይሰማዋል። ይህ ደግሞ ከፍተኛ ደስታ ይፈጥራል። ይህንን ሀሳብ በተመለከተ አቶ ታደሰ ሁንዴ እንዲህ ይገልጹታል።

> ወንድ ልጅ በጋብቻ ዕለት የትዳር አጋሩ ድንግል ሆና ሲያገኛት በቃላት የማይገለጽ ከፍተኛ ደስታ ይሰማዋል። ደስታው ወደር የለውም መንግስተ ሰማይን የወረሰ ያክል ይሰማዋል። ምክንያቱም በማንም ያልተነካች ሴት ማግኘት የተለየ እርካታ ስለሚሰማና ያሸናፊነት ስሜት ስለሚፈጥር ነው። ይህ ደስታ ከሌሎች ደስታዎች የሚለየው ደስታው ዘላቂ መሆኑ ነው። ለምሳሌ እኔ ከባለቤቴ ጋር ከተጋባን ወደ አርባ አመት በላይ ሆኖናል። ይህን ሁሉ አመት ስንኖር በባለቤቴ ሁሌም ደስተኛ ነኝ። የትም ውላ ብትገባ አምናታለሁ፤ ይህ የሆነው ደግሞ ዝም ብሎ አይደለም፤ ያኔ እኔና ባለቤቴ ስንጋባ በጫጉላ ቤት የተፈጠረው ደስታ እስካሁን ድረስ አብሮ በመዝለቁ ነው (ቃለ መጠይቅ 12/11/2011 ዓ.ም)።

በ15/11/2011 በሥርዓቱ ከተጋቡ አባቶች ጋር በተደረገ ቡድን ተኮር ውይይትም አንድ ወንድ ልጅ በጋብቻው ዕለት ሙሽራዋ ድንግል ሆና ሲያገኛት የአሸናፊነት፣ ከፍተኛ ደስታ ከመሰማቱም በተጨማሪም በትዳሩ እርግጠኛ ለመሆን እንደሚያስችለው የገለጹ ሲሆን በ16/11/2011 በሥርዓቱ ከተጋቡ እናቶች ጋር በተደረገ ቡድን ተኮር ውይይት ደግሞ አንዲት ሴት በሰርጓ ዕለት ድንግል ሆና መገኘቷ በግንኙነት ወቅት የህመም ስሜት ቢኖረውም በህመሙ ስሜት ውስጥ ግን፣ ለሙሽራዋ ድል አድራጊነት፣ እርግጠኝነት ፣ኩራት እንዲሰማት ሲያደርግ በተቃራኒው ከጋብቻ ውጪ ድንግልና ሲወሰድ ለሴቶች ከፍተኛ የሆነ የተስፋ መቁረጥ ስሜት እንደሚያሳድር በቡድን ውይይቱ ወቅት ተገልጿል።

የአንድ ሰው የመጀመሪያው ወሲባዊ ግንኙነት ለቀጣዩ አመታት ለሚኖረው ወሲባዊ ግንኙነት እርካታ ጋር የተገናኘ ነው። በመሆኑም ሴቶች የመጀመሪያ ጊዜ ወሲባዊ ተራክቧቸው በጋብቻ ዕለት አስደሳች ከሆነ በቀጣይ በትዳር ህይወታቸው ያላቸው ወሲባዊ ግንኙት እርካታ ያለበት መሆኑን የጥናቱ ተሳታፊዎች አረጋግጠዋል (Smith እና Shaffer ፣ 2013) ።

ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር የበቁ ሴቶች ለትዳር አጋራቸው የሚኖራቸው አመለካከት ደግሞ ወ/ሮ በለጡ ተሾመ እንዲህ ይገልጻሉ።

> ሴት ልጅ ድንግልናዋን ያስረከበችው ወንድ የመጀመሪያዋ በመሆን ከሱ ዉጪ ጀግና ያለ መስሎ አይታያትም። ይህ ደግሞ ልቧ ወደ ሌላ እንዳይሸፍትና ተረጋግታ ትዳሯን እንድትመራ ከፍተኛ ጥቅም አለው። ፍቅሯ የጸና እንዲሆን ያደርጋታል። በአብዛኛው የድሮ እናቶች ባሎቻቸው ሲሞትባቸው ሀዘናቸው በእጅጉ የጸና ነበር፤ እስከ ስንት ወር አልጋ ላይ አልተኛም ብለው አመድ ላይ እየተንከባለሉ ሲያለቅሱ ይታያል። ከዚያ በኋላም በፍጹም ሌላ ሰው ገላየን አይነካም በማለት እስከ መጨረሻው ብቻቸውን ይኖራሉ። ይህ የሆነበት ምንም ወንድ ሳያውቁ ስለሚገናኙ ሌላ ባገባ እነደሱ አይሆንልኝም ብለው ስለሚያምኑ ነው (ቃለ መጠይቅ 04/11/2011 ዓ.ም)።

ከላይ ከተጠቀሱት ሀሳቦች የምንረዳው ድንግልናን ጠብቆ ለትዳር መብቃት ለተጋቢዎች፣ ለወላጆች እና ለማህበረሰቡ ከክብርና ከደስታ አንጻር ብሎም የትዳር እድሜን ለማራዘም ከፈተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ያመለክታል።

### 4.3.3. ጤናማ ማህበረሰብ ከመፍጠር አኳያ ያለው ፋይዳ

ኤች. አይ. ቪ. ኤድስ ቫይረስ ከሰው ወደ ሰው ከሚተላለፍባቸው መንገዶች ዋነኛው ልቅ የሆነ ግብረስጋ ግንኙነት ነው። በበሽታው በአብዛኛው የሚጠቁት ወጣቶች ሲሆኑ ወጣት ሴቶች ደግሞ አብላጫውን ቁጥር እንደሚይዙ የተለያዩ ሀገራት ላይ የተጠኑ ጥናቶች ያሳያሉ። ለምሳሌ በአፍሪካና በደቡብ እስያ አገሮች በአብዛኛው በኤች. አይ. ቪ. ኤድስ ቫይረስ የተጠቁት ወጣቶች ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል ወጣት ሴቶች ከፍተኛውን ቁጥር መያዛቸውን (Rosenthal & Moore, 2006) ይገልጻሉ። በማያያዝም ኤች.አይ ቪ. ኤድስ ቫይረስ እያደረሰ ባለው ጥፋት በግንባር ቀደምትነት ተጠቂ የሆኑት እድሜያቸው ከ15-24 የሚገኙ ወጣት ሴቶች መሆናቸውን ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ። "በኤች. አይ. ቪ. ቫይረስ ከተያዙት ወጣቶች ውስጥ የሴቶቹ ቁጥር ከወንዶቹ በሁለት እጥፍ ይበልጣል" (Paterson, 1996) በመሆኑም አንድ ሴት ልጅ እስከ ጋብቻ ዕለት ምንም አይነት ግብረ ስጋ ግንኙነት ካልፈጸመች በግብረ ስጋ ግንኙነት አማካኝነት ከሚተላለፉ በሽታዎች እራሷን ትከላከላለች ማለት ነው። ይህንን ሀሳብ ወ/ሮ አልማዝ ደጀኔ እና ደስታ ማሞ እንዲህ ይገልጹታል።

> በእኛ ዘመን ኤች.አይ ቪ. ኤድስ ባይኖርም በግብረ ስጋ ግንኙነት አማካኝነት የሚተላለፉ በሽታዎች እነደነ ጨብጦ፣ፈንጦ የመሳሰሉ ነበሩ። ነገር ግን በነዚህ በሽታዎች የሚጠቁት ትዳር የመሰሩት ሴቶች እንጂ ትዳር ያልመሰረቱ ወጣቶች ስጋት አልነበረባቸውም ነበር። ምክንያቱም በዚያ ዘመን ከጋብቻ በፊት ወሲብ መፈጸም በማህበረሰቡ ዘንድ ይወገዝ ስለነበር ለበሽታ መጋለጡም አልነበረም። አሁን ግን በተቃራኒው በግብረ ስጋ ግንኙነት አማካኝነት የሚተላለፉ በሽታዎች በበለጠ የሚያጠቁት ወጣቶችን ነው። ይህ ደግሞ በወቅቱ የነበረው ባህል (ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት) በአምራች የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙተን ምን ያህል ከሞት እንደሚታደገው ያሳያል። በተጨማሪም ከጋብቻ በፊት ግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸም ላልተፈለገ እርግዝና ስለሚያጋልጥ ከጤና አንጻር ከፈተኛ ተጽዕኖ አለው። ለምሳሌ አንድ ሴት ልጅ ያልተፈለገ እርግዝና ሲገጥማት ከቤተሰቦቿ እና ከማህበረሰቡ ለመደበቅ ስትል ውርጃ ትፈጽማለች። ይህ ደግሞ ለሞት ሊዳርጋት ይችላል። እርግዝና ባይከሰት እንኳ እርግዝናን ለመከላከል ሲባል የሚወሰዱት መድሀኒቶች ከመውለድ ጋር በተገናኘ ሌላ ችግር እንደሚፈጥሩ ይታወቃል። ከጋብቻ በፊት የወሊድ መከላከያ መድሀኒት መውሰዱ ለመውለድ

ሲፈለግ የሚቸገሩበት ሁኔታ አለ። ይህ ደግሞ በትዳር ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አለው። ልጅ የሚሰጠው ፈጣሪ ቢሆንም በራስ ምክንያት ልጅ መውለድ አለመቻል ሲያጋጥም በጣም ከባድ ነው። በዚህ ምክንያት ትዳራቸውን ያጣሉ። ስለዚህ እነኚህ የጤና ጉዳቶች በተጓዳኝ ትዳር ላይም ችግር ስለሚፈጥሩ ድንግልናን ጠብቆ ለትዳር መብቃት ጠቀሜታው ይህ ነው ተብሎ በአጭሩ የሚገለጽ አይደለም (ቃለ መጠይቅ 05/11/2011 ዓ.ም፤ 13/11/2011 ዓ.ም)።

ይህንኑ ሀሳብ ወ/ሮ ፋናዬ ወርቁ እንደሚከተለው ያጠናክሩታል።

በኛ ማህበረሰብ በቀድሞ ጊዜ ሴት ልጅ ከጋብቻ በፊት ምንም አይነት ወሲባዊ ግንኙነት ስለማይኖራት (ድንግልናዋን ጠብቃ ለትዳር በመብቃቷ) በትዳር ህይወቷ ለመውለድ አትቸገርም። ምክንያቱ ደግሞ ከጋብቻ በፊት ምንም አይነት የወሊድ መከላከያ ስለማትጠቀም ነው ብዬ አምናለሁ። እኔ ለምሳሌ ባገባሁ በአመቴ ወለድኩ መልሼ በሶስት አመቴ ወለድኩኝ ሁሉንም ልጆቼን የወለድኩት በዚህ መልኩ ነው። ከጋብቻ በፊት ምንም አይነት ወሲባዊ ግንኙነት ስላልነበረኝ ምንም መድሀኒት አልተጠቀምኩም። ስለዚህ ከወሊድ ጋር የተጋናኘ ምንም አይነት ችግር አልገጠመኝም። ታዲያ የኔን ነገርኩሽ እንጂ በኛ ጊዜ በተፈጥሮ መካንነት ካልገጠመ በስተቀር መድሀኒት መጠቀም ስላልነበረ ችግሩም አልነበረም። አሁን አሁን ያሉ ልጆች ከጋብቻ በፊት ግንኑነት ይጀምራሉ ከዚያም እርግዝና ሲከሰት ጽንሱን ለማቋረጥ ሲሉ ለብዙ በሽታ ይጋለጣሉ። እርግዝና ባይከሰትና ውርጃ ባይፈጽሙ እንኳ የወሊድ መከላከያ ስለሚጠቀሙ በትዳር ወቅት ለመውለድ ሲሞከሩ ይቸገራሉ (ቃለ መጠይቅ 07/11/2011 ዓ.ም)።

ከተላይ ከተገለጹት ሀሳቦች የምንረዳው ድንግልናን ጠብቆ ለትዳር መብቃት በግብረ ስጋ ግንኙነት አማካኝነት ከሚተላለፉ በሽታዎችና ከስነተዋልዶ ጤና አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ የነበረው መሆኑን ያሳያል።

### 4.3.4. ከኢኮኖሚ አኳያ ያለው ፋይዳ

በ5/11/2011 ዓ.ም በተደርገ ቡድን ተኮር ውይይት እንደተገለጸው አንዲት ሴት ልጅ ድንግልናዋን ጠብቃ ለትዳር ስትበቃ ደስታና ክብር የተሰማቸው ዘመድ አዝማዶች ለሙሽሮች የሚያበረክቱት ስጦታ ለሙሽሮች ትዳር ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ

ያደርጋል። ሥርዓቱን ምክንያት በማደረግ ከተለያዩ አካላት (ከሙሽራው ቤተዘመዶች እና ከሙሽሪት ቤተዘመዶች) የሚገኘው ገቢ ከፍተኛ ነው። ይህ ደግሞ ለሙሽሮቹ የጎጆ መውጫ ይሆናል። ምክንያቱም ማህብረሰቡ በአብዛኛው የሚተዳደረው በግብርና በመሆኑ ሙሽሮችም ለግብርና ስራ የሚያስፈልጉ እንደ በሬ፣ የእርሻ መሬት፣ ላም ወዘተ ሊኖራቸው ይገባል። እነዚህ ተጋቢዎች ደግሞ ከጋብቻ በፊት የሚተዳደሩት በቤተሰባቦቻቸው ስር በመሆኑ የራሳቸው የሆነ ምንም አይነት ሃብት አይኖራቸውም። ስለዚህ በስጦታ ያገኙት ገቢ ለትዳራቸው መነሻ ሀብት ወይም የጎጆ መውጫ ይሆናቸዋል። ለምሳሌ ሙሽሮቹ ከሁለቱ ቤተሰብ በሚያገኙት ወይፈኖች፤ ጥማድ በሬ ይኖናሉ። ይህ ደግሞ ለአንድ ገበሬ ሳይቸገር የእርሻ መሬቱ አርሶ ይከርማል። በመሆኑም ለሁለቱ ተጋቢዎች ከኢኮኖሚ አንጻር መሰረት እንደተጣለላቸው ያሳያል። እንዲሁም በስጦታ በሚያገኟቸው የተለያዩ ነገሮች (ጊደሮች፣ መሬት፣ የቤት እቃዎች፣ ብር፣ ወዘተ) የመተዳደሪያ ሀብታቸውን ይጨምራሉ።

ከላይ ከተገለጸው ሀሳብ የምንረዳው በወቅቱ በነበረው የአኗኗር ዘይቤ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች በሚደረገው የጋብቻ ሥርዓት ከቤተ ዘመድ ለሙሽሮች የሚሰጡ ስጦታዎች ለተጋቢዎች የሚያደርገው ኢኮኖሚ ድጎማ ከፍተኛ መሆኑን ነው።

## 4.4. በሥርዓቱ ላይ እየታዩ ያሉ ለውጦችና የማህበረሰቡ አስተያየት

ይህ ክፍል በዋናነት በሰርግ ወቅት ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች በሚደረገው ሥርዓት ላይ ለውጥ ለመከሰት በምክንያትነት የሚነሱ ጉዳዮችን ከማህበሩ አተያይ አንጻር ይዳስሳል። ከላይ በተገለጹት ልዩ ልዩ መረጃዎች በአሁኑ ወቅት ሥርዓቱ ሙሉ በሙሉ እንደጠፋ ተገልጿል። ሥርዓተ ከበራው በጥንት ጊዜ በሁሉም አካባቢ በሰፊው የሚከወን ሲሆን ቀስ በቀስ ግን በከተማው አካባቢ ያሉት ወረዳዎች የጋብቻ ሥርዓቱ ባህላዊ ይዘታቸው ለቀው ወደ ዘመናዊነት ተቀይረዋል። አሁን አሁን ደግሞ በሁሉም የወረዳው አካባቢ ሙሉ በሙሉ ጠፌቷል። ለውጡን በተመለከከተ ወ/ሮ እጅጋየው ወዳጆ እንዲህ ይገልጹታል።

> ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለሚበቁ ሴቶች ይደረግ የነበረውን ሥርዓት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለወጠ የመጣው ቀስ በቀስ ነበር። በፊት በፊት በነቀታ የሰርግ ሥርዓት ወቅት ይደረግ የነበረው ስረዓት ድንግልናን ጠብቆ ለትዳር መብቃት እንደ

> አንድ የሰርግ ክፍል ትልቅ ቦታ ተሰጥቶት ይከበር ነበር። በተለያዩ ምክንያቶች ግን ቀስ በቀስ እየተለወጠ መጣ፤ ከዚያ ሙሉ በሙሉ ጠፋ። ለምሳሌ በዶረኒ ወረዳ ኦሮሞ ማህበረሰብ በነቀታ (Naqata) የጋብቻ አይነት ቅድሚያውን ድርሻ የሚወስዱት ወላጆች የነበረበት ሁኔታ ቀርቶ ጥንዶች ተፈቃቅደው በውጭ ከጨረሱ በኋላ ለቤተሰብ ሲያሳውቁ ቤተሰብ ደግሶ መዳር ተጀመረ። ሴት ልጅ ድንግልናዋን ጠብቃ ለጋብቻ ስትበቃ ለሙሽሪት ቤተሰብ ያልተሸረፈ ብርሌ፣ ድንግልናዋን ካልጠበቀች ደግሞ የተሸረፈ ብርሌ ይወሰድ የነበረው ባህሉ እየተበረዘ መጣና ወደ ዳቦ መቀየር ጀመረ። በጫጉላ ቤት ከወንዱ ቤተሰብ ተመርጣ የምስራቹን አረጋግጣ ትናገር የነበረችው ሴት ቀርታ ሙሽሮቹ ተስማምተው የምስራቹን ከሰውነታቸው ክፍል አንዱን በስለታማ ነገር በመቁረጥ ሙሽሪት ድንግል የሆነች በማስመሰል ሻሹን ደም ይቀባሉ። ሚዜዎችም የደም ሸማውን ይዘው ለታዳሚ በማሳየት መጨፈር እና ገንዘብ መሰብሰብ ተጀመረ። ይህ የሚሆነበት ምክያት በድሮ ጊዜ ወጣቱ የማህበረሰቡን ባህል በመፍራት ይገለገልበት ስለነበር ነው። ከዚያ በኋላ ወላጆች ሥርዓቱን ይፈልጉት እንጂ ወጣቶች እየተውት መጡ። ለወጡ እየቀጠለ መጣና ወላጆችም ጥያቄውን (ሥርዓቱን) እያላሉት መጡ። በመጨረሻ ወላጆችም ሆኑ ወጣቶች ድንግልናን በተመለከተ ይደረግ የነበረውን ሥርዓት በመተዋቸው ምክንያት ሙሉ በሙሉ ቀረ (ቃለ መጠይቅ 15/11/2011 ዓ.ም) ።

ከላይ የተገለጸውን ሀሳብ በማጠናከር የለውጡን ሁኔታ ታደሰ ቀናአ እንዲህ ያጠናክሩታል።

> ሥርዓቱ በጥንት ጊዜ በሁሉም የወረዳው አካባቢዎች በሰፊው የሚከወን ሲሆን አሁን አሁን ግን ሙሉ በሙሉ ቀርቷል። ለውጡም የመጣው ቀስበቀስ ነው። ቀደም ባለው ጊዜ በከተሞች አካባቢ ይቅር እንጂ በገጠር ከተሞችም ሆነ በገጠሩ ክፍል በደንብ ይከወን ነበር። ሥርዓቱን ከመቀበል አንጻርም ከአዋቂ እስከ ህጻን ሁሉንም ያማከለ ነበር። ምክንያቱም ሁሉም የብሄረሰቡ ክፍል ያልተበረዘ ባህልን ብቻ ይገለገል ስለነበር ነው።እየቆየ ግን ወጣቶች የትዳር ምርጫቸው በራሳቸው ሆነ ማለትም የወላጆች ቀደምትነት ቀረ፤ ለትዳር አጋራቸው የሚያስቀምጡት መስፈርትም ተለወጠ። በዚህ ጊዜ ሁለቱ ተጋቢዎች እርስ በእርስ ይስማሙና ሁሉን ነገር በውጭ ከጨረሱ በኋላ ለወላጆች ያሳውቃሉ፤ወላጆችምጋብቻውን በቀላሉ ይስማማሉ። ይሁን እንጂ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች ይደረግ የነበረው ሥርዓት

> ወላጆች ይፈልጉት ስለነበር ይዘቱን ቀይሮ ይከበር ነበር።አሁን አሁን ግን ወላጆችም ሙሉ በሙሉ ትተውታል (ቃለ መጠይቅ 07/11/2011 ዓ.ም)።

ከላይ ከተገለጹት ሀሳቦች የምንረዳው ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች ይደረግ የነበረው ሥርዓት የቀረው በቅጽበት ሳይሆን ቀስ በቀስ እንደሆነና በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ እንደቀረ ያመለክታሉ።

ለሥርዓቱ መቅረት በምክንያትነት ከሚነሱት ጉዳዮች መካከል የብዙሃን መገናኛ እና የማህበራዊ ድረገጾች መስፋፋት፣ የሀይማኖት ተጽኖ የዘመናዊነት አስተሳሰብ እና ዘመናዊ አስተዳደር ናቸው።

### 4.4.1. የብዙሃን መገናኛ እና የማህበራዊ ድረገጾች መስፋፋት

የማህበረሰቡ ባህል በውስጣዊም ይሁን በውጫዊ ጉዳዮች መነሻነት እየተለወጠ መሄዱ አይቀሬ ነው። ለለውጦቹ በዋናነት የሚጠቀሱት ከሌላ ማህበረሰቦች ጋር ባለው ግንኙነቶች የማህበረሰቡ ባህል መበረዝ፣ የከተሞች መስፋፋት እና የቴክኖሎጂዎች መስፋፋት ነው (Dorsan, 1972 ፣Turner,1967)። የብዙሃን መገናኛ መስፋፋት በተለይም በቴሌቪዥን፣ በድራማ፣ በፊልም፣ በኢንተርኔት፣ በማህበራዊ ድረገጾች አማካኝነት የሚተላለፉ የወሲብ ልቅ ፊልሞች በማህበረሰቡ ዘንድ ተጽኖ በመፍጠር ለባህሉ መጥፋት ከፍተኛ አስተዋጾ አበርክተዋል።

ይህ ጫና በብዛት ወጣቶች ላይ ይስተዋላል። በመሆኑም በብዙሃን መገናኛና በማህበራዊ ድህረገጽ መስፋፋት ምክንያት ለማህበረሰቡ የሚደርሱ መረጃዎች ባህሉ እንዲበረዝ፣ አልፎም እንዲጠፋ አድርገዋል። በተለይ ወጣቶች በነዚህ በመገናኛ ብዙሃንና በማህበራዊ ድህረገጾች አማካኝነት የሌላውን አለም ባህል ከመውረስ (በተለይ የውጩን አለም) አልፎ የራስን ባህል በመተው የሌላውን ባህል እንደራስ አድርገው ሲጠቀሙት ይስተዋላል። በዚህም ምክንያት በጋብቻ ወቅት አንዲትን ሴት ልጅ ከጋብቻ በፊት ድንግልናን እንደመስፈርት ማንሳትም ሆነ ከጋብቻ በኋላ ድንግልናዋን ጠብቃ በመቆየቷ ማወደስ እንደኋላ ቀርነት ይቆጠራል። ይህንን ሀሳብ ወ/ሮ በለጡ ተሾመ እንዲህ ይገልጹታል

> አሁን አንድ ወጣት ለትዳር አጋረነት የፈለጋትን ሴት ያን ያህል በትኩረት አያጠናም፣ ቢያጠና እንኳ የሚያጠናው ገቢዋን፣ የቤተሰቦቿን የሀብት ደረጃ፣

አለባበሷን እና መልኳን እንጂ ድንግል ናት ወይ ብሎ ቢጠይቅ መሳቂያ ነው የሚሆነው። ምክንያቱም ይህንን ጥያቄ መጠየቁ ጨዋነቷን ለማረጋገጥ ነው ብሎ የሚያስብ የለም። እንዲያውም አስተሳሰቡ ኋላ ቀር እንደሆነ ተብሎ ይታመናል። ስለዚህ በወጣቶቹም ሆነ ወላጆች "ፋራ" ላለመባል ጥያቄውን አያነሱትም (ቃለ መጠይቅ 04/11/2011 ዓ.ም)።

አቶ ረጋሳ ገመቹም በ12/11/2011 ዓ.ም በተደረገላቸው ቃለ መጠየቅ እንዲህ በማለት ሀሳቡን ያጠናክሩታል። "ባህሉ እንዲቀር ያደረጉት በየደረጃዉ ያሉ ለዉጦች ናቸው። የቴክኖሎጂ እድገት፣ የሚዲያ መስፋፋትና የመረጃ ልውውጥ መበራከት ባህሉ እንዲቀር ተጽዕኖ ፈጥረዋል። ባህሉን ለማስቀረት በመንግስትም ሆነ በሌላ አካላት የተሰራ ምንም ስራ አልነበረም።" ሲሉ፤ በ 5/11/2011 ዓ.ም  በተደረገ ቡድን ተኩር ውይይትም "ባህሉን ያስቀረው ዘመን ነው። ልጆች ፊልም፣ ድራማ ስለሚያዩ ያዩትን ተግባራዊ እያደረጉ የራሳቸውን ባህል ሊተውት ችለዋል።" በማለት ሀሳቡን ያጠናክራሉ።

ከላይ ከተገለጹት መረጃዎች የምንረዳው የብዙሃን መገናኛና የማህበራዊ ድህረገጽ መስፋፋት ለሥርዓቱ መጥፋት ከፊተኛ ተጽዕኖ ማሳደሩን እንዲሁም በብዙሃን መገናኛና በማህበራዊ ድህረገጽ መስፋፋት አማካኝነት የሚመጣውን ተጽዕኖ ወጣቶች የበለጠ ተጠቂ እንደሆኑ ያመለክታል።

### 4.4.2. ሀይማኖትዊ ተጽዕኖ

ሀይማኖት ተጽዕኖ የሚያደርሰው ሥርዓተ ከበራው ላይ ነው። ሥርዓተ ከበራው ላይ የነበረው መሰረት በግ አርዶ፣ ጨፌ ቆርጦ ወደ ጫጉላ ቤት ይገባ የነበረው፣ የደም ሸማ ይዞ በሙሽሪት እና በሙሽራው ቤት ይጨፈር የነበረው ጭፈራ፣ ሲርባ ዱረባ (Sirba Durba)፣ ደለጋ (Dalaga) የመሳሰሉት በዝማሬ እና በመንዙማ እየተለወጡ መጡ። ሀይማኖት በተለያዩ ባህላዊ ጭፈራዎች ላይ ተጽዕኖ እንደ ፈጠረ Mogos (2011) ለዶረኒ ባህልና ቱሪዝም ስለ ሲርባ ዱርባ (Sirba Durba) ባቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ (Trimingham, 2007) እና (Levine, 2014) በመጥቀስ አረጋግጧል። በመሆኑም ይህ ተጽኖ በተዘዋዋሪ በሥርዓቱ ላይም ተጽዕኖ መፍጠሩን ያመለክታል። አቶ ረጋሳ ገመቹ የሚከተለውን ብለዋል።

ሁሉም ሀይማኖት ዝሙትን ያወግዛል። ሀይማኖት ሁሉም ሰው እራሱን ከዝሙት ጠብቆ ለትዳር እንዲበቃ ያስተምራል። ይህ ማለት ደግሞ በድንግልና ለትዳር

> እንድትበቃ ያዛል ማለት ነው። ነገር ግን ድንግልናን ምክንያት በማድረግ የነበረው ሥርዓት (ጭፈራው፣ የምስራች ማሳየቱ፣ የተሸረፈ ብርሌ እና ያልተሸረፈ ብርሌ ማሳየቱ፣ ስጦታው…) አሁን አሁን ሰዎች ከባህላዊ ክዋኔ ይልቅ ወደ ሀይማኖት በማድላታቸው ቀርቷል። እንዳጠቃላይ በአሁን ወቅት በእኛ አካባቢ በሰርግ ወቅት ከባህላዊ ክዋኔች ይልቅ ጎልተው የሚታዩት ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች ናቸው (ቃለ መጠይቅ 12/11/2011 ዓ.ም) ።

ይህንኑ ሀሳብ አቶ ሞገስ ከበደም በ10/12/2011 ዓ.ም በተደረገ ቃለመጠይቅ እንዲህ በማለት ያጠናክሩታል። "አሁን አሁን በኛ አካባቢ በሰርግ ወቅት ጎልቶ የሚታየው ዝማሬ፣ መንዙማ እንጂ እነሲረባ ዱርባ (Sirba Durbaa)፣ ረገዳ (Ragada)፣ ሆታ እና የመሳሰሉት ብዙም አይታዩም። አያይዘውም በዚህ ጊዜ በሥርዓተ ከበራው ወቅት የሚከወኑት ክዋኔዎች አብዛኛዎቹ ሀይማኖታዊ ክዋኔዎች ናቸው" ይላሉ።

ከላይ ከተጠቀሰው ሀሳብ የምንረዳው ምንም እንኳን ሀይማኖት አስተምሮቱ ማንም ሰው እስከጋበቻ ዕለት እራሱን ከዝሙት እንዲጠብቅ (በድንግልና እንዲቆይ) ቢሆንም በቀጥታ ባይሆንም በሥርዓቱ ላይ ተጽዕኖ እንዳስከተለ ያመለከታል። የተወሰኑ ወደ አካባቢው የመጡ አዳዲስ ሃይማኖቶችና የሀይማኖት አስተምሮቶች ከሥርዓቱ ጋር የሚጋጩ በመሆናቸው ለመቅረቱ ምክንያት ሆነዋል።

### 4.4.3. የዘመናዊ አስተሳሰብ መስፋፋት

ቀደም ባለው ጊዜ ወጣት ሴቶች በትምህርት ሳቢያ ከተወለዱበት አካባቢ የመራቁ ሁኔታ እንብዛም አልነበረም። በዚህ ምክንያት ወጣቶች የአካባቢያቸውን ባህል አክብረው በራሳቸው የአኑኗር ዘይቤ ይኖሩ ነበር። አሁን አሁን ግን የአካባቢ ማህበረሰብ ልጆች በትምህርት ምክንያት ሌላ ቦታ በመሄድ መኖር ሲጀምሩ የሚኖሩበትን አካባቢ ባህል መከተል ይጀምራሉ፤ የሌላዉንም አካባቢ ባህልም ወደ አካባቢያቸው በማምጣት ነባሩን ባህል ይበርዙታል። ይህንን ሀሳብ በተመለከተ ወ/ሮ ፋናዬ ወርቁ እንዲህ ይገልጹታል።

> ልጆቻችን ትምህርት ሲማሩ ካደጉበት አካባቢ እረቀው ይሄዳሉ። ሲሄዱ ደግሞ የራሳቸውን ባህል ለሌላው አውርሰው እነሱም የሌላ ወርሰው ይመጣሉ። በእኛ ጊዜ ትምህርት ስላልነበረ ወላጆቻችን ከአባት ቅድመ አያታቸው የወረሱትን ባህል

ሳይጨምሩ ሳይቀንሱ ሙሉ በሙሉ ያወርሱናል። እኛም ሌላ የምናየው ባህል ስላልነበረ ያንኑ ተቀብለን ተግባራዊ እናደርጋለን። ለምሳሌ ድንግልናን በተመለከተ ለደንግልና የሚሰጠው ዋጋ፣ ባህላዊ ከበራው ሁሉንም ልክ እንደወላጆቻችን ተግባራዊ እናደርገው ነበር። አሁን ግን የኛ ልጆች ትምህርት በመማራቸው የአስተሳሰብ ለወጥ አመጡ። ባህል ከመከተል ይልቅ እነሱ ከሌላ ቦታ ያመጡትን ባህል እኛ እንድንጠቀም አድርገውናል። በመሆኑም ድንግልናን በተመለከተ እነሱ ሲማሩ "ድንግል ነሽ?" ብሎ መጠየቁንም ሆነ ሥርዓቱ ሲያቆሙት እኛም አቆምነው (ቃለ መጠይቅ 07/11/2011 ዓ.ም)።

ከላይ ከተገለጸው ሀሳብ የምንራዳው በትምህርት የተስፋፋው ዘመናዊ አስተሳሰብ ምክንያት ልጆች ከአደጉበት አካባቢ ርቀው መሄዳቸው የራሳቸውን ባህል በመተው የሄዱበትን አካባቢ ባህል እንዲወርሱ አድርጓቸዋል። ወላጆችም የራሳቸውን ባህል ከማውረስ ይልቅ ልጆቻቸው ያመጡትን ባህል እየተቀበሉ መሆኑን ያመላክታል። ስለዚህ ድንግልናቸው ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሰዎች መቅረት መንስኤ ሆኗል።

### 4.4.4. ዘመናዊ አስተዳደር

አንዳንድ ከሥርዓቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተግባራት በዘመናዊ አስተዳድር ውስጥ ተቀባይነት የሌላቸው በመሆኑ ባህሉ እንዲጠፋ የራሳቸውን አስተዋጾ አበርክተዋል። ለምሳሌ አንዲትን ሴት ልጅ ድንግልና የላትም ብሎ መግረፍ በወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም። በ12/11/2011 ዓ.ም በተደረገ ቃለ መጠየቅ "ምንም እንኳን ሥርዓቱን በተመለከተ በህግ እና በደንብ ተደንግጎ ይቅር ባይባልም በአሁኑ ወቅት ድንግልና የላትም ብሎ ሴት ልጅን መግረፍ ወንጀል ነው። ያስቀጣል፤ያሳስራልም።" በማለት አቶ አሰፋ ጉደታ ይገልጻሉ። ከዚሁ ጋር በተገናኘ የሚነሳው ሌላው ጉዳይ ወላጆች ዘመናዊ የልጆች አስታዳደግ ላይ ያላቸው ግንዛቤ ነው። በዚህ ሀሳብ ዙሪያ ወ/ሮ አልማዝ ደጀኔ እና ወ/ሮ ንጉሴ ኡርጂ እንዲህ ይላሉ።

ወላጆች ልጆቻቸው መብትና ግዴታቸውን ከባህል ጋር አጣጥመው እንዲያስኬዱ ከማድረግ ይልቅ ልቅ መተውን እንደመብት ይቆጥሩታል። ለምሳሌ በእኛ አካባቢ ልጆች ቤተክርስቲያን፣ መስጊድ እና ትምህርት ቤት ይሄዳሉ። ሲሄዱ ለምን ሄዳችሁ ወይም አትሂዱ ማለት ሳይሆን ስንት ሰዓት ነው የምትሄዱት? ስንት ሰዓት

ትመለሳላችሁ ብሎ መጠየቅ መብት መጋፋት አይደለም። ወላጆች ለልጅ መብት መስጠት ማለት ልጆች ባህላቸውን ዘንግተው በራሳቸው ፍላጎት መተዳደር ማለት እንዳልሆነ አልተረዱትም። ምክንያቱም ወላጆች ባህልን በትክክል እየነገሩ ቢያሳድጓቸው ልጆችም በቀላሉ እራሳቸውን መከታተል ይችሉ ነበር። ለምሳሌ ሁሉም እምነት ልጆች የእምነት ቦታ ሲሄዱ በስነ ምግባር እንዲያድጉ ያስተምራል። ወላጆች ደግሞ የተማሩትን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ቤት ውሰጥ ባለማስተማራቸውና የነበረውን ተሞክሮ ለልጆቻቸው ባለመንገራቸው ሴት ልጅ ድንግልናን ጠበቆ ለትዳር መብቃት እየቀረ መጣ (ቃለ መጠይቅ 05/11/2011 ዓ.ም፤ 10/11/2011 ዓ.ም) ።

ይህንኑ ሀሳብ በተመለከተ አልማዝ ተሰማ እንዲህ ያጠናክሩታል።

በፊት በፊት ወላጆች ለክብራቸው ስለሚጠነቀቁ ለልጆቻቸው የሚያደርጉት ክትትል ከፍተኛ ነበር። ሴት ልጆች እንደፈለጉ ዘመድ ቤት አይሄዱም፣ ሲረባ ዱረባ (Sirba durba) ለመሄድ የግድ አብሮ የሚሄድ ወንድም ወይም የጎረቤት ልጅ ሊኖር ይገባል ፤ እንጨት ለቀማም ሲኬድ ራቅ ያለ ቦታ ከሆነ የሚላኩት ከእናቶች ጋር ነበር። ልጆችም ወላጆቻቸው አድርጉ ያሏቸውን በሙሉ ያደርጉ ነበር። አሁን ወላጆችም ልጆቻቸውን እንደ በፊቱ አይከታተሉም። ልጆችም “መብት ነው” በሚል ሰበብ ለወላጆቻቸው አይታዘዙም። ልጆች ደግሞ በተለይ አፍላ እድሜ ላይ ሲሆኑ ክፉና ደጉን ለይተው አያውቁትም። ስለዚህ የወላጅ ክትትሉ እየላላ ሲመጣ ባህላዊ ክዋኔዎችም እየቀሩ መጡ (ቃለ መጠይቅ 22/11/2011 ዓ.ም)።

ከላይ ከተጠቀሰው ሀሳብ የምንረዳው ወላጆች ልጆቻቸውን በፊት በነበረው የልጆች አስተዳደግ ባህላዊ ሥርዓቱን ተከትለው ለማሳደግ አሁን ያለው አስዳደር ሁኔታ እንደማይፈቅድላቸው ያመለክታል። በመሆኑም ባህሉን ለማስቀጠል አሁን አሁን በቀጥታ ባይሆንም በተዘዋዋሪ ተጽኖ እንዳሳደረ ያሳያል።

በአጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ በኢሉ አባቦር ዞን ዶረኒ ወረዳ ድንግልናቸውን ጠበቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች ይደረግ የነበረውን ባህላዊ ሥርዓት፣ ሲርባ ዱርባና ድንግል፣ሥርዓቱ ለማህበረሰቡ የነበረው ፋይዳ እንዲሁም ሥርዓቱ አሁን ያለበት ሁኔታ በሰፊው ተዳሰዋል። በቀጣይ ምዕራፍ የጥናቱ ማጠቃለያ ሀሳብና አስተያየት ይቀርብበታል።

# ምዕራፍ አምስት

## 5. ማጠቃለያ እና አስተያየት

### 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ዋና ትኩረቱን ያደረገው በኢሉ አባቦር ዞን ዶረኒ ወረዳ በኦሮሞ ማህበረሰብ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረግ ሥርዓት ላይ ነው። የጥናቱ ዋና አላማ በማህበረሰቡ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች ስለሚደረገው ሥርዓት፣ ለማህበረሰቡ የሚሰጠዉን ማህበራዊና ስነልቦናዊ ፋይዳ እንዲሁም ሥርዓቱ አሁን ስላለበት ሁኔታ ማሳየት ነው። በመሆኑም ይህንን አላማ ከግብ ለማድርስ ስለ ብሄረሰቡ ባህል ጠንቅቀው የሚያውቁ የባህሉ ባለቤቶች እና በሥርዓቱ ጋብቻቸውን የፈጸሙ ግለሰቦች በቃለ መጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት እንዲሁም ከሰነድ ፍተሻ የተለያዩ የጽሁፍና የምስል መረጃዎችን በመመልከት በቂ መረጃ ማግኘት ተችሏል።

የተገኙ መረጃዎችን መሰረት በማድርግ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት በነቀታ (Naqata) የጋብቻ አይነት የሚከወን ሲሆን ሥርዓቱ ምን እንደሚመስል በሚገባ ለማሳየት ይጠቅም ዘንድ በአከዋወኑ ቀደም ተከተል መሰረት ከመተጫጨት እስከ ትዳር ምስረታ ድረስ ያሉትን ሥርዓቶችና ከድንግልና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን በክፍል በክፍል ዳሷል።

በቅድመ ጋብቻ አንዲት ለጋብቻ የታጨች ልጃገረድ ስለሚጠበቅባት ሀላፊነት፣ ለጋብቻ ከታጨችበት እስከ ጋብቻዋ ዕለት የሚደርሱባት ፈተናዎችና እንዲሁም በሁለቱ ተጋቢዎች ቤተሰቦችም የልጆቻቸው ትዳር የሰመረ እንዲሆን የተለያዩ ቀጠሮዎች በመያዝ ሚልኪ አይተው ተጋቢዎቹ ፊት ለፊት የሚገናኙበትን የቀለበት ሥርዓት አዘጋጅተው ሙሽሪትም ሆነች ሙሽራው ለጫጉላ ቤት ለሚኖራቸው ግንኙነት አቅም እንዲኖራቸው በቤተሰቦቻቸው ይቀለባሉ። በተጨማሪም ሙሽሮቹ የሠርግ ቀናቸው ሊደርስ አስራ አምስት ቀናት ሲቀሩት የሙሽሮቹ ጓደኞች በሁለቱ ቤተሰብ ቤት ሲርባ ዱርባ (Sirba Durbaa) በመጨፈር የሰርጉን ድባብ ይፈጥራሉ።

በጊዜ ሰርግ ወቅት ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች ጨዋነታቸውና ባህል አክባሪነታቸውን ለማመልከት በሰርጉ ዕለት የተለያዩ ተግባራትና ክዋኔዎች ይከወናሉ። ምሽት በሙሽራው ቤተሰብ ቤት ሚዜዎች ምስራቹን (የደም ሸማዉን) ይዘው ሲጨፍሩ

የሙሽራው ቤተሰብና ቤተዘመዶቹ ለሙሽሮቹ ስጦታዎች በመስጠትና የተለዩ ጭፈራዎች በመጨፈር ደስታቸውንና አክብሮታቸውን ይገልጻሉ። በሰርጉ ማግስትም ሙሽራዋ ድንግልናዋን ጠብቃ ለጋብቻ መብቃቷን ለማመልከት ወደ ቤተሰቡቿ ቤት ያልተሸረፈ ብርሌ ሲላክ የሙሽሪት ቤተሰብና ቤተዘመዶቿ በተመሳሳይ ሁኔታ ያላቸውን አድናቆትና ክብር በተግባርና በክወና ይገልጻሉ። በተቃራኒው ሙሽሪት ቢጋብቻዋ ዕለት ድንግል ሆና ካልተገኘች በሰርጓ ዕለት ምሽት በባሏ በአለንጋ የምትገረፍ ሲሆን በሰርጓ ማግስት ደግሞ ሙሽሪት ድንግልናዋን ጠብቃ ለትዳር እንዳልበቃች ለማመልከት የተሸረፈ ብርሌ ወደ ቤተሰቦቿ እንደሚላክ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።
በማህበረሰቡ ከሚታወቁ ባህላዊ ጭፈራዎች መካከል አንዱ ሲርባ ዱርባ (Sirba Durbaa) ሲሆን ባህላዊ ጭፈራው ባላገቡ ወጣቶች፤ በሌሊት ሴትና ወንድ በመሆን በጥንድ የሚጨፈር የጭፈራ አይነት ሲሆን በወረዳው ይዘወተር ነበር። ጭፈራው በሚጨፈርበት ጊዜ ወጣቶች የከንፈር ወዳጅ የመያዝ፣ የመሳሳም እና የመተቃቀፍ መብት አላቸው። ነገር ግን ማህበረሰቡ ይህንን ነጻነት ከገደብ ጋር በመስጠቱ ወጣት ሴቶች ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚገጥሟቸውን ፈተናዎች በመቋቋም ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር እንደሚበቁ የሚደረግበት ሥርዓት እንደነበረው መረጃዎቹ ያሳያሉ።

በጥናቱ የታየው ሌለኛው ጉዳይ ድንግልናቸውን ጠብቆ ለትዳር ለበቁ ሴቶች ይደረግ የነበረው ሥርዓት ማህበራዊ ጠቀሜታ ነበረው። ለተጋቢዎችና ለቤተሰቦቻቸው ደስታን፣ እርካታን፣ በራስ መተማመንን፣ መረጋጋትን፣ ኩራትን በመፍጠር የትዳር ፍቺን የመቀነስ ከፍተኛ ስነልቦናዊ ፋይዳ ነበረው። ከጤና አኳያ ደግሞ በግብረ ስጋ ግንኙነት አማካኝነት ከሚተላለፉ በሽታዎችና ከስነ ተዋልዶ ጤና አንጻር ጠቀሜታው የጎላ ነው። ባህላዊ ሥርዓቱ በነበረበት ወቅት ትዳር የሚመሰረተው በከፍተኛ መጠናናት በመሆኑ፣ በተጋቢዎቹና በተጋቢዎች ቤተሰብ መካከል መተማመንንና ፍቅርን ስለሚፈጥርና ሥርዓቱ እድሜም ሆነ ጾታ ሳይለይ ሁሉንም ስለሚያሳትፍ ማህበራዊ ግንኙነትን ከማጠናከር አኳያም ተቀሜታው የጎላ ነው። እንዲሁም ይህ ሥርዓት በሚከወንበት ጊዜ ሁለቱ ተጋቢዎች የሚተዳደሩት በቤተሰቦቻቸው አማካኝነት በመሆኑ በሥርዓተ ከበራው በስጦታ የሚገኘው ገቢ ለተጋቢዎቹ ጎጆ መውጫ ስለሚውል ሥርዓቱ ኢኮኖሚትያዊ ፋይዳ እንደነበረውም መረጃዎች ያሳያሉ።

ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች ይደረግ የነበረው ሥርዓት የቀረው በቅጽበት ሳይሆን ቀስ በቀስ ነው። ቆየት ባለው ጊዜ በሁሉም የወረዳው ቀበሌዎች ቱባ

ባህሉ በስፋት ይከበር ነበር። ከጊዜ በኋላ ደግሞ በገጠሩ አካባቢ ብቻ እየተከበረ በከተማው አካባቢ እየቀረ ሲመጣ የአከባበር ሁኔታውም ይዘቱን እየለቀቀ መጣ። በአሁኑ ጊዜ ባህላዊ ሥርዓቱ በወረዳዋ በሚገኙ በሁሉም ቀበሌዎች ሙሉ በሙሉ ጠፍቷል።

በቴክኖሎጂ መስፋፋት በተለይ ቲቪ፣ ሬዲዮ፣ ድራማ፣ ፊልም፣ ኢንተርኔት፣ ማህበራዊ ድህረ ገጾች በማህበረሰቡ ዘንድ ዘመናዊ እሳቤን በመፍጠራቸው በአሁኑ ጊዜ ባህላዊ ሥርዓቱ ሙሉ በሙሉ እንዲጠፋ አድርገዋል። ለሥርዓቱ መጥፋት በምክንያትነት የሚነሳው ሌለኛው ጉዳይ የሃይማኖት ተጽዕኖ ነው። የሀይማኖትን ተጽኖ በሥርዓቱ ይከወኑ የነበሩ የተለያዩ ክዋኔዎችና ተግባራት (ጭፈራዎች፣ የደም ሽማ፣ የተሸረፈ ብርሌና ያልተሸረፈ ብርሌ የመሳሰሉት) አሁን አሁን በተለያዩ ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች ተተክቷል። እንዲሁም ሥርዓቱ በነበረበት ወቅት ወጣቶች በትምህርት ምክንያት ከትውልድ ቦታቸው ወደ ሌላ ቦታ የመሄድ እድሉ ስላልነበረ የባህል መወራረሱና መበረዙ እምብዛም አልነበረም። በተጨማሪም አሁን ባለው ዘመናዊ አስተሳሰብ ባህሉ ይቅር ተብሎ በህግና በደንብ ባይደነገግም ሴት ልጅ ድንግልናዋን ጠብቃ ለትዳር ባለመብቃቷ መግረፍም ወንጀል መሆኑ፤ ወላጆችም ልጆቻቸውንእንደበፊቱ በራሳቸው መንገድ (በከፍተኛ ቁጥጥርና ቅጣት) ማሳደግ ባለመቻላቸው ለስራዓቱ መጥፋት ምክንያት መሆናቸውን መረጃዎቹ ያሳያሉ።

## 5.2 አስተያየት

ድንግልናቸው ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት ለተጋቢዎች ሆነ ለተጋቢዎች ቤተሰብ በሚያስገኘው ስነልቦናዊ ፋይዳ የትዳር ፍቺን ከመቀነስ አኳያ አስተዋጾ የጎላ በመሆኑ ጠቃሚ ባህሉ የሚያገግመበት ሁኔታ ቢፈለግ መልካም ይሆናል፤
በአሁኑ ስዓት ባህላዊ ሰርዓቱ ሙሉ በሙሉ ከመጥፋቱም ባሻገር ስለሥርዓቱ የሚያቁ የባህሉ ባለቤቶች በእድሜ መግፋት ምክንያት ባህሉን በሚመለከት መረጃዎችን በተገቢው ሁኔታ ለማግኘት አዳጋች እየሆነ በመምጣቱ ሰንዶ ማስቀመጡ ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነው። በመሆኑም የሚመለከተው ክፍል ባህሉን ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ መረጃውን ካሉት የባህሉ ባለቤቶች በድምጽ እና በጽሁፍ ተሰንዶ የሚቀመጥበት ሁኔታ ጊዜ ሳይሰጠው ቢጀመር መልካም ይሆናል፤

በወረዳው የሚኖረው ማህበረሰብ በርካታ ፎክሎራዊ እሴቶች ያሏት ሲሆን በአብዛኛው እየከሰሙ ያሉ በመሆናቸው መሉ በሙሉ ከመጥፋታቸው በፊት ፎክሎራዊ ጥናት በማድረግ በተለያዩ ዘመናዊ መረጃ ማከማቻ ዘዴዎችን በመጠቀም የሚቀመጡበት ሁኔታ ቢመቻች ለመጪው ትውልድ ጠቃሚ ይሆናል፤

በጽሁፍ እና በቪዲዮ ተሰንደው በወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተቀመጡ ባህላዊ እሴቶች በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን በማሰራጨት ባህሉን የሚተዋወቅበት ሁኔታ ቢፈጠር፤

በዚህ ጥናት ከተነሳው ርዕሰ  በተጨማሪ በሌሎች የጋብቻ አይነቶች የሚደረጉ ባህላዊ ሥርዓቶች በንጽጽር ቢጠኑ የተሻለ እይታ ሊሰጡ ይችላሉ። በተጨማሪም የእያንዳንዱ የባህሉ ሥርዓቶች ከተለያዩ ፎክሎራዊ ጽንሰ ሃሳብ አንጻር ቢተነተኑ ጠቃሚ ይሆናል።

# ዋቢዎች


ለማ ንጋቱ (1999ዓ.ም). በየም ብሄረሰብ ጾታ ተኮር ተረቶች የወንድና ሴት ምስል ትንተና ለኤም.ኤ ዲግሪ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ, የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና እና ስነ-ጹሁፍ ትምህርት ክፍል, አዲስ አበባ.

ሰለሞን ተሾመ (2007 ዓ.ም). *የፎክሎር ምንነት እና የጥናቱ ትኩረት አቅጣጫ.* አዲስ አበባ: ፋር ኢስት ትሬዲንግ.

ስንቅነሽ አጣለ (2007 ዓ.ም). *ባህል ለልማት በበርታ ብሄረሰብ. ዶክተሬት ዲግሪ*, አዲስ አበባ  ዩኒቨርሲቲ, የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና እና ስነ-ጹሁፍ ትምህርት ክፍል, አዲስ አበባ.

በጅጋ ተካ (2008 ዓ.ም). *በቱለማ ኦሮሞ ስለባህላዊ የፍቅር ግ ን ኙነቶች ና ኤች አይ ቪ ኤድስ የሚነገሩና የሚከወኑ የስነቃል አይነቶች ይዘት ትንተና.* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ. አዲስ አበባ: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ.

ባህሩ ዘርጋው (2014). *ከፍተኛ የአማርኛ መዝገበ ቃላት.* አዲስ አበባ: Misc Ethiopian Publication.

አዜብ ወርቅነህ (2006 ዓ..ም.). *የከፍቾ ብሄረሰብ የሴቶና የወንዶች አለባበስና አጋጊያጥ.* የኤም.ኤ ዲግሪ ጥናታዊ ጽሁፍ, አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ, በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና እና ስነ-ጹሁፍ ክፍል, አዲስ አበባ.

የራስወርቅ አድማሴ (2004 ዓ.ም). *ባህል ለልማት በኢትዮጵያ.* አዲስ አበባ: ፎረም ፎር ሶሻል ስቱዲ.

ያለው እንዳወቅ (2009 ዓ.ም ). *የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር.* ባህር ዳር: ተፈራ ስዩም አሳታሚ.

ደስታ ወልዴ (2006 ዓ.ም). *የዲዚ ብሄረሰብ የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔ.* የኤም.ኤ ዲግሪ ጥናታዊ ጽሁፍ, አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ, የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት, አዲስ አበባ.

ገላጋይ አለማየው (2005 ዓ.ም). *መልካአ ስብኣት.* አዲስ አበባ: ዜድ ማተሚያ ቤት.

Anette, W. (2010). Virginity testing as a local public health initiative: a ‘preventive ritual’ more than a ‘diagnostic measure’. *Journal of the Royal Anthropological Institute, 16*, 532-550.

Bagby, P. (1963). *Culture and History: Prolegomena to the Comparative Study of Civilizations.* Berkeley: University of California Press.

Bauman, R. (1986). *Story, Performance and Event, Contextual studies of oral Narratives* (Vol. 10). Cambridge: Cambridge University Press.

Ben-Amos, D. (1971). Toward a definition of folklore in context. *The Journal of American Folklore, 84*(331), 3-15.

Bersamin, M., Fisher, D., Walker, S., & Hill, D. G. (2007, August). Defining Virginity and Abstinence: adolescents' interpretations of sexual behaviors. *Journal of Adolescent Health, 41*(2), 182-188.

Carrie, M. R. (2016). *Virginity and Marriage in the early Christian Church.* Athens: University of Georgia.

Cindoğlu, D. (1997). Virginity tests and artificial virginity in modern Turkish medicine. *Women's Studies International Forum*, (pp. 253-261).

Cresswell, J. W., & David, C. (2017). *Research Design: Qualitative and Quantitative Approaches,* (5th ed.). London: Sage Publications.

Creswell, J. (1994). *Research Design: Qualitative and Quantitative Approaches .* London: Sage Publications.

Daniel, L. (2004). *Gender violence and the price of virginity: theory and evidence of incomplete marriage contracts.* University of Chicago Mimeo.

Donald, B. (1991). *Human Universals.* Sage Publications.

Dorsan, R. M. (1972). *Folklore and Folklife: An Introduction.* Chicago and London: University of Chicago Press.

Dundes, A. (1965). The study of folklore in literature and culture: Identification and interpretation. *The Journal of American Folklore, 78*(308), 136--142.

Esra, K. (2015). The social construction of virginity in Turkish context Atheortical perspective. *The Journal of Academic Social Science studies, 40*, 429-438.

Etikan, E., & Musa, S. (2016). Compariosn of convenience sampling and puposive sampling. *American Journal of theoretical and applied statistics, 5*(1), 1-4.

Finnegan, R. (1992). Reflecting Back on Oral Literature in Africa: Some Reconsiderations After 21 Years. *South African Journal of African Languages*, 39-47.

Glassie, H. (1995). Tradition. *The Journal of American Folklore, 108*(430), 395-412.

Gray, D. E. (2018). *Doing Research in the Real World* (4th ed.). London: SAGE Publications.

Green, T. A. (1997). *an Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, music and Art.* California: ABC- CLIO, Inc.

Hajru, L. F. (2013). Virginity-Features and concepts in Kosovo society. *American Academly of clinical Sexlogists*.

Hield, F. (2007). *English Folk Singing andthe Construction of Community.* The University of Sheffield, Sheffield.

Horner, A. E. (1990). *The Assumption of Tradition: Creating, Collecting, and Conserving Cultural Artifacts in the Cameroon Grassfields (West Africa).* PhD Thesis, University of California, Anthropology, Berkley.

Jervis, N. (2011). *What is a Culture?* Retrieved 2019, from http://updateslive.blogspot.com/2011/10/culture-vs-civilization-nancy-jervis.html

Kahn, J., & London, K. (1991). Premarital Sex and the Risk of Divorce. *Journal of Marriage and Family, 53*(4), 845-855.

Kapchan, D. A. (1995). Performance. *The Journal of American Folklore, 108*(430), 479-508.

Kathry, A. W. (2010). *The Power of Virginity: The Political Position and Symbolism of Ancient Rome's Vestal Virgin›.* Oregon: Western Oregon University.

Kevin, K. (2017). *Of Holy Virginity (St.Augustine).* Retrieved 2019, from www.newadvent.org

Korumas, E. K. (2015). The social construction of virginity in Turkish Context Atheortical perspective. *The Journal of Academic Social Science studies, 40*, 429-438.

Levine, D. N. (2014). *Greater Ethiopia: The Evolution of a Multiethnic Society.* London, Chicago: Chicago University Press.

Meraj, A. M. (2018). Importance of Marriage in Islam. *International Journal of Research GrantHaalayah, 6*(11), 1-6.

Mogos, K. (2011 E.C. ). *Naqata: Aadaa Fuudhaafi Heerumaa Oromoo Doorannii.* Elemo: Waajjira Aadaafi Tuurizimii Aanaa Dooranniitti.

Okombo, O., & kabirara, w. m. (n.d.). *Understanding Oral Literature.* Kenya University Press.

Oljira, L., Berhane, Y., & Worku, A. (2012). Pre-marital sexual debut and its associated factors among in-school adolescents in eastern Ethiopia. *BMC Public Health, 12*.

Olson, D. H. (2006). Circumplex model of marital and family systems. *Journal of family therapy, 22*(2), 144-167.

Paterson, G. (1996). *Women in the Time of AIDS: Women, Health and The Challenge of HIV.* Orbis Books.

Rosenthal, D., & Moore, S. (2006). *Handbook of Adolescent Development.* Psychology Press Ltd.

Schoemaker, G. H. (1990). The emergence of folklore in everyday life. *A fieldguide and sourcebook*, p. 3.

Sims, M. C., & Stephens, M. (2005). Living Folklore; An Introduction to the Study of People and Their Traditions. *The Ohio State University and Ohio Wesleyan*.

Singer, R. (2003, June 5). AIDS in Africa: Chastity Tests: Unusual tool for Publlic Health. *Christian Science Monitor*.

Sizemb, P. M. (2009). *Reasons for undergoing virginity testing: A study of young people in rural KwaZulu-Natal.* Durban: Faculty of Humanities, Development and Social Science, University of KwaZulu-Natal.

Smith, C. V., & Shaffer, M. J. (2013). Gone But Not Forgotten: Virginity Loss and Current Sexual Satisfaction. *Journal of Sex and Marital Therapy, 39*(2), 96-110.

Sommers, A. L., & Sommers, M. A. (2000). *Virginity, Everything you need to know about.* New York: The Rosen Publishing Group INC.

Taressa, T. T. (2011). *The Certificate of Virginity:Honor,Marrige and Morocan Femele Immagration.* Colombia: Coluambia University.

Toelken, B. (1996). *Dynamics of folklore.* Logan: Utah State Univeristy Press.

Trimingham, J. S. (2007). *Islam in Ethiopia.* London: Routledge.

Turner, M. B. (1967). Philosophy and the Science of Behaviour.

Tylor, E. B. (1871). *Primitive Culture: Researches Into the Development of Mythology, Philosophy, Religion, Art, and Custom.* London: Burns and Company.

Vansina, J. M. (1985). *Oral Tradition as History.* Wisconsin: University of Wisconsin Press.

Yohannes, M., Tegabu, D., G/Slassie, M., & Gidey, B. (2016). Value Of Virginity Related With Sexual Behaviour And Associated Factors Among Youth In Mekelle City, Northern Ethiopia. *European Journal Of Pharmaceutical And Medical Research, 3*(11), 199-2015.

# አባሪዎች

# አባሪ አንድ

## ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

### ሀ. ግሊዊ መረጃዎችን ለማግኘት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ሙሉ ስም?
2. እድሜ?
3. የትውልድ ስፍራ (የመኖሪያ ስፍራ)?
4. ጾታ
5. መተዳደሪያ?

### ለ. ለመረጃ አቀባዮች የተደረገ ቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

1. በብሄረሰቡ የሚታወቁ የጋብቻ አይነቶች ምን ምን ናቸው?
2. በነቀታ የጋብቻ አይነት ከድንግልና ጋር በተያያዘ የሚከወኑትን ክዋኔዎች በቅደም ተከተል ዘርዝር
3. ድንግልናዋን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት ምን ምንድን ነው? በዝርዝር አስዱ።
4. ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁና ላልበቁ ሴቶች ያለውን የአከባበር ልዩነት ምንድ ነው?
5. ድንግልናን ጠብቆ ለትዳር መብቃት ጠቀሜታው ምንድ ነው?
6. ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች በሚደረገው ሥርዓት ላይ ለውጥ አለ? ካለ ለለውጡ ምክንያቶቹ ምንድናቸው ብለው ያስባሉ?
7. አንድ ሴት ልጅ ታጭታ ለጋብቻ እስክትበቃ መታለፍ ያለባቸዉን ሂደቶች በዝርዝር ያስረዱ፡፡
8. "ሲርባ ዱርባ ጨፍረው ያውቃሉ?" የአጨፋፈር ሁኔታውን ከጊዜ፣ ከቦታ፣ከእድሜ ጋር በመገናኘት ያስረዱ
9. ሲርባ ዱርባ (Sirba Durba) ጨፍረው ያውቃሉ? አጨፋፈሩን፣ ያለውን ጠቀሜታና ድንግልናን ጠብቆ ለትዳር ለመብቃት የሚያስከትለው ተጽኖስ አለው? ካለው ተጽኖውን እንዴት መቋቋም ይቻላል?

**Af-Gaaffii**

Hunduma dura af-gaaffii kanaaf asitti naaf argamuu kessaniif guddaan isin galateeffadha. Af-gaaffileen kun qo'annoo digirii lammaffaa gutachuuf qofa kan oolu ta'uu isaa ibsaa, ragaan naaf kennamu dhugaarratti akka hundaa'u kabajaanan isin gaafadha

**Eenymmaa**

Maqaa Guutuu ______ Saala________ Umurii ________ Hojii _________ Teessoo _________

1. Sirna gaa'ila Aanaa Doranni keessatti beekam maal maali?
2. Sirna gaa'ila naqataa keessatti durbummaa wajjin walqabatee sirnawwan geggefaman dura duuba isaa eggattani nuf tarreessa.
3. Sirni shamarran durbummaa isaani eegani hanga guyyaa gaa'ila isaani ga'aniif godhamu maal maali? Bali'naan utuu nuuf ibsitani.
4. Shamarran durbumma isaani dhabanif gaafa guyyaa gaa'ila isaani irratti sirni kabajaa raawwatamu garaagarummaan isaa maali?
5. Durbummaa eeggatanii hangaa guyyaa gaa'ila ga'uun faayidaa maali argamsisaa?
6. Sirni kabajaa shamarran durbummaa isaani eegani hanga guyyaa gaa'ila isaani ga'aani godhamuu irratti jijjiramni mul'ateera? Yoo jijjiramni jiraatee, sababni isaa maal sinitti fakkaata.
7. Shamarreen tokkoo erga kaadhimamtee hanga guyyaa gaa'ila isheetti sirnootni keessa darbu qabdu bali'inaan nuuf ibsa.
8. Sirba durbaa irratti hirmaattani beektuu? Sirna sirba durbaa yeroo, iddoo fi umrii wajjiin walqabsisaati nuuf ibsa.
9. Faayidaa sirbi durbaa qabuu, akkasumas shamarran durbummaa isaani eegani hanga guyya gaa'ila isaani ga'uuf sirbi durbaa dhibbaa inni qabu maali?

# አባሪ ሁለት

## የቡድን ተኮር ዉይይት መነሻ ሀሳቦች

1. ድንግልናቸውን ጠብቀው ለጋብቻ ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት በየትኛው የጋብቻ አይነት ይከውናል?
2. ድንግልና የምን መገለጫ ነው?
3. በነቀታ የጋብቻ አይነት ከሰርግ በፊትም ሆነ በሰርጉ ዕለት በሚከወኑ ተግባራት ድንግልናን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች ከሚደረጉ ሥርዓት ጋር ግንኙነት ያላቸው የትኞቹ ናቸው?በዝርዝር አስረዱ
4. አንድ ሴት ልጅ ድንግልናዋን ጠብቃ ለትዳር መብቃቷ በምን ይረጋገጣል?
5. ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች በጋብቻ ወቅት የሚሰጧቸው ስጦታዎች ምን ምን ናቸው?
6. ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት ፋይዳው ምንድነው? ከምን ከምን አንጻር በዝርዝር አስረዱ
7. ድንግልናቸውን ጠብቀው ለጋብቻ ለበቁ ሴቶች የሚደረገው ሥርዓት አሁን በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? ለለውጡ በምክንያትነት የሚነሱ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?
8. የሲርባ ዱርባ ባህላዊ ጭፈራ አጨፋፈሩን፣ከጊዜ፣ከቦታ አንጻር በዝርዝር ተውያዩ፡፡
9. በሲርባ ዱርባ ጭፈራዎች ከሚከወኑ(ከሚተገበሩ ተግባራት) ድንግልናን ጠብቆ ለትዳር ለመቃት የሚያጋጠሙ አስቸጋሪ ፈተናዎች አሉ? ካሉ ምን ምን ናቸው?

**MarGaree**

Hunduma dura marii garee kanaaf asitti naaf argamuu kessaniif guddaan isin galateeffadha. Gaafileen mariin garee kanarratti dhiyaatanis ta'ee, deebiiwwan kennaman qo'annoo Mastarsii gutachuuf qofa kan oolu ta'uu isaa ibsaa, deebii siirri ta'e kennuun hirmaannaa ho'aa akka taasiftanii kabajaanan isin gaafadha

1. Sirni kabajaa shamarran durbummaa isaani eggatani hanga guyyaa gaa'ila ga'aniif kabajammi sirna gaa'ilaa isa kam keessatti raawwatamaa?
2. Durbummaan hawaasa naannoo Doranni keessatti maal ibsa?

3. Sirna gaa’ila naqataa keessatti guyyaa cidhaa duraa fi booda shamarran durbummaa isaani eegani hanga gaafa guyyaa cidha isaanii ga’aanif sirnootni geggeffamani isaan kami? Bal’inaan naaf ibsa.
4. Shamarri tokkoo yeeroo gailashee durba ta’uu ishee maalin mirkana’aa?
5. Keennaan shamarran durbummaa isaani eggatani hermannif kennamu maal maali?
6. Durbummaa eegattani heerumuun faayidaa inni qabu bal’inaan nuuf ibsa.
7. Sirni kabajaa shamarran durbummaa isaani eggatani heerumanif godhamu yeroo ammaa maal irra jira? Sababootni jijjira dhufeef ka’ani maal fa’i?
8. Sirna sirba durbaa haala shubbisicha, yeroo fi umrii wajjin walqabsisaati mar’iadha.
9. Sirba durbaa irratti hirmaachuun durbummaa eggatani heerumuuf dhibbaa inni fiduu jira? Yoo jiraate maal fa’i?

## አባሪ ሶስት

## በሥርዓቱ ጋብቻቸውን ለፈጸሙ እናቶች የቀረቡ የውይይት ጥያቄዎች

1. አንዲት ሴት ልጅ በጋብቻ ዕለት  ድንግል ሆና መገኘቷ ምን የተለየ ስሜት አለው?
2. በተላያዩ አጋጣሚዎች አንድት ልጃገረድ ድንግልናዋን ብታጣ በሰርጓ ወቅት ምን አይነት ስሜት የሰማታል?
3. ድንግላናን ጠብቆ ለትዳር ለመብቃት የሚገጥሙ ፈተናዎች ምን ምን ናቸው?

## Gaffile Hadholli sirnaa kaanan ga'la isaanni rawataannif dhihaatan

1. Durbii tokko yeroo gaa'ilashe durbumma qabatte argamuushetti maaltuu itti dhaga amma?
2. shamarren tokko sababota adaadatiin gaa'elan duraa durbumma ishee yoo dhabde yeroo gaa'ilashe maaltu itti dhagahamaa?
3.  Durbuumma qabataanii  erumuuf gaa'ilan dura wantonni gufuu ta,an maal fa.i?

## አባሪ አራት

## በሥርዓቱ ጋብቻቸውን ለፈጸሙ ወንዶች (አባቶች) የቀረቡ የውይይት ጥያቄዎች

1. በጫጉላ ቤት በመጀመሪያ ወሲባዊ ተራክቦ ወቅት ሙሽሪት ድንግል ሆና በመገኘቷ ለወንዶች የሚፈጥረው ስሜት ምንድ ነው?
2. በጋብቻ ወቅት በሚደረገው ወሲባዊ ግንኙነት መሽሪት ድንግል ሆና ባትገኝ በወንዶች ላይ የሚፈጥረው ተጽኖ ምንድነው?
3. በጋብቻ ዕለት ድንግልናን ለመወሰድ የማይቻልባቸው ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው?

## Gaffile Abbotii sirnaa kaanan ga'la isaanni rawataannif dhihaatan

1. Ademsaa Raakoo keessatti shamarren tokko yoo durbumma dhabde dhirootaf maaltuu itti dhagahamaa?
2. Yeroo cidha irratti ykn Wal qunamtii saala yeroo jalqabef tasfamuutti irratti shamaaran tokko yoo durba taatee argamte dhirootaf maaltuu itti dhagahamaa?
3. Yeroo ga'la dhirii tokko halli durbumma itti fudhachu dhadhabuu maal maal fa'i?

# አባሪ አምስት

## የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ተ.ቁ | መረጃ አቀባይ ስም | ጾታ | ዕድሜ | ሥራ | መረጃ የተሰበሰበት ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ታደሰ ሁንዴ | ወ | 74 | ግብርና | ኤሌሞ |
| 2 | ታደሰ ሱፓ | ወ | 79 | ,, | ወይራ |
| 3 | ሂካ ወዬሳ | ወ | 50 | ‘’ | ፋኒ |
| 4 | ፍሪሳ ጉታማ | ወ | 86 | ,, | ቦሬጮ |
| 5 | ጉዲና ዴቢሳ | ወ | 80 | ‘’ | ፋኒ |
| 6 | ኮርሳ ቡሊ | ወ | 48 | ,, | ,, |
| 7 | ፊይሳ አሰፋ | ወ | 33 | | ቦሬጮ |
| 8 | ፍቃዱ ፍሪሳ | ወ | 86 | ,, | ወይራ |
| 9 | ኣሰፋ ዳባ | ወ | 81 | ,, | ,, |
| 10 | ገባዬ ከበዴ | ሴ | 30 | ‘’ | ቦሬጮ |
| 11 | ቀልቤሳ ጅፋር | ወ | 76 | ,, | ,, |
| 12 | አሰፋ ጉዲና | ወ | 48 | መንግስት ሰራተኛ | ኤሌሞ |
| 13 | ሁሴን ሲራጅ | ወ | 45 | ,, | ኤሌሞ |
| 14 | ጫልቱ ተሰማ | ወ | 57 | ግብርና | በዴሳ |
| 15 | አልማዝ ደጀኔ | ሴ | 60 | ግብርና | ኤሌሞ |
| 16 | ፋናዬ ወርቁ | ሴ | 79 | ,, | ወይራ |
| 17 | በለጡ ተሾመ | ሴ | 50 | ነጋዴ | ኤሌሞ |
| 18 | ኢታና ማሞ | ወ | 86 | ,, | ቦሬጮ |
| 19 | ታደሰ ቀነኣ | ወ | 80 | ግብርና | ቦንዳዎ |
| 20 | ደስታ ማሞ | ሴ | 48 | የቤት እመቤት | ፋኒ |
| 21 | እጅጋየሁ ወዳጆ | ሴ | 33 | የቤት | ቦሬጮ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | እመቤት | |
| 22 | ንጉሴ ኡርጂ | ሴ | 86 | ,, | ኤሌሞ |
| 23 | አባይነሽ መረጋ | ሴ | 81 | ,, | ኤሌሞ |
| 24 | ረጋሳ ገመቹ | ወ | 53 | መንግስት ሰራተኛ | ኤሌሞ |
| 25 | አስካሉ ደገፋ | ሴ | 76 | ,, | ፋኒ |
| 26 | አልማዝ ፍቃዱ | ሴ | 38 | መንግስት ሰራተኛ | ኤሌሞ |
| 27 | መዲና መሀመድ | ሴ | 35 | ነጋዴ | ኤሌሞ |
| 28 | ሞገስ ከበደ | ወ | 35 | የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሰራተኛ | ኤሌሞ |

# አባሪ ሰባት

## ፎቶ ግራፎች





አቶ ረጋሳ ገመቹ ቃለ መጠይቅ ሲደረግላቸው አቶ ሞገስ ከበደ ቃለ መጠይቅ ሲደረግላቸው





ወ/ሮ በለጡ ተሾመ ቃለመጠይቅ ሲደረግላቸ አቶ አሰፋ ጉደታ ቃለመጠይቅ ሲደረግላቸው



**አቶ ታደሰ ቀንኣ** ከቃለ መጠይቅ በኋላ



ወ/ሮ አልማዝ ደጀኔና ፋናዬ ወርቁ ከቃለ መጠይቅ በኋላ